"be agurah tennagne yetereta, mehale agedawn yetemetta" (a person who looses the litigation by admission is like a person who has been struck on his leg). He would then request that judgement be entered against the defendant. The party that invoked *"agurah tennagne"* would be required to pay one Birr as a court fee. No appeal was allowed from such a ruling.

C. Introduction of Oral or Documentary Evidence

If the defendant denied some of the facts alleged against him, the facts which were denied had to be proved. The plaintiff may therefore introduce oral or documentary evidence, or both, to prove his allegation.

After both parties had laid their bets and the issue between them had been determined, at least three witnesses from each side would be heard. The witness would openly testify before the court in the presence of the parties or their legal representatives. Where available, documentary evidence would have to be submitted to the court. At this juncture, we should appreciate the admissibility and the probative value of evidence obtained through the what was known as *Yechibette Dagna*.[10]

If, for reasons of old age or serious sickness, a witness was prevented from appearing before the court, the depositions of that witness had to be taken by a judge commissioned for this purpose, the *Yechibette Dagna*. This judge would be informed by the court as to the issues raised, and would be required to report back the testimony of the witness. This judge would therefore go to the locality where such a witness lived, together with the parties to the dispute. He would then hear the testimony of the witness in the presence of the parties, four observers selected by each party and the local *Chika Shum*. On his return, in the presence of the parties, he would report orally the testimony to the judge who had given him the assignment.[11]

If the *Yechibette Dagna* made errors in transmitting the testimony, the method of correction that was used was as follows:

> If he added to, or missed out something from what was stated by the witnesses, the interested party may state: Remember your honour: as God has endowed you with the power of memory, so let God help you to recall what has been testified by So-and-So.[12]

If the *Yechibette Dagna* held to his version, the observers would be required to give their own. Depending on which one was proved correct, either *Yechibette Dagna* would be reproved, or the party which had made the allegation would pay compensation to the *Yechibette Dagna*.

In principle, a witness was not required to tender an oath prior to giving his testimony. He would, however, be required and warned to testify the truth and only the truth.

Failing this, the party against whom the witness tesfified had the right to request the court to require the witness to tender an oath, and this was done during mass, particularly when the holy communion was offered. The witness would close

the door of a church[13] and/or hold the Holy Bible, saying:

> May He perforate me like His cross,
> May He erase me like His picture,
> May He chop me down into pieces like His flesh,
> May He spill me like His blood, and
> May He choke me up as His Altar is closed,
> If I am not telling the truth.

If he had already testified out of court, the other party may impeach the credibility of his testimony or may claim that it may not be admissible at all.

Consanguineous relationship and other relationships, such as those of filiation, godfather, adopted child, godchild and the like, were grounds that could be invoked to bar a person from testifying or to discredit his testimony.[14]

The party which called the witness would, before asking him to testify, warn him as follows:[15]

> One may go to hell after death;
> One may be reduced to bones, laying sick in bed;
> One may also be a permanent inmate of a hospital;
> All the same, one is obliged to tell the truth.

In a similar manner, defendant will advise the witness to tell the truth and ask him to testify that he did not know what was alleged by the plaintiff.

After all the witnesses had given their testimony, the party who felt that most of the witnesses had testified in his favour would pray for judgement to be entered in the following manner.

> As a threshing-ground would go to the one who prepared it, judgement should be made in favour of one who has been proven right.

There were instances where each party to the suit would claim that the testimony given stood in his favour. In such a situation, contentions were settled by mere allocation of the testimony to this or that party by the persons selected as observers. These persons were known as *Intibe Emagne*.[16] Later on, however, a rule was enacted that required the witness who had given the testimony which had

become the object of contention to be recalled, to ascertain as to whom his testimony favoured.[17] His answer would automatically settle the matter.

D. Tatayyaq: be interrogated

In the past, parties to a civil case had no use of such legal institutions as defence witnesses. For the cause of action alleged by the plaintiff, there always lay a claim by the defendant that it should have been he who ought to have had the right to establish whether the alleged cause of action existed or not.[18]

On this point, Rev. M. Russell, commenting on this mode of litigation, wrote the following about 150 years ago:

> The lawyers stand on either side of the plaintiff and the defendant pleading in a loud tone of voice their several causes, during which process wagers of mules, cows, sheep and gold are continually laid by the orators that they will prove such and such charges contained in the libel....[19]

The exercise of such procedural right used to be invoked either by the party to the case personally, or by his counsel. Where such questions of law arose, the other party would say *Kafe*[20] or *Kettebekaye*[21]

On the day fixed for the hearing, the plaintiff, either himself or through his counsel, and before proceeding to the interrogation in accordance with the rules of the *Tatayyaq muget*, would ask whether or not the rules of procedure were correct. If the defendant's answer was in the positive, then the plaintiff would go on throwing out various questions to show the implications of the claim set forth.

The plaintiff was allowed to pose only one question at a time, and the contending party had to give a single and direct answer to every question asked. In this manner, question and answer went back and forth between the adversaries. A bet was laid down to sanction this rule of procedure. To respond anything less or more than what was required amounted to violating the rules of procedure.[22]

If one party violated this rule of procedure, he would be required to produce a guarantee for the payment of the wager made earlier. Whether or not a party had violated these rules was established by the Techewoch. Even where a party readily admitted the commission of such a fault, he nevertheless had to pay the bet.

When the plaintiff finished his questioning, the defendant would in turn start posing questions.

E. Wurd Menzat or Bela Lebelha: art of advocacy and

challenge after the examination and cross-examination of the case had been finalized and before the judge gave his decision, the parties would resort to wurd anezaz, the art of advocacy applied to convince the judge and the persons attending the court session by the use of poetry and eloquent expressions.

At the same time, each party would endeavour to ridicule and harass the other party, by exposing some of the disgraceful deeds alleged to be committed by the opponent, and shameful events that had reputedly occurred in his family background, with a view to discrediting the adversary by making public his weak points.

The following presentation may roughly show the challenge involved:

> Tell me and I will tell you the system
> of the **Ate Ser'at**[23] and the truth of Abraham.
> Never will I speak a lie,
> but the truth and only the truth.
> On one side, the judge,.
> On the other myself,
> The judgement rendered by the judge...
> and an animal slaughtered by the knife of an Adal;
> never shall the judgement be quashed,
> and would not there be a soul to be alive.
> Daring to pay honey,
> Pulling down the enemy to his knees.
> If I have performed a bad deed,
> I regret it.
> But if I have done well,
> you should never let me fail.[24]

In a similar manner, the other party in his turn would endeavour to convince the judge and to ridicule his adversary.

These are many emotion-laden words; none-the-less they resemble the present

legal concept of judgement where opinion is given by both parties, just before the judge sums up the proceedings and renders his judgement.

The other purpose of *wurd menzat* was to win over the judge. In this regard, a **wurd** made by a certain *Basha* Mullatu Wolde Yohannes was believed to have greatly impressed *Afe-Negus* Nessibu:

"A piece of leather thrown into the fire,
A bed splendid with leather attire,
So would Nessibu roast one found to be a liar,
as the piece of leather thrown in the fire,
Warm and soft, he is for the truth,
keeps it in the bosom of the bed,
that it may have warmth."[25]

Once litigation had passed the *wurd anezaz* stage, the *Techewoch* (assessors) would be asked to give their opinion in ascending order of seniority.

F. Opinion Giving and Rendering of Judgement

Techewoch or judges would tender the following catch when giving their opinion as to how the case should be disposed of:

"Let me face my trial and let it be brought before the wronged,
If I did anything wrong and justice is shunned.
Let the enemies of my lord be sent to the sword,
let those close by the lord be beheaded,
and those afar smashed."[26]

The observers, after giving their analysis, would recommend a decision.

Finally the judge would give his reasoned judgement. He would finally say to the plaintiff or the defendant, as the case might be:

"I have decided against you, pay court fees and the bet.[27]

This would be the end of the matter, unless and apeal was lodged to the next higher court.[28]

G. Appeal

An appeal may be based on substantive or procedural issues, including interlocutory matters. Every complaint lodged against the judgement or interlocutory decisions of a court was examined not only by judges sitting in higher courts, but also by *Korqwaris*, i.e. assessors attending the court session.

Appeals made on interlocutory order were not so infrequent as implied by Art. 184 of the Criminal Procedure Code. Whenever one of the parties felt that such interlocutory decisions would be prejudicial to the principal issue, he was justified in making an interlocutory appeal, if, for instance, on a question of title, a ruling was given as regards the mode of proving such subsidiary issues as the existence of a preemptive right in the customary law of a specific society, which would adversely affect the interest of the complainant, unless immediately addressed; then this might be considered as a justifiable ground for lodging an interlocutory appeal.

Another matter that was taken to a higher court, particularly that of the *Afe-Negus*[29], was the question of interpretation of law. The *Yeyigebal Kireker*, a dispute over who has the right to prove an allegation, and questions of interpretation of law were submitted to the *Afe-Negus*, who was assisted by the *Ras Wembers*.[30] For instruction or guidance as to how a set of facts or questions of law were to be interpreted, it was to this court that judges of lower rank had to make reference.

III. CONCLUSION

The system of litigation conducted in accordance with the rules of the *Tatayyaq Muget*, during the last century and the beginning of this century, was indigenous and unique to Ethiopia.

A close observation of the old laws of Ethiopia, as summarized above, reveals that the procedural laws were more developed than the substantive laws. This is attributable to the teachings of scholars of the *Fetha Negast*[31], to the experiences gained in the practice of the legal profession and to the traditional value attached to the practice of bringing up young men as legal apprentices in the courts of governors and in the imperial palace. The fact that litigation, at least as regards the "road-side" courts, was a voluntary and spontaneous form of adjudication has greatly contributed to making the administration of justice a civic obligation of any law-abiding citizen. This and other factors combined have succeeded in making the

traditional procedural laws relatively well developed.

NOTES

1. Esette-Ageba means betting, i.e. agreeing to pay the amount the terms of wager offered by the adversary. Shibeshi Lemma, Yettentu Esat Ageba Muget, senior research paper submitted to the Department of Ethiopian Languages, Addis Ababa University (unpublished), Law Faculty Archives,(1965 Ethiopian Calender).

2. Virgin, Eric, The Abyssinia I knew (London, Macmillan and Co. Ltd. 1956), p.91 quoted in Shibeshi Lemma, **Yettentu Esat Ageba Muget**. op.cit. p.2.

3. In the preamble of most of the proclaimed laws, there was a stipulation to the effect that one had the right to bring a case to a passer-by, and the passer-by had the power to act as a judge and render justice.

4. The "Road-side courts" do not follow the Tatayyaq Muget Procedure.

5. Chika Shum is a local chief.

6. Melkegna is a governor of a locality.

7. At different levels of courts, different members of Techiwoch or Korqwaris (assessors) were selected by both parties and the judge, the number varies from 6 to 8 Techiwoch.

8. All kinds of guarantees were not used in all cases.

9. This was a kind of wager paid in cash, i.e., four Birr for every bet of mar (honey).

10. A commissioned judge.

11. Mateme Selassie Wolde Meskal, Yegnam-Allou Eniwqachew (Addis Ababa, Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University, 1958 Ethiopian Calender) (unpublished), p.39.

12. Ibid.

13. Closing the door of a church takes place for important matters only.

14. Interview with Fitawrari Abebe Gebre, former judge and a high government official knowledgeable about the traditional mode of litigation.

15. Ibid.

16. Assessors nominated afresh for the particular hearing.

17. Mahteme Selassie, op.cit., p. 40.

18. Ibid.

19. Russell, Michael, Nubia and Abyssinia (New York J. and J.Harpper, 1833) p.267, quoted in Shibeshi Lemma, op.cit.p.2.

20. Kafe literally means "with my mouth": technically, however, it is a request for leave to appear with a counsel; such plea entitled one to three days' grace.

21. Kettebekaye is a request for permission to appear with a counsel; it entitled one to seven days' grace.

22. Mahteme Selassie, op.cit., p. 40.

23. Atse Ser'at literally means "The law of the king". It was a way of invoking the customary principles of law that had been applied and recognized by courts as either substantive or procedural law of the country.

24. Mahteme Selassie, op.cit., pp. 40-41.

25. Interview with Bitwoded Zewde Gebre-Heyot, former high government official.

26. Mahteme Selassie, op.cit., p.39.

27. Interview with Fitawarari Abebe Gebre, cited above, at note 11.

28. The list which shows the hierarchy of regular courts prior to 1935 was as follows:

    1) **The Zufan Chilot** (Crown Court)
    2) The **Afe-Negus** Court (Court of national jurisdiction)
    3) **The Shalleka Court** (Court of the Governor)
    4) **Yekal Dagna** (District Court)
    5) **Yesir or Yafer Dagna** (court of first instance).

29. The Chief Justice.

30 Justices appointed by the central government to assist the Afe-Negus with appellate jurisdiction, sitting in six divisions to hear appeals coming from areas allotted to each of the divisions of the court.

31. The Law Book entitled The Law of the Kings. It was introduced to Ethiopia between the 15th and the 16th centuries, and incoperated into the legal system of Ethiopia in 1908 by Menelik II.

የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ
ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት

መዝገብ/ቁ.1272/77

ታህሣሥ 4 ቀን 1978 ዓ.ም

የአዲስ አበባ አውራጃ ፍርድ ቤት
የሥራ ክርክር ችሎት

ዳኛ፥ አቶ ያሬድ አሸናፊው
ይግባኝ ባይ፥ ስለ የኢንተርናሽናል ኮሚኒቲ ት/ቤት አቶ ንጉሴ ፍታወቅ ቀረቡ።
መልስ ሰጪ፥ ሚሰስ ስቬትላና ማሚዶቫ ቀረቡ።
መዝገቡ ያደረው ለምርመራ ነው። መዝገቡን ከሕግ ጋር አገናዝበን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

- <u>ውሳኔ</u> -

ይህ ይግባኝ የቀረበው የሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የግልግል ዳኛ በመልስ ሰጪ በቀረበው አቤቱታ መነሻ አከራክሮ ሐምሌ 24/1977 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው።

በአሁኑ ይግባኝ ባይና በመልስ ሰጪ መካከል በግልግል ዳኛው ፊት ባካሄዱት የፅሁፍና የቃል ክርክር መነሻ የተመለከትነው ፍሬ ክርክር በአጭሩ እንዲህ የሚመስል ነው።

መልስ ሰጪ በግልግል ዳኛው ፊት ያቀረቡት አቤቱታ በኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ ኢትዮጵያዊ ባል በማግባቴ ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሆኔ እየታወቀና ቀደም ሲል

ያለሥራ ፈቃድ መሥሪቱን እየተገነዘበ ይግባኝ ባይ የሥራ ፈቃድ አውጥቶልኝ ከነሐሴ ወር 1977 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ኅዳር 10/1977 ዓ.ም በሙዚቃ አስተማሪነት ቀጥሮ ሲያሰራኝ ከቆየ በኋላ የሥራ ፈቃድሽ የተሰረዘ በመሆኑ ከሥራ ትሰናበቺያለሽ በማለት ያሰናበተኝ ያለአግባብ ስለሆነ ያለአግባብ ከሥራ ከተሰናበትኩ ጀምሮ ያለው ደመወዜ ተከፍሎኝ ወደሥራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት አመልክታለች። ይግባኝ ባይም ቀርቦ ባቀረበው ክርክር ከነሐሴ 1975 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ኅዳር 10/1977 ዓ.ም ድረስ የተቀጠረችው እንደ ውጪ ሀገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ተጠይቆላት በመሆኑ የሥራ ፈቃዷ ተሰርዟል። የሥራ ፈቃድ የተሰረዘበት የውጪ ሀገር ዜጋ ወደሥራ ልመለስ ብሎ መጠየቅ በደንቡ ስለማይችል መልስ ሰጪ ወደሥራ ልመለስ ብላ ያቀረበችው ጥያቄ ውድቅ መሆን አለበትɪ... በማለት ተከራክሯል። የግልግል ዳኛውም ጉዳዩን ካጣራ በኋላ መልስ ሰጪ ኢትዮጵያዊ የሆነ ባል በማግባቷ የኢትዮጵያ ዜግነት ስላላት የሥራ ፈቃዱ መሠረዝ ወይም አለመሠረዝ በሥራ ውሉ ላይ ውጤት የለውም፥ ... በማለት መልስ ሰጪ ከሥራ ከተሰናበተችበት እለት ጀምሮ ያልተከፈላት ደመወዝና ጥቅም ተሰጥቷት ወደሥራዋ እንድትመለስ ወስኗል። ይህ ይግባኝ ባለፈው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የቀረበ ነው። ከውሳኔው ጋር የግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክሮች እና ማስረጃዎች ገልባጭ ቀርቧል።

የይግባኝ ባይ ቅሬታ ያዘለው ፍሬ ሃሳብ - የግልግል ዳኛው መልስ ሰጪዋ ኢትዮጵያዊት ናት በማለት የሰጠው ውሳኔ በሕግም ሆነ በፍሬ ነገር ያልተደገፈ በመሆኑ ውድቅ ተደርጎልን ... በውሳኔ እንዲሻርልን የሚል ነው።

መልስ ሰጪ በበኩላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ ስለ ማንኛውም ክርክር በግልግል ዳኛው ፊት ያቀረቡ በመሆኑ መድገምን አለመፈለጋቸውን በመግለፅ ይግባኝ ባዩ መቃረሚ በሌለው ክርክር ለማንገላታት ሆን ብለው ያቀረቡት ክርክር መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተገንዝቦ የቀረበውን ይግባኝ ባለመቀበል ወደ ት/ቤቱ ተመልሼ እንድገባ በግልግል ዳኛ የተሰጠውን ውሳኔ ያፅድቅልኝ ብለዋል።

ይህም ፍርድ ቤት በይግባኝ በቀረበው መዝገብ ላይ ተገቢ የሆነውን የፅሁፍና የቃል ክርክር ካደረጉ በኋላ መዝገቡን መርምሮ ሊጣሩ በሚገባቸው ነጥቦች ላይ ተገቢ

ማጣሪያ ካደረገ በኋላ በተለይም ስለዜግነት መለወጥ ጥያቄ ላይ ተገቢ እውቀት ያላቸውን ግለሰብ ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የፓስፖርት ቪዛና የዜግነት ክፍል ኃላፊ አስጠርቶ ጉዳዩን አጣርቷል።

ከዚህ በላይ በይግባኝ ባዩና በመልስ ሰጪ መካከል የተካሄዱትን ክርክሮች ጠቅለል ባለ መልክ ለመንደርደሪያ አቅርበናል። ቀጥለን የምንመለከተው ለውሳኔ ከቀረበው ጭብጥ <u>የግልግል ዳኛው የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም</u>? ከሚለው ጥቅል የሆነ የውሳኔ ሃሣባችን መነሻ ሥር ያሉትን ጭብጦች፣ ማለትም

1. የግልግል ዳኛው መልስ ሰጪ ኢትዮጵያዊ ባል ስላገባች ኢትዮጵያዊት ሆናለችና የሥራ ፈቃዱ መሰረዝ ወይም አለመሰረዝ በሥራ ውሏ ላይ ውጤት የለውም ያለው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?

2. ...

የሚሉትን ነጥቦች ከተገቢው ሕግና የአሠራር ልምድ ጋር አገናዝበን የደረስንበትን የውሳኔ ሃሣብ እንደቅደም ተከተላቸው በመመልከት የመደምደሚያውን ውሳኔ እንመለከታለን።

ከላይ ወደ መሠረትነው አንደኛው የውሳኔ ጭብጥ አወሳሰን ስንሄድ የተመለከትናቸው ጉዳዮች ማለትም አንድ የውጪ ሀገር ዜጋ እንዴት ኢትዮጵያዊ ሊሆን ይችላል? በሕጉና በአሠራር ልምዱ የኢትዮጵያ ዜግነት አሰጣጥ እንዴት ነው? እና ሌሎችም ነጥቦች ላይ አንዳንድ ፅንሰ ሃሳቦችን በመዳሰስ እንመለከታለን።

የግልግል ዳኛው መልስ ሰጪ የኢትዮጵያ ዜጋ ናቸው፣ ስለሆነም የይግባኝ ባይ የሥራ ፈቃድ ደብተሩን መሠረዝ ወይም አለመሠረዝ በሥራ ውሉ ላይ ምንም ተፅእኖ የለውም ለሚለው የውሳኔ ሃሣብ መነሻ በ1922 ዓ.ም የወጣው የዜግነት ሕግ ላይ እንደተደነገገው መልስ ሰጪ ኢትዮጵያዊ ባል በማግባታቸው ኢትዮጵያዊ ይሆናሉ ስለሚል ይኸንንም የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በደብዳቤ ስለገለፀ መልስ ሰጪ

ኢትዮጵያዊውን ባላቸውን ካገቡበት ዕለት ጀምሮ ኢትዮጵያዊ ናቸው የሚል መሆኑን ተመልክተናል።

በሕግ ዓለም እያንዳንዱ ሃገር አንድ ግለሰብ ያለውን መብትና ግዴታ የሚወይቀውና የሚያጣው እንዴት እንደሆነ ካሉ ሌሎች ህጎች ጋር በተጨማሪ የዜግነት ሕግ እንደሚኖራቸው ይታወቃል። በእነዚህ የዜግነት ሕጎች ላይ በጥቅሉ የሚነገርላቸው ባሕርይ ነክ መብትና ግዴታ የሚገልፁ ዜግነት እንደሚቀየር የሚገልፁ ድንጋጌዎችና ሌሎችንም የሚሸፍኑ ይደነገጋሉ።

እነዚህ የዜግነት ሕጎች በተለይ የዜግነት መለወጥ ላይ የተለያዩ ድንጋጌዎችን ቢያሰፍሩም ከወዲሁ የእነዚሁኑ ድንጋጌዎች ባሕርይ በሁለት ልንከፍላቸው እንችላለን። ይኸውም አንደኛው ከተወለዱበት ሃገር ዜግነታቸው ሌላ በተጨማሪ በሌላ ሃገር ዜግነት እንዲሰጣቸው በመጠየቅ ዜግነት እንዲያገኙ የሚፈቅድ ጣምራ ዜግነት /dual nationality/ የሚፈቅዱ ሃገሮች እንዳሉ እና በሌላ በኩል ከተወለዱበት ሃገር ዜግነታቸው ሌላ ዜግነት ጠይቀው ያገኙ ከሆነ እንዱን ወይም የተወለዱበትን ሃገር ዜግነት ቀሪ የሚያደርጉ ጣምራ ዜግነት የማይፈቅዱ እንዳሉ እንረዳለን። ሆኖም በየትኛውም ሀገር ሆነ በዓለም ዐቀፍ ሕጎች ላይ የተፃፉ መጻሕፍት ሆነ የየሃገሩ የዜግነት ሕጎች አላማ የምንረዳው ማንኛውም ግለሰብ ለራሱም ሆነ ለልጆቹ ሰብአዊ ክብር ዜግነት ሳይኖረው /stateless/ እንዲኖር አይፈቅድም።

የዜግነት ሕግ መኖር ለምን አስፈለገ? የሚለው ጥያቄ በየእለቱ በምንኖረው ኑሮአችን ውስጥ በየደቂቃው እፈታችን የሚደቀን ጥያቄ ነው። የዜግነት መብት ያለው ግለሰብ በዜግነቱ የሚያገኘው መብት እና የሚጠበቅበት ግዴታ እንዳለ እንደሚያሳውቀን ሁሉ በእንፃሩም በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ ለሚከሰቱ ውጤቶች መፍትሄ ለመሻት በሚቀርቡ ክርክሮች ላይ ተፈፃሚ የሆነውን ሕግ ለመለየት የሚነሳውን ውዝግብ ቀሪ እንደሚያደርገው ካለው የፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው ወይም ኮንፍሊክት ኦፍ ሎው አወሳሰን ላይ የምንረዳው ነው።

ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት ወደ ሃገራችን ስንመለስ የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ 1922 ዓ.ም በአዋጅ በብርሃነ ሰላም በ6ኛው ተራዝ በቁጥር 30 ሐምሌ 15/1922

በወጣው ጋዜጣ ላይ ወጥቷል። የዚህኑ የዜግነት ሕግ እሳቤ ካሉት ድንጋጌዎች አጣምረን ስንመለከት የምንረዳው ሃሳብ በተለይ አንቀፅ 4 ላይ ያለውን ድንጋጌ ከተከታታዮች ጋር ተገናዝበው ሲነበቡ የኢትዮጵያ ዜግነት ሕግ ጣምራ ዜግነት እንደማይፈቅድ እንረዳለን። በዜግነት አሰጣጡ ላይም ሁለት ዓይነት የዜግነት አሰጣጥ እንዳለ እንመለከታለን። ይኸውም:-

> አንደኛው በትውልድ ሃገሩ ለዐቅመ አዳም ሆነ ሄዋን የደረሰ፣ ቢያንስ አምስት ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ የኖረና እራሱን ለማኖር የሚችል፣ አማርኛ ቋንቋ መናገር የሚችልና፣ በቀድሞ ሕይወቱ በወንጀል ተከሶ ያልነበረ ግለሰብ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት የሚሰጥ ዜግነት አንቀጽ 12 ላይ እንደተመለከተው እና
>
> ሁለተኛው እንደአንደኛው ያለምንም ተጨማሪ ጥያቄ የውጭ አገር ዜጋ የሆነች ግለሰብ ከኢትዮጵያዊ ጋር ስትጋባ በጋብቻው ምክንያት የሚሰጣት መሆኑን በዚሁ ሕግ አንቀፅ 2 ላይ ያለውን በመመልከት እንረዳለን። በተለይ በዚህ መዝገብ ላይ ላለው ክርክር አወሳሰን የሚጠቅመውን በጋብቻ የሚሰጠውን ዜግነት የሚደነግገውን ሕግ እንመለከታለን። በ1992 ዓ.ም በኢትዮጵያ ዜግነት ሕግ በአንቀጽ 2 ላይ እንዲህ ይላል። "አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከውጭ ሃገር ሴት ጋር በስርአት የተጋባ እንደሆነ ሴተዮዋ የኢትዮጵያ ዜጋ ትሆናለች።"

በእርግጥ የዚህ ህግ የአማረኛ "ትሆናለች" የሚለው ቃል ከአማርኛው ትርጉም ግልፅ ባለመሆኑ የተለያየ ሃሣብ የሚሰነዝርበት ቢሆንም የእንግሊዘኛው ትርጉም "confer" የሚለው ቃል ይበልጥና ግልፅ እንደሚያደርገውና ሕጉ የሰጣትን መብት የተጠቃሚዋ ግለሰብ ፈቃድ መታከል እንዳለበት እንዲገመት የሚመያደርገው ነው።

በሕጉ አፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱት ችግሮች አማራጭ የሚሆነው ግን የተጋቢዋ ግለሰብ ፍላጎት እና የግለሰቧ የትውልድ ሃገር የዜግነት ሕግ ዜግነት መቀየርን የሚከላከል አለመሆን መታየት እንዳለበት ተደርጎ መታየቱ ተገቢ መሆኑን እንመለከታለን። ምክንያቱም በአንድ በኩል መልስ ሰጪ ወይም ተጋቢዋ ዜግነቱን አልፈልግም ብትልስ ሕጉ አስገዳጅነት አለው ወይ? የሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ አስገዳጅነት የለውም የሚል መደምደሚያ ላይ ስለሚያደርሰን ይህም በግዴታ ሳይሆን እስካሁን በሃገራችን በዚሁ ሕግ አፈጻጸም ላይ ካለው ልምድ መብት ተጠቃሚዋ ተገቢው ክፍል ቀርባ ዜግነቱን መፈለጓን መግለፅና የቀድሞ ዜግነቷን ቀሪ መሆን ማረጋገጥ እንዳለባት እንረዳለን። ይህ ካልሆነ ግን በሕጉ የተሰጠው መብት እንዳለ ሆኖ መብት ተጠቃሚዋ የቀድሞ ዜግነቷ ላይ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ዜግነት እንድታገኝና ካለው የዜግነት ህግ ጋር የሚጋጨው ጣምራ ዜግነት /dual nationality/ እንዲኖራት መንገድ ያመቻቻልና ነው። በዚህ መሠረት በዚሁ ሕግ ተጠቃሚ በሕጉ የተሰጣትን መብት ተቀብላ በዚሁ መብት ያለባትን ግዴታ ለመወጣት ፈቃደኛ ለመሆን በተግባርም ሆነ በተለያየ መስክ የምታሳይ መሆን እንዳለባት እንገነዘባለን። በሌላ አነጋገር ሕግ በክስተቶች መሐከል ያለ ውስጣዊ እውነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነትና ተደጋጋሚነት የሚገልፅ ስለሆነ በሕጉ የተሰጣትን መብት ለመፈለጓ በግልፅም ሆነ ቢያንስ በአኳኋን መጠቆሟ መታየት አለበት።

ከዚሁ አጠቃላይ ግንዛቤ በመነሳት ወደ ደረስንበት የውሳኔ ሃሣብ ከመመልከታችን በፊት የመልስ ሰጪን አጠቃላይ ሁኔታ እንመለከታለን። መልስ ሰጪ

1. ከኢትዮጵያዊ ባላቤታቸው ከአቶ በላይ ደቻሳ ጋር እ.ኤ.አ. 1976 ዓ.ም ሞስኮ ከተማ ተጋቡ።

2. መልስ ሰጪው ወደ ኢትዮጵያ በ1972 ዓ.ም ከመጡ በኋላም ሆነ በሃገራቸው ባለ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ቀርበው ኢትዮጵያዊ ለመሆን በሕጉ የተሰጣቸውን መብት የተቀበሉ ለመሆናቸው አልገለፁም።

3. ኢትዮጵያዊ ካገቡ በኋላ ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1974 ዓ.ም ድረስ ለያሬድ ት/ቤት ያለሥራ ፈቃድ ሥራ ይዘው አገልግለዋል። ከዚያም ደግሞ በተድሞውና ባለው ዜግነታቸው መነሻ የውጪ ሃገር ዜጋ ነኝ በማለት በ20/9/82 ዓ.ም. እ.ኤ.አ በተጻፈ የሥራ ፈቃድ ደብተር እንዲያገኙ የፓስፖርት ቁጥር 376067 የሆነ የUSSR ፓስፖርት እንዳላቸው በመግለጽ ባቀረቡት ፈቃድ መጠየቂያ መሠረት አሠሪው ይግባኝ ባይ ለውጪ ሃገር ዜጎች የሥራ ቅጥር ውል ክፍል ጠይቆ የሥራ ፈቃድ በማውጣት መልስ ሰጪን በአስተማሪነት ከ1975 ዓ.ም. እስከ ኅዳር 10/1977 ዓ.ም. ካሠራቸው በኋላ የሥራ ውሉ በመቋረጡ የሥራ ፈቃድ ደብተሩ እንዲሰረዝ ተደርጓል። የሥራ ፈቃድ ደብተሩም በመልስ ሰጪ እጅ እንዳለ ነው።

4. ከኢትዮጵያዊው ባለቤታቸው ጋር ከተጋቡበት ከ1976 እ.ኤ.አ. ጀምሮ በሕጉ የተሰጣቸውን መብት ሳይጠይቁ ወይም ለመውሰድ ሳይጠይቁ ቆይተው ጥር 7 ቀን 1977 ዓ.ም. ጠይቀው ዜግነቱን ለመቀበል በመፍቀዳቸው የቀድሞውን ዜግነታቸውን በመተው የኢትዮጵያ ዜጋ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ደብተር ሚያዝያ 19 ቀን 1977 ዓ.ም. /የ USSR/ ራሺያ ፓስፖርት መመለሳቸው ተረጋግጦ በዜግነት መዝገብ በሁለተኛው ሺህ አንድ መቶ ስድስተኛው ገፅ ላይ ተመዝግበዋል።

በመጨረሻም ለክርክሩ አወሳሰን ቀጥታ የሆነ ተፅእኖ ባይኖረውም በቅርብ የኢትዮጵያ ዜግነት ደብተር ከወሰዱ በኋላ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ሳያወጡ በUSSR ፓስፖርት ወደ ሃገራቸው ለመሄዳቸው እራሳቸው አምነዋል። በተጨማሪም ለሃገራቸው ኮሚኒስት ፓርቲ ማእከላዊ ኮሚቴ ዜግነቴን ለመቀየር ያለኝን ፍላጎት በመግለፅ አመልክቶ እስካሁን መልስ አላገኘሁም በማለት በ28/3/78 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ገልጸዋል።

ከመልስ ሰጪ አጠቃላይ ምስል በመነሳት ወደ መዝገቡ አወሳሰን ስንመለስ የደረስንበት የውሳኔ ሃሣብ በተለይም መልስ ሰጪ ከይግባኝ ባይ ጋር የሥራ ውል

በፈፀሙበት ወቅት ኢትዮጵያዊት ነበረች? ወይስ አልነበረችም? በሚለው ነጥብ ላይ ያለንን ሃሳብ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

1. ምንም እንኳ በዜግነት ሕጉ ላይ መልስ ሰጪ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ ባል ካገባች ኢትዮጵያዊት ትሆናለች ቢባልም ይኸንኑ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች ሐምሌ 12 ቀን 1977 ዓ.ም. በፃፉት ደብዳቤ ቢገልፁም ከላይ በዝርዝር እንደገለፅነው ይኸንኑ መብታቸውን ለመጠቀም አለመፍቀዳቸውን

ከራሱ ከውጪ ጉዳይ ሚ/ር የአሠራር ልምድ መብቱን ለመጠቀም የቀድሞ ዜግነታቸውን ተረ በማድረጋቸው የተሰጣቸው ደብተር ጥቅም ጋር ተገናዝቦ ሲታይ መልስ ሰጪ ኢትዮጵያዊ ካገቡም በኋላ ሆነ ከዚያም በፊት ከጋብቻው በኋላ በሕጉ የተሰጣቸው የኢትዮጵያ ዜግነት መብት ጋር በተጨማሪ የትውልድ ሃገራቸውን ዜግነት ይዘው መቆየታቸውን ከቀረቡት ማስረጃዎች ተመልክተናል። ይኸውም ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ የሥራ ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው ሊሰሩ ከቆዩ በኋላ ደግሞ የሥራ ፈቃድ በትውልድ ሃገራቸው ዜግነት ደብተር መጠየቃቸውን ስንመለከት መልስ ሰጪ በዜግነት ሕጉ ያልተፈቀደውን ጥምር ዜግነት በማያዝ እንደቆዩ ተረድተናል። ስለሆነም በዚሁ ጊዜ ውስጥ ከይግባኝ ባይ ጋር የፈፀሙት የሥራ ውል በውጪ ሀገር ዜጎች የሥራ አቀጣጠር ደንብ መሠረት ነው ብለናል።

.....

ከይግባኝ ባይ ጋር በፈፀሙት የሥራ ውል ላይ ይዘውት በነበረው ጥምር ዜግነት /dual nationality/ ውስጥ በአንዱ በ USSR ራሺያ ዜግነት እንዲገዛ ፈቅደው የተስማሙበት በመሆኑ የሥራ ውሉ አፈፃፀም እና የውሉ ቀሪነት እንደውጪ ሀገር ዜጋ አቀጣጠር የሚፈፀም ነው ብለናል።

በሃገሪቱም የውጪ ሃገር ዜጎች ቅጥር ውል ላይ ተፈፃሚ በሆነው ደንብ መሠረት አሠሪው የሥራ ፈቃድ ጠይቆ ከተሰጠው በኋላ ሠራተኛው የሥራ ውሉን በመፈፀሙ

የሥራ ፈቃድ ከተሠረዘ ሠራተኛው የሥራ ፈቃዱ የተሰረዘው ያለአግባብ ነው በማለት ወደ ሥራ እንዲመለስ መጠየቅ እንደማይችል የተደነገገ በመሆኑ የመልስ ሰጪ የሥራ ፈቃድ ስለተሰረዘ ወደ ሥራ ልመለስ ይገባል ለማለት እንደማትችል በአዋጅ ቁጥር 64/68 አንቀፅ 14/1 እና በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በወጣው የታህሣሥ 1974 ዓ.ም. መመሪያ የተገለፀ በመሆኑ መልስ ሰጪ ያነሳችውን ክርክር አልተቀበልነውም።

...

የጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ
ሕጋዊ አስተያየት

<u>ዜግነትን በተመለከተ</u>

.... በ1922 በወጣው የዜግነት ሕግ በአንቀጽ 2 "አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከውጪ ሀገር ሴት ጋር በሥርዓት የተጋባ እንደሆነ ሴትዮዋ የኢትዮጵያ ዜጋ ትሆናለች" ይላል። በሁሉም ደረጃ አከራካሪው ነጥብ "ትሆናለች" ማለት ምን ማለት ነው? የሚለው ነበር። ሕጉ ራሱን በራሱ አስፈጻሚ ቢመስልም ጉዳዩን ያየው የአውራጃ ፍርድ ቤት የፈቃደኝነት ሁኔታ መታየት እንዳለበት ያትታል። ሕጉ የፈቃደኝነት መኖርን ስለማረጋገጥ አያወሳም። በእንፃሩም ዜግነትን በማስገደድ ለግለሰብ መስጠት እንደማይቻል ግልጽ ቢሆንም አቤት ባይ ከጊዜ በኋላ የተከራከረችው ሕጉ "በግድ" ኢትዮጵያዊት አድርጎኛል በማለት ነው። ነገር ግን አንዲት ግለሰብ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ብታገባም የቀድሞ ዜግነቷን በተለያዩ ምክንያት ይዛ መቆየት ከፈለገች ሕጉ አይከለክላትም፥ ልምድም ይህን ያረጋግጣል። ብዙ የውጭ አገር ዜጎች ኢትዮጵያውያንን አግብተውም ቢሆን የቀድሞ ዜግነታቸውን እንደያዙ እንደሚቆዩ የምናውቀው ሐቅ ነው። በመሆኑም አንዲት ግለሰብ ኢትዮጵያዊ ማግባቷ ብቻውን ኢትዮጵያዊ ዜጋ ለመሆን ፍላጎት እንዳላት ሊያሳይ አይችልም።

ዜግነት መሠረታዊ የሆነ የፖለቲካ መብት ሲሆን አንድ ግለሰብ ከመንግሥት ጋር የሚኖረውን በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት የሚያመለክትና በዚህም ሳቢያ የኅብረተሰብ አካል የሚያደርገው ሕጋዊ አቋም ነው። ከዜግነት መብት ነፃነትና ግዴታ ይመነጫሉ። ስለዚህም የፈቃደኝነት አለመኖርን የሚያሳዩ ምልክቶች ካሉ ሕጉ የውጭ ዜጋ ለሆነው ግለሰብ ዜግነት የሚፈቅድለት ቢሆንም ግለሰቡ በሕግ ኢትዮጵያዊ ሆንዋል ለማለት አይቻልም። ዜግነትን በማስገደድ መስጠት ስለማይቻልና በእንፃሩም የዜግነት ሕጉ ለምሳሌ ከአንቀጽ 16 እንፃር ባልና ሚስት የተለያየ ዜግነት ይዘው ሊቆዩ መቻላቸው ሲታይ በጋብቻ ምክንያት ኢትዮጵያዊ ዜግነት በዚህ ሁኔታ ብቻ /ማለትም automatically/ ይገኛል የሚል አቋም ትክክል አይሆንም።

በዚህም ረገድ በዜግነት ሕጉ አንቀጽ ሁለት በአማርኛውና በእንግሊዝኛው ቃላት የትርጉም ልዩነት የለም። ስለዚህም የአንቀጽ ሁለት ድንጋጌ "ሴትዮዋ የኢትዮጵያ ዜጋ ትሆናለች" ሲል ሌላ በተጨማሪ የምትጠየቀው ነገር ሳይኖር "ከፈለገች" ኢትዮጵያዊት ትሆናለች ተብሎ መተርጎም ይኖርበታል። በዚህ በቀረበልን ጉዳይ ወ/ሮ ስሺትላና ከጋብቻ ዕለት ጀምሮ ኢትዮጵያዊት መሆን ትችል ነበር። ነገር ግን ግለሰቧ ለኛ ግልጽ ባልሆነልን ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ማለትም ይህ ያሁኑ ክርክር ከተወሰነ ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ኢትዮጵያዊት ለመሆን ፈቃደኛ እንዳልነበረች ወይም ስታወላውል መቆየቷን ወይም ኢትዮጵያዊት ለመሆን አለመወሰንዋን የሚያሳዩ ተጨባጭ ማስረጃዎች ቀርበዋል። የሶቭየት ኅብረት ዜጋ መሆንዋን ገልጻ በሙዚቃ አስተማሪነት ለመቀጠር ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተቀበለችው የሥራ ፈቃድ የሶቭየት ዜጋ ናት ማለቱ ከጋብቻዋ በኋላ በሶቭየት ፓስፖርት ተጠቅማ ሀገሪዋ ደርሳ መመለሷ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዜግነት ጉዳይ ክፍል ቀርባ "ከእ.ኤ.አ. 1985 /ከኅር 1977/ ጀምሮ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ይፈቀድልኝ" ስትል ማመልከቷ ኢትዮጵያዊ ዜግነትን ቀደም ሲል ለመውሰድ ፈቃደኛ እንዳልነበረች ወይም ማወላወሏን ወይም በርግጥ አለመወሰንዋን የሚያሳዩ ማስረጃዎች ናቸው። ከላይ እንደተገለፀው የፈቃደኝነት ሁኔታ በ1922 የዜግነት ሕግ አንቀጽ 2 በግልጽ አልተመለከተም። ነገር ግን ከላይ በተጠቀሰው ምክንያትና ይህ ሁኔታ በአንቀጽ 4 ግልጽ ስለሆነ የፍላጎት መኖርና መገለጽ በአንቀጽ 2 ላይም ሊኖር የሚገባ የሕግ አውጪው ሀሳብ ነው ለማለት ይቻላል።

በአንቀጽ 5 ኢትዮጵያዊት ሴት ከውጭ አገር ሰው ጋር ጋብቻ ብትፈጽም "... የባሏን ዜግነት የምትይዝ የሆነች እንደሆን ..." የኢትዮጵያ ዜግነቷ እንደሚቀር ተደንግጓል። ከዚህ ድንጋጌ ግልጽ የሚሆነው አንዲት ኢትዮጵያዊት የባሏን ሀገር ዜግነት በመቀበል ፈቃደኝነት ማሳየት እንደሚኖርባት እንጂ የባሏ ሀገር የዜግነት ሕግ ስለፈቀደላት ብቻ ኢትዮጵያዊነቷ እንደማይቀር ነው። ይህም ሕግ አውጭው ባንድ በኩል ግለሰቦች ዜግነት ሳይኖራቸው እንዳይቀሩ በሌላም በኩል ጣምራ ዜግነት እንዳይዙ ያበጀው መከላከያ ስለሆነ ይኸው ሁኔታ በአንቀጽ 2 ላይም ተግባራዊ ሊሆን ይገባዋል። ስለዚህም ወ/ሮ ስሺትላና እ.ኤ.አ በ1979 ከኢትዮጵያዊ ጋር ጋብቻ በመፈጸሟ ብቻ በሕጉ ኢትዮጵያዊት ልትሆን ብትችልም የኢትዮጵያን ዜግነት

በተለያየ ምክንያት እስከ እ.ኤ.አ. 1985 ድረስ ለመውሰድ ፈቃደኛነቷን ባለመግለጿ የዜግነት ፈቃድ በዚሁ ዓመት የጠየቀች መሆንዋና ከዚያ በፊት በተሰጣት የሥራ ፈቃድ ላይ የሶቭየት ኅብረት ዜጋ መሆንዋን በመግለጿ ፈቃደኛነቷ ከጊዜ በኋላ የመጣ መሆኑን ማየት ይቻላል። ዜግነቷን ጨምር በዚህ የሥራ ፈቃድ ላይ የተጠቀሱት ዝርዝር ጉዳዮች እሷው በሰጠችው መረጃ ላይ የተመሠረተ ለመሆኑ አልተጠራተርንም። በመሆኑም ግለሰቧ ከኢንተርናሽናል ኮሚኒቲ ትምህርት ቤት ጋር ውል በተፈራረመችበት ወቅት ኢትዮጵያዊት አልነበረችም።

ዜግነትን በተመለከተ በዚህ አቤቱታ ላይ ሊመረመር የሚገባው ሌላው ነጥብ የጣምራ ዜግነት ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ በተለይም ከአንቀጽ 4, 6, 7, 11, 17 እና 18 እንደምንረዳው ጣምራ ዜግነት የተከለከለ ነው። በሌላም በኩል የሶቭየት ኅብረት ዜጋ የሆን/ች/ ዜግነት በጋብቻ አልጓያጣ /ታጣ/ በሶቭየት ኅብረት የዜግነት ሕግ የተደነገገ ነው። በመሠረቱ የሶቭየት ኅብረት ዜግነትን ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለመተው የተወሰነ ሥነ ሥርዓት ተከትሎ ማስፈቀድ የሚያስፈልግ ሲሆን መላቀቅም የሚቻለው ጥያቄው ተቀባይነት ሲያገኝ ነው። በሶቭየት ሕግ ጣምራ ዜግነት በግልጽ የተከለከለ ነው።

ጣምራ ዜግነት የተከለከለ ነው ሲባልም አንድ የውጭ ዜጋ የሆነ ግለሰብ የሶቭየትንም ይሁን የኢትዮጵያን ዜግነት መቀበል የሚችለው የቀድሞ ዜግነቱን የተወ /ወይም በሕጋችን አነጋገር ከቀድሞ ዜግነቱ "የተላቀቀ"/ እንደሆነ ብቻ ነው ማለት ነው። ዜግነቱን ግለሰቡ የሚያገኘው በጋብቻ መሆን አለመሆኑ ለሕጉ አፈጻጸም ልዩነት አይኖረውም።

የሁለቱን ሀገር ሕጎች አገጣጥመን ስናይ የምንደርስበት መደምደሚያ የሚከተለው ነው።

ወ/ሮ ስቬትላና የሶቭየት ዜግነቷን አስፈቅዳ ሳትተው ወይም ሥነ ሥርዓቱንም ሳትከተል የሶቭየት ዜግነቷን አልፈልገውም ሳትልና ይህንኑ ሳታረጋግጥ ኢትዮጵያዊ በማግባቷ ብቻ የሶቭየት ዜግነቷ እንደማይቀር የሶቭየት ሕግ ይደነግጋል። ማለትም

ከጋብቻዋ በኋላም ግለሰቧ ከሶቭየት ሕግ አንፃር የሶቭየት ዜጋ ሆና ቀይታለች ማለት ነው። የግለሰቧም እምነት ባንድ ወቅት ይኸው ነበር። ምክንያቱም ዜግነቷን ለመቀየር ጠይቃ ከጊዜ በኋላ የተፈቀደላት ስለሆነ ነው።

ጣምራ ዜግነትን በተመለከተ የሁለቱ ሀገር ሕጎች ተመሳሳይ አቋም አላቸው ብለናል። የሚለዩት የሶቭየት ሕግ ግልጽ በመሆኑ ነው። ጥቂቶችን የሀገራችንን የዜግነት ሕግ አንቀጾች ብናይ ሕጉ ጣምራ ዜግነትን እንደሚከላከል ማስረዳት ይቻላል። ለምሳሌ በሕጉ አንቀጽ 2 ከአንዲት ኢትዮጵዮዊት ሴትና ካንድ የውጭ ዜጋ የተወለደ ልጅ በአንቀጽ 6 የአባቱን ዜግነት እንደያዘ ይቆጠራል። ከኢትዮጵያዊት በመወለዱ የእናቱን ዜግነት እፈልጋለሁ ያለ እንደሆነ ግን በተቀዳሚ ያባቱን ዜግነት መተውን ማረጋገጥ ይኖርበታል። /አንቀጽ 1ን ያገናዝቧል/። በተመሳሳይ አንቀጽ 9 ባንድ በኩል ጣምራ ዜግነትን በሌላም በኩል ግለሰቦች አለዜግነት እንዳይቀሩ መከላከሉን በቀላሉ ማስተዋል ይቻላል።

ስለዚህ ጣምራ ዜግነትን ይኸን ያህል የሚመከላከለው የኛ ሕግ ሌላው ቢቀር የጣምራ ዜግነት ሁኔታ እንዳይፈጠር ጉዳዩ በአንቀጽ 2 የሚተዳደረው ወ/ሮ ስቬትላና ተጨማሪ ነገር ሳትጠይቅ ለፎርማሊቲ ያህል እንኳ 1/ ሕጋዊ ጋብቻ ከኢትዮጵያዊ ጋር የፈጸምኩ ስለሆነ፥ 2/ የቀድሞ ዜግነቴን /በሶቭየት ሕግ መሠረትም ይሁን ያን ሳልከተል/ የተውኩና ኢትዮጵያዊት ለመሆኔ የወሰንኩ ስለሆነ ይኸው ታውቆ የዜግነት መብቴ ይረጋገጥልኝ ብላ ሳታመለክትና ታውቆም ማረጋገጫ ሳትቀበል በጋብቻ ብቻ ኢትዮጵያዊት ሆናለች ማለት በሕጉም ይሁን ሕጉ በሚያራምደው ፖሊሲ ተቀባይነት የለውም።

የአውራጃው ፍርድ ቤት አስተሳሰብ ግን ግለሰቧ ጣምራ ዜግነት ለመያዝ እንደሞከረች የሚያወሳ ነው። ይህም ያለምክንያት አልነበረም። ግለሰቧ በተለያየ ጊዜ የተለያየ ዜግነት ያላት እንደምትመስል ከፋይሉ ማየት ይቻላል። ጣምራ ዜግነት በሕጋችንም በሶቭየት ሕግም ባለመፈቀዱ ቀደም ሲል በተጠቀሰው ምክንያት በኢትዮጵያ ሕግ ምንም ተጨማሪ ነገር የማይፈለግባት ቢሆንም ግለሰቧ በኋላ

እንዳደረገችው ከሶቭየት ዜግነቷ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሳትላቀቅ ኢትዮጵያዊት ነበርኩ ወይም ሆኛለሁ የሚለው ክርክሯ የሚያጥጣ ሆኖ አላገኘነውም።

ከቀይሉ ካገኘነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አንደኛው ደብዳቤ እንደምንገነዘበው ወ/ሮ ስቬትላና በጋብቻ ምክንያት "ወዲያውኑ" ኢትዮጵያዊት ከሆኑች በሌላም በኩል በሶቭየት የዜግነት ህግ በጋብቻዋ ብቻ የሶቭየት ዜግነቷን ካላጣች ግለሰቧ ጥምር ዜግነት ነበራት ወይ? የሚለውን ጥያቄ ከሌላም አንጻር መመርመር ተገቢ ነው። በርግጥም የሶቭየት ሕግ በሶቭየት ግዛት የኢትዮጵያ ሕግም በኢትዮጵያ ግዛት ተፈጻሚ እንደሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ስለዚህም በኢትዮጵያ ሕግ ግለሰቧ ኢትዮጵያዊት ከሆኑች የሶቭየት ሕግ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈፃሚነት ስለሌለው ኢትዮጵያዊት ናት የሚል ክርክር ይቀርብ ይሆናል። ነገር ግን ግለሰቧ ባንድ አጋጣሚ በሶቭየት ግዛት ብትገኝስ? የሶቭየት ዜጋ ናት ልንል አይደለምን? ክርክሩን ከተቀበልን ግለሰቧ በሶቭየት ሕግ አንፃር የሶቭየት ዜጋ በኢትዮጵያ ሕግ አንፃር የኢትዮጵያ ዜጋ አይደለችምን? ነገር ግን ሁለቱም ሕጎች ጥምር ዜግነትን እንደማይፈቅዱ እናውቃለን። የኢትዮጵያን የዜግነት ሕግ አንቀጽ 4, 6, 7, 9, 11, 17 እና 18 አጣምረን በመመርመር ከመጀመሪያ ዜግነቷ ሳትላቀቅ ሁለተኛውን ዜግነት ልታገኝ አትችልም በሚለው መደምደሚያ ላይ ቀደም ሲል ደርሰናል። ከዚህም አቅጣጫ የፈቃደኝነቷን ሁኔታ ወሳኝ ሆኖ እናገኘዋለን። በዚህ ጉዳይ ላይ ግለሰቧ እንደ እ.ኤ.አ. እስከ 1985 /1977/ ድረስ የሶቭየት ፓስፖርት ይዛ ስትገለገልበት መቆየቷ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሆና ቢሆን ኖሮ ልትፈራረመው የማትችለውን ውል መፈራረሟ የውጭ ዜጋ በመሆንዋ በወቅቱ ውሉ ሊያስከትለው ይችል ከነበረ ብሄራዊ የዜግነት ግዳጅ* ነፃ መሆንዋ የሶቭየት ሕብረትን መንግሥት ካስፈቀደች በኋላ የኢትዮጵያ ዜግነት ከጋብቻዋ ዕለት ጀምሮ ሳይሆን እ.ኤ.አ. 1985/1977/ ጀምሮ

*ግለሰቧ የውጭ ዜጋ ስለነበረች በወቅቱ ብሄራዊ መዋጮ እንድትከፍል አልተጠየቀችም፤ መክፈል አለብኝ ብላም አልተከራከረችም።

እንዲሰጣት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን በራዲ ጽሁፍ መጠየቋና ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያዊነት መመዝገቧ ግለሰቧ እስከ 1985 ድረስ የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ሳይሆን ላለመሆን ፍላጎት እንደነበራት በግልጽ እናያለን።

ግለሰቧ ከሶቭየት ዜግነቷ የተላቀቀችው የሶቭየት ሕግን ተከትላ በሥነ ሥርዓት "ተፈቅዶላት" ነው። ይህን ሥነ ሥርዓት ላትከተልም ትችል ነበር። ይህን ያደረገችው ምናልባትም የተንት ዜግነቷን በተለያየ ምክንያት እንደገና ማግኘት ብትፈልግ በሥርዓት መላቀቁ ጠቃሚ ሆኖ ስለታያት ይሆናል የሚል ግምት መውሰድ ይቻላል።

አስተያየት ሊሰነዘርበት የሚገባው አንድ ሌላ ጉዳይ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚቀርበው የዜግነት ይሰጠኝ ወይም ይፈቀድልኝ ጥያቄ ሕጋዊ ትርጉም ነዉ። በዘልማድ "ፈቃድ" ይጠየቅ እንጂ መሥሪያ ቤቱ ዜግነት "አይሰጥም"። ዜግነት የሚገኘውም ይሁን የሚሰጠው በዜግነት ሕጉ ሲሆን አስፈጻሚው ግን በሕጉ እንደተመለከተው የተጠቀሰው መሥሪያ ቤት ነው። አንድ ግለሰብ ማመልከቻ ሲያቀርብ በሕጉ ዜግነት ላገኝ እችላለሁ ፈቃደኛ ነኝ ይታወቅልኝ ወይም እንዳገኝ ይደረግ ማለቱ ነው። ካለው አሠራር እንደተረዳነው አመልካች ጥያቄውን በሚያቀርብበት ወቅት የቀድሞ ዜግነቱን የሚመለከት መሠረታዊ ማስረጃዎቹን ለሚኒስቴሩ ይመልሳል ወይም አግባብ ላለው አካል ለመመለሱ ማስረጃ ያቀርባል። ሚኒስቴሩም በኢትዮጵያዊነት መዝገቦ መታወቂያ ይሰጠዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ የሆነውም ይኸው ነው። አቤት ባይዋ ጥር 7 ቀን 1977 ባቀረበችው ማመልከቻ መነሻ ሚያዝያ 17 ቀን 1977 የተፈረመ የኢትዮጵያዊ ዜግነት መታወቂያ ደብተር ከመሥሪያ ቤቱ ተቀብላለች።

ያገቡ ሴቶች ዜግነት በኢትዮጵያ ሕግ

ጌታቸው አበራ*

- ሀ -

በ1930 በወጣው የኢዮጵያ የዜግነት ሕግ ላይ ስለ አገቡ ሴቶች ዜግነት የሚያወሱት አንቀጾች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለተለያዩ ትርጓሜዎች መንስኤ ሆነዋል። በወ/ሮ ስቬትላና ማማዶቫና በአሜሪካን ኮሙኒቲ ት/ቤት መሐከል የተነሳው የሥራ ክርክር[1] ላይ ዋና አርእስት የሆነው ስለ አንዲት ከኢትዮጵያዊ ጋር ስለተጋባች ሩሲያዊት ዜግነት ጉዳይ ነበር፤ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የግልግል ዳኛ ወ/ሮ ስቬትላና ኢትዮጵያዊ ዜጋ ስላገባች፣ በዚሁ ጋብቻ ምክንያት ኢትዮጵያዊት ሆናለች ብሎ ወስንዋል። በይግባኝ ጉዳዩን የሰማው የአውራጃ ፍርድ ቤት ግን ወ/ሮ ስቬትላና ኢትዮጵያዊ ስላገባች ብቻ የኢትዮጵያ ዜጋ ልትሆን አትችልም ብሎ ወስንዋል። ይህም ውሳኔ በተሟይነት በአቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ተቀባይነት አግኝቷል።

የአውራጃው ፍ/ቤት ውሳኔ፣ ኢትዮጵያዊ ስላገቡ የውጭ ዜጋ ሴቶች ዜግነት ጉዳይ ሁለት ጠቃሚና አስፈላጊ ጭብጦችን ያነሳል፤ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት በውጭ አገር ዜጋ ሴቶችና በኢትዮጵያ ዜጋ ወንዶች መሐከል የሚደረገው ጋብቻ በሴቶች ዜግነት ላይ ምን ውጤት ያመጣል? አንድ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት፣ አንዲት ከኢትዮጵያዊ ጋር የተጋባች የውጭ ዜጋን፣ ህጉ ጣምራ ዜግነትን ይከለክላል በሚል ምክንያት ብቻ የኢትዮጵያ ዜግነት ሊከለከላት ይችላልን?

በዚህ ፅሁፍ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያገቡ የውጭ አገር ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ በ1930** በወጣው የኢትዮጵያ የዜግነት ሀግ ውስጥ የተደነገጉት አንቀጾች፣ ከድር

---

* የትርፍ ጊዜ ሌክቸረር፣ ሕግ ፋኩልቲ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

** በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ያለው የጊዜ አቆጣጠር ሁሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ነው።

ጀምር በተለምዶ በሚታወቀው የቤተሰብ አንድነት መርህ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ለማሳየት ተሞክሮዋል። ለዚህም አሳማ ሊባል ስላገቡ ሴቶች የሚያወሳውን የኢትዮጵያን የዜግነት ሕግ ትክክለኛ ትርጉሙን ለማስቀመጥ ስላገቡ ሴቶች ዜግነት የሚደነግገው ሕግ ዕድገት ተመርምሯል። በመቀጠልም ስለጣምራ ዜግነት አጠር ያለ ማብራሪያ ተሰጥቷል። ይህም የሆነው በዚሁ ጉዳይ ላይ የተለያዩ አስተያየቶችና ትርጓሜዎች ስለታዩ ነው። በ1930 ዓ.ም. የወጣው የዜግነት ሕግ ምንጮች ይሆናሉ የተባሉትን ሁኔታዎች ከገመገምን በኋላ ይህንን ሕግ በመጠቀም የአውራጃው ፍ/ቤት ኢትዮጵያዊ ስላገባች የውጭ አገር ሴት ዜግነት ጉዳይ የሰጠውን ብይንም እንመረምራለን። በመጨረሻም በማጠቃለያ መልክ በሕግ ማውጣትና በዳኝነት ሥራ መሐከል ያለውን ልዩነት፣ እንዲሁም አንዱ በሌላው ሥራ ጣልቃ ሲገባ በዝምታ ማለፉ የሚፈጥረውን ችግርና ውጤቶቹን በተመለከተ አንዳንድ አስተያየቶች ይሰጣሉ።

- ለ -

የዜግነት ፅንስ ሃሳብ ዕድገት በቅድመ ሁኔታነት የሉዓላዊ አገሮችን መፈጠርና የአለም አቀፍ ግንኙነት መኖርን ይጠይቃል።[2] አንድ አገር ከሌሎች አገሮች ጋር አለም አቀፍ ግንኙነት ከሌለው ለዚያ አገር ህዝብ የዜግነት ህጎች መታወጅ ምንም ፋይዳ የለውም። ሌሎች አገሮች ከሌሉ እናም አለም አቀፍ ግንኙነት ከሌለ፣ ፓንሁይስ "አጋጣሚ ጉዳዮች"[3] ያላቸው ችግሮች አይነሱም። ብዙ አገሮች ባሉበት ሁኔታ ውስጥ የተጠናከረ የእርስ በርስ አለም አቀፍ ግንኙነት ስለሚኖር፣ በዚያን ወቅት አንድ ግለሰብ የዚህ ወይም የዚያ አገር ዜጋ ነው የሚል ችግር ይነሳ ይሆናል። አንድ ሰው የዚህ ወይም የዚያ አገር ዜጋ ነው ብሎ የመለየት ችግር በተጨባጭ መልኩ የተከሰተው የብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ግዴታ ሲጀመርና የብሄራዊ ፖለቲካዊ መብቶች ለዜጎች ሲታወጁ ነው።[4]

አንድ ግለሰብ የአንድ አገር ዜጋ ነው ብሎና ከሌሎች አገሮች ዜግነት ለይቶ መወሰን፣ በግዴታ በአገሮች መሐከል ግንኙነት መኖሩን ያሳያል። እንግዲህ ይህ የሚያሳየን የዜግነት ጥያቄዎች በመርህ ደረጃ መወሰን ያለባቸው በአለም አቀፍ ሕግ መሆኑን ነው።

ይሁን እንጂ፣ የዜግነት ፅንሰ ሐሳብ የቅርብ ጊዜ ክስተት በመሆኑ፣ አለም አቀፍ ሕግ እስካሁን ድረስ የዜግነትን ጉዳይ የሚዳኙ ተጨባጭ ሕጎች አላወጣም። አለም አቀፍ ህግ በደፈናው እያንዳንዱ አገር እነማን ዜጎቹ ሊሆኑ እንደሚችሉ በራሱ የውስጥ ሕግ የመወሰን መብት እንዳለው ይቀበላል።[5]

ስለዚህም ያገቡ ሴቶች ዜግነት በእያንዳንዱ አገር ሕግ መሠረት ይወሰናል ማለት ነው። ስለአገቡ ሴቶች ዜግነት ጉዳይ የሚደነግጉ የተለያዩ አገሮች የዜግነት ሕግ ድንጋጌዎች ከሁለት መሠረታዊ መርሆዎች በአንዱ ይመራሉ። አንደኛው መርህ ሚስት የባሏን ዜግነት እንድትይዝ ሲጠይቅ፣ ሁለተኛው መርህ ደግሞ ሚስት ዜግነቷን እራሷ እንድትመርጥ መብቷን ለእራስዋ ይተውዋል። እስከ አንደኛው የአለም ጦርነት ማብቂያ ድረስ ብዙ አገሮች ያለ ልዩነት የመጀመሪያውን መርህ ይከተሉ ነበር፤ በዚህም መሠረት ጋብቻው ለሴትዮዋ የባሏን ዜግነት ይሰጣት ነበር። ሚስት የባሏን ዜግነት ማግኘትዋ ትክክል ነው በማለትም ብዙ ክርክሮች ቀርበዋል። አንደኛው ክርክር የቤተሰብን አንድነት ለመጠበቅ ሲባል ሚስት፣ ባልና አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ሁሉ አንድ ዓይነት ዜግነት ሊኖራቸው ይገባል የሚል ነው። የዚህ ክርክር መንፈስ ይህን ዓይነቱ ሥርዓት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ባልና ሚስት ታማኝነታቸውን ለተለያዩና ምናልባትም ሊቃረኑ ለሚችሉ መንግሥታት ሲገልፁ የሚደርሰውን ችግር ያስቀራል የሚል ነው።

ባልና ሚስት ለተለያዩ የህግ ሥርዓቶች ተገዥ በሚሆኑበት ጊዜ በዜግነታቸው የሚጠበቅባቸውን ልዩ ልዩ ሕጋዊ ግዴታዎች ለመወጣት ሲሉ ከግልም ሆነ ከጋራ ሀብታቸው ላይ በሚከፍሉበት ጊዜ በቤተሰቡ ላይ ከባድ ችግሮች ሊደርሱ ይችላሉ።[6] ከመንግሥት ጥቅም አኳያ ሲታይም አንድ መንግሥት ሉዓላዊነቱን የሚቀበል፣ አንድ ወጥና ያልተከፋፈለ ቤተሰብ ይፈልጋል የሚል ክርክርም አለ። ብዙውን ጊዜ እንደሚታየው ሚስት ከጋብቻ በኋላ ወደ ባሏ የዜግነት አገር ትሄዳለች። እንዲሁም ማንኛውም በአንድ አገር ግዛት ውስጥ ያለ ሰው ለዚያ አገር መንግሥት ታዛዥነት ይጠበቅበታል። በተጨማሪም ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ ቤተሰብን እንደ አንድ የዜግነት መሠረታዊ አካል መውሰድ ለመንግሥት ያመቸዋል የሚል አስተያየትም አለ።

እዚህ ላይ አንድ ግልፅ የሆነ ነገር አለ፤ ይኸውም የቤተሰብ አንድነትን ወይም አንድ ወጥ ለመንግሥት ታማኝነትን ለመጠበቅ ሲባል የአንዲት ሴት ፈቃድ ሳይጠየቅ የባሏን ዜግነት እንድትይዝ ማድረግ ሚዛናዊነት የጎደለው አሠራር ነው። ምክንያቱም ይህ ዓይነቱ አሠራር ሴትዮዋን በቀጥታ በሚያገባት ጉዳይ እንደግለሰብነቷ ያላትን የማይገሰስ መብት አላወቀላትም።

ሚስት የባሏን ዜግነት እንድትይዝ በተደረገበት መንገድና፣ ባልየው የሚስቲቱን ዜግነት እንዲይዝ በማድረግ የቤተሰቡን አንድነትና አንድ ወጥ ለመንግሥት ታማኝነት ሊጠበቅ ይቻል ነበር። አብዛኛውን ጊዜ እንደታየው ሚስት የባሏን ዜግነት እንድትይዝ ይደረጋል እንጂ፣ ባል የሚስቱን ዜግነት እንዲይዝ አይደረግም።[7] አንዳንዴ ባል በሚስት የዜግነት አገር በሚኖርበት ጊዜ ዜግነትን ለማግኘት በሚደረገው ሥነ ሥርዓት ውስጥ የግል ተግባርና ፍላጎት አብረው እንዲገኙ ዕድል ይሰጣል። ይህንን ዕድል ግን ሚስት አታገኝም።

ይህ በአገቡ ሴቶች የዜግነት ህግ ላይ የሚታየው የሴቶችን መብት ከቁብ አለመቁጠር የኋላ ቀርነት ምልክት ነው። በፊውዳል ሥርዓተ ማህበር ውስጥ ካቆጠቆጠው የወንድ ትምክህተኝነት በፊት የነበረው የአገቡ ሴቶች የዜግነት ህግ የተሻለ ሰብአዊነትና እኩልነት የሚታይበት ነበር። በጊዜው የነበረው ህግ በሮማውያን ህግ ውስጥ በታወቀው "ማንም ሰው ዜግነቱን እንዲቀይር ወይም በያዘው ዜግነት እንዲፀና አይገደድም" በሚለው መርህ ላይ የተመሠረተ ነበር።[8]

በአሜሪካን አገር እስከ 1855 ድረስ የዜግነት ማግኘት፣ ማቆየትና ማጣት ጉዳዮች የሚወሰኑት ዜግነቱ በሚመለከተው ሰው ፈቃድ ነበር። በእርግጥም ይህ ነፃነት ተፈጥሮአዊ እና የማይገሰስ የሁሉም ሰዎች መብት እንደሆነ የሚቆጠርና "በሕይወት፣ በነፃነት እና በደስታ ለመኖር" እጅግ አስፈላጊ መብት ተደርጎ ይታይ ነበር።[9]

ይሁን እንጂ ማንም ሊረዳው በሚችል መንገድ፣ ይህ የአሜሪካን ህግ አቋም ብዙም ሳይቆይ ወደ ወንድ ትምክህተኝነት ወጥመድ ገባ። በ1955 ዓ.ም. የአሜሪካን

ህግ አውጪ ምክር ቤት የአሜሪካ ዜግነትን አሜሪካዊ ባል ላገቡ የውጭ አገር ሴቶች የሚሰጥ ህግ አሳለፈ።[10] እንዲሁም በ1907 ዓ.ም. ይኸው ምክር ቤት ባወጣው ሌላ ህግ፥ አንዲት አሜሪካዊት ሴት የውጭ አገር ዜጋ ካገባች የባሏን ዜግነት እንደምትይዝ ወሰነ፥ ማለትም የአሜሪካ ዜግነቷን አጣች ማለት ነው።[11]

በዚህም እርምጃ የአሜሪካን የዜግነት ህግ "ዘመናዊ" ተደርጎ በብሪታኒያ የህግ ሥርዓት ከ1944 ጀምሮ ይሠራበት ከነበረው ከኮመን ሎው መርህ ጋር ሊጣጣም ችሏል። በእንግሊዝ አገር እስከ 1844 ድረስ የአንዲት ሴት ዜግነት በጋብቻ ምክንያት አይቀየርም የሚለው የኮመን ሎው መርህ ይሠራበት ነበር።[12] ይህ ህግ የብሪታኒያ ዜጋ ላገቡ የውጭ አገር ሴቶችም ሆነ የውጭ አገር ዜጋ ላገቡ የብሪታኒያ ዜጋ ሴቶች ይሠራ ነበር።[13] የዚህ ህግ መሠረት የሆነው ሀሳብ፥ አንድ ዜጋ ለሀገሩ ንጉሥ ያለው ታማኝነት በዚያ ሰው የግል ፈቃድ ሊቀየር አይችልም ከሚል ፊውዳላዊ የታማኝነት ፅንሰ ሀሳብ የመነጨ ነው።

ይህ የኮመን ሎው ህግ ግን በ1804 በወጣውና በጊዜው ዘመናዊ በነበረው በኮድ ናፖሊዮን የፊውዳል ህግ መቀየሩ አልቀረም። የኮድ ናፖሊዮን ህግ አንቀፅ 12 በፊት የነበረውን ህግ፥ ማለትም ፈረንሳዊ ያገባች የውጭ አገር ሴት የባሏን ዜግነት ማግኘቷን ሳይቀይር፥ በአንቀፅ 19 ላይ የውጭ ዜጋ ያገባች ፈረንሳዊት የባሏን ዜግነት እንደምታገኝ ደንግጓል። ይህ ድንጋጌ ከፊውዳሉ ህግ መርህ ጋር ሲወዳደር አንድ እርምጃ ወደፊት የተራመደ ነበር፤ ምክንያቱም በኮመን ሎው ህግ መሠረት አንዲት የውጭ ዜጋ ያገባች ሴት ለአገርዋ መንግሥት ያላትን ታማኝነት፥ የባሏን ዜግነት በማግኘቷ መቀየር አትችልም ነበር፤[14]

ይህ እንግዲህ በፈረንሳይ አብዮት መንፈስ ለሴቶች በከፊል ነፃነትን ያጎናፀፈ ነበር። ኮድ ናፖሊዮን በአውሮፓ አህጉር የዜግነት ህጎች ዕድገት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያስገኘ ነበር። ለምሳሌም በ1844 የብሪታንያ ፓርላማ አንድ ህግ አወጣ፤ በዚህም ህግ መሠረት አንዲት የብሪታኒያ ዜጋ ያገባች የውጭ አገር ሴት የብሪታንያን ዜግነት እንድታገኝ ፈቀደ። ይህ ከኮመን ሎው መርሆዎች ያላቀቀ የመጀመሪያ እርምጃ ነበር። የብሪታኒያ የዜግነት ህግ በበለጠ ምሉዕ የሆነው በ1870 ፓርላማው ሌላ ህግ

ሲያወጣ ነበር፤ ይህም ህግ ማንኛውም ያገባች ሴት ከባሏ ጋር በተጋቡበት ወቅት፣ ባሏ የያዘውን ዜግነት እንደያዘች እንድትቆጠር ደነገገ።[15]

እንደገናም በ1889 ዓ.ም. የፈረንሳይ ህግ ያገቡ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ ሌላ አዲስ መርህ አመነጨ፤ ይኸውም የኮድ ናፖሊዮንን አንቀፅ 12 በመቀየርና ተጨማሪ አንቀፅ በማያያዝ፣ የፈረንሳይ ሴት ጋብቻው የባሏን ዜግነት ካልሰጣት በስተቀር በጋብቻ ምክንያት ዜግነቷን እንደማታጣ ደነገገ።[16]

በኮድ ናፖሊዮን ላይ ያገቡ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ የተደነገጉት መርሆዎች ቀስ በቀስ በተለምዶ "የሰለጠነው አለም" በሚባሉት አገሮች ላይ ለውጥ አስከተሉ። የዚህ ህግ ተፅእኖ በተለይም ከአንደኛው የአለም ጦርነት ማብቂያ በኋላ በእጅጉ እደገ። ወደ 1930 ዓ.ም. ገደማ 15 የሚሆኑ የአውሮፓ አገሮች የዜግነት ህጎች የውጭ አገር ሴት የባሏን ዜግነት የምታገኝበትን ህግጋት ደነገጉ። አንዳንዶቹ የላቲን አሜሪካ አገሮችና አምስቱም የስካንዲኒቪያ አገሮች ተመሳሳይ ህጎችን አወጡ።[17]

- ሐ -

ከላይ እንደተገለፀው ዜግነት የተግባርና የፍላጎት ውጤት ነው፤ በመሆኑም አንድ ሰው በአንድ አገር ውስጥ እየኖረ የሌላ አገር ዜጋ ሊሆን ይችላል።[18] ይህ የሚያመለክተው፣ አንድ ሰው በተግባር እና በፍላጎቱ ካልሆነ በስተቀር ዜግነት ሊያገኝ ወይም ሊያጣ እንደማይችል ነው። ይህ አባባል ትክክል የሚሆነው ዜግነት የማግኘትም ሆነ የማጣት ጉዳዮች ከተገቢው ዜግነት የማግኛ ወይም ዜግነት የማጣ ህጋዊ ሥነ ሥርዓቶች ሲያያዙ ነው። ባገቡ ሴቶች ዜግነት ማግኘት ወይም ማጣት ጉዳይ ላይ ግን ይህ አባባል ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህና ከ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በፊት እንደ ትክክለኛ አባባል አይታይም ነበር። እስከ አሁንም ድረስ ቢሆን ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ አገሮች የህግ ሥርዓት ውስጥ እንደ ትክክለኛ አባባል አይቆጠርም።

በሌሎች አገሮች የዜግነት ሕጎች ዕድገት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳደሩት የኮድ ናፖሊዮን አንቀፅ 12 እና 19፣ የ1844ቱና የ1870ው የብሪታንያ ፓርላማ ህጎች፣ በ1855 እና በ1907 በአሜሪካን ኮንግሬስ የወጡት ህጎች፣ ሁሉ የተመሠረቱት ለመንግሥት ታማኝነትን በሚጠይቀው የፊውዳላዊ ጽንስ ሃሳብ ላይ ነው። በዚህም ምክንያት ለመንግሥት ያልተከፋፈለ የቤተሰብ ታማኝነትን ለማስገኘት ተብሎ፣ የቤተሰብ አንድነትን ለማምጣት በሚል ሽፋን፣ ከአገባቸው ሴት ነፃነት ይበልጥ የመንግሥት ጥቅም ቅድሚያ ተሰጥቶት ይታያል። ስለዚህም ጋብቻ በመፈፀሟ ምክንያት ብቻ ሚስት የባሏን አገር ዜግነት እንደያዘች ይቆጠር ነበር። የሴትዮዋ ፈቃደኝነት ዓይን ባወጣ መንገድ ተንቋል፤ አንዳንዴም እሷን በቀጥታ በሚመለከት ጉዳይ ላይ ፈቃደኛ ነች ተብሎ ሲገመት ቆይቷል።

ከ1922 በፊት በአሜሪካን አገር አሜሪካዊ ያገባች የውጭ አገር ሴት ፈቃደኝነቷ ሳይጠየቅ አሜሪካዊት ትሆን ነበር። በ1922 ጋብቻን አስመልክቶ በአንዲት አሜሪካዊ ባገባች ሴትና በባሏ መካከል በተደረገ ሙግት /በብራደርና በዙብሪክ መካከል/፣ የአሜሪካ ፍ/ቤት የውጭ አገርዋ ሴት በዚያ ጋብቻ[19] ምክንያት የአሜሪካ ዜግነት አግኝታለች ብሎ ፈርዷል /አፅንኦት የተጨመረ/። ከ1922 በፊት በኬሊና በኦወን ጉዳይ ተግባራዊ የሆነው ደንብ ሲሠራበት የቆየ ሲሆን፣ ይኸውም ከአንድ አሜሪካዊ ዜጋ ጋር የነበረ የጋብቻ ሁኔታ ዜግነትን ለማግኘት በቂ ነው የሚል ነበር።[20] በአጠቃላይ ሌላ ተቃዋሚ ህግ እስካልነበር ድረስ በጋብቻቸው ዘመን ሁሉ የሚስት ዜግነት የባሏ ዜግነት ነበር።[21]

አንዳንድ ጊዜም ሴትዮዋ ዜግነቷን የመተው ፈቃደኝነቷ ጋብቻውን በመፈፀሟ ይገመታል ተብሎ ተወስንዋል። በማኬንዚ እና በሄር መካከል በተደረገ ክርክር የአሜሪካ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጋብቻ በመፈፀሙ ምክንያት ጋብቻው የሚያመጣው ህጋዊ ውጤት ታውቋል በሚል ግምት የአሜሪካን ዜግነት የመተው ፈቃደኝነት አለ ብሎ በይንዋል።[22]

የውጭ አገር ሴቶች የባሎቻቸውን ዜግነት የማግኘት ፈቃደኝነታቸው ከጋብቻው መፈፀም ሊገመት ይችላል የሚል ተመሳሳይ ክርክርም ሊቀርብ ይችላል። በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ አመለካከት ግን ለጋብቻ ፈቃደኛ መሆን ማለት ዜግነት የማግኘትም ሆነ የመተው ፈቃደኝነትን ያመለክታል ብሎ ለማሰብ ያስቸግራል። ጋብቻ መፈፀም በራሱ ህጋዊ ውጤትን የሚያመጣ ህጋዊ ተግባር ነው። ዜግነትን የማግኘትም ሆነ የማጣት ተግባርም እንደዚሁ ፍፁም የተለየ እና ነፃ ህጋዊ ተግባር ሆኖ የተለያዩ ህጋዊ ውጤቶችንም ያስከትላል።

አንድ ሰው የጋብቻን ህጋዊ ውጤቶች ለመቀበል ፍቃደኝነቱን ሰጥቶ፣ በሌላ በኩል ግን አዲስ ዜግነት በማግኘት ወይም የነበረውን ዜግነት በማጣት የሚመጡትን ህጋዊ ውጤቶች ለመቀበል ፍቃደኝነቱን ላይሰጥ ይችላል። በጋብቻ መፈፀም ምክንያት ዜግነት የማግኘት ወይም የማጣት ፍቃደኝነት አለ ብሎ መገመት ግን የሚያሳየው ነገር ቢኖር በመሠረቱ ፍትሃዊ ባልሆነ ሥርዓት ላይ የተመሠረተውንና ጊዜው ያለፈበትን የታማኝነት ፅንሰ ሃሳብ ለመቀጠል የሚደረግ ጥረት መሆኑን ነው።

አድሎአዊና ፍትሃዊ ያልሆነ ህግ ተቀባይነት እንዲኖረው መሞከር የሚያመጣው ችግር ከፍ/ቤቱ የብይን ምክንያቶች ሊታይ ይችላል።

ከላይ በጠቀስነው በማኬንዚና በጄር ክርክር የውጭ አገር ዜጎችን ያገቡ አሜሪካውያን ሴቶች ዜግነታቸውን እንዲያጡ የደነገገውን ህግ አድሎአዊና ፍትሃዊ ያልሆነ ነው ተብሎ ለቀረበው ክርክር ፍርድ ቤቱ ሲመልስ፤ በጋብቻው ወቅት በሌሎች አገሮች ይታወቅ በነበረው የጋብቻ አንድነት ፅንሰ ሃሳብ መሠረት ሚስትየዋ ወዲያውኑ የባሏን ዜግነት ካልያዘች፣ አሜሪካውያን ሴቶች ያለፈቃዳቸው ዜግነታቸውን እንዲተው የሚያደርገው ህግ፣ አንድ ወጥ ዜግነት እንዲኖር ከሚጥረው ፖለቲካዊ አስተሳሰብ አኳያ ፍትሃዊ ነው ብሏል።[23] በዚያን ጊዜ ይህን አንድ ወጥ ዜግነትን የሚያቀነቅነውን ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ለማሳካት ተብሎ፣ አንዲት ያገባች ሴት ዜግነቷን የመምረጥ ነፃነቷ ቢረገጥ ለውጥ አያመጣም ነበር።

ከዚህ አቅጣጫ ሲታይ እንዲት የውጭ አገር ዜጋ በጋብቻ ምክንያት የባሏን ዜግነት መያዟን እንደ አንድ የሌላ አገር ዜግነት ማግኛ መንገድ /ናችራላይዜሽን/ መቀበል አሳሳች ይሆናል። ምክንያቱም ከመወለድ ውጭ የሚገኝ ዜግነትን ለማግኘት ዜግነቱን የሚያገኘው ሰው ተግባርና ፍላጎት ከህጋዊ ሥነ ሥርዓቱ በፊት እንዲኖር ይጠበቃል፤[25] ይህ ደግሞ የሌላን አገር ሰው ያገባች የውጭ አገር ሴት ዜግነቷን ያገኘችበትን መንገድ ሊገልፅ አይችልም። ምክንያቱም የሌላን አገር ሰው ያገባችው የውጭ አገር ሴት ጉዳይ ላይ የጋብቻው ውጤት ወዲያውኑ የመጣ ነው፤ የባሏን ዜግነት እንድታገኝም ሆነ የራሷን ዜግነት እንድታጣ የሴትዮዋ ተግባርም ሆነ ፍላጎት አስፈላጊ አይደለምና። ከ1922 በፊት በአንዳንድ አገሮችና ከዚያም በኋላ እስከ ብዙ ጊዜ በብዙ አገሮች የነበሩት ያገቡ ሴቶችን የሚመለከቱ የዜግነት ህጎች ዋነኛ አላማ አንድ ወጥ ዜግነትን የሚያተነትነውን ፖለቲካዊ አስተሳሰብ አራምዶ፣ አንድ ወጥ ታማኝነትን ለመጠበቅ እንደነበር ሊታወስ ይገባል።[26] ይህ የፖለቲካ ግብ የተሳካው ያገባችው ሴት ፈቃዷን የመግለፅ ተፈጥራዊ መብቷን፣ የባሏን ዜግነት በምትይዝበት የራሷን ዜግነት በምታጣበት ጊዜ እንዳትጠቀምበት በመናቅ ነበር።

በዚህ ረገድ በአውሮፓ አህጉር የነበረው ልምድም ከአሜሪካኑ ልምድ አይለይም ነበር። በአውሮፓ ውስጥም ቢሆን የጋብቻ መፈፀም በራሱ የሚስትን የዜግነት ማጣት ያስከትል ነበር። ከአንደኛው የአለም ጦርነት በኋላ ወደ 15 የሚሆኑ የአውሮፓ አገሮች ያወጧቸው የዜግነት ህጎች፣ የአገሮቻቸውን ዜጎች ያገቡ የውጭ አገር ሴቶች ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የባሎቻቸውን ዜግነት እንደሚይዙ ደንግገው ነበር።[27]

በአምስቱም የስካንዲኒቪያ አገሮች የውጭ አገር ሴቶች ወዲያውኑ የባሎቻቸውን ዜግነት ይይዙ ነበር። በጀርመንና በጣሊያንም፣ የውጭ አገር ሴቶች ከአገሩ ዜጋ ጋራ ስትጋባ፣ የባሏን ዜግነት ወዲያውኑ እንደምትይዝ ተደንግጓል።

ነገሮች በዚህ ሁኔታ በመቀጠላቸውና ጋብቻ ወዲያውኑ የዜግነት ለውጥ መፍጠሩ በሰፊው የተለመደና በብዙ የአለም አገሮችም ጠንካራ በሆነ መንገድ ስለሚሠራበት በ1923 ዓ.ም. በስቶክሆልም በተደረገው አለም አቀፍ የህግ ኮንፈረንስ

ላይ ፕሬዚዳንት ሃማርስኪልድ "በአሁኑ ሁኔታዎች፣ ጋብቻ ወዲያውኑ በሚስት ዜግነት ላይ የሚፈጥረውን ውጤት ለማስቀረት የሚታሰብ ማኛኛያ፣ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነቱ ዝቅተኛ ይሆናል"[28] ብለዋል። እንዲሁም አንዳንድ የአለም አቀፍ ህግ ባለሙያዎች አንድ ደረጃ በመራመድ፣ የአገባች ሴት ዜግነት የባሏ ዜግነት መሆኑ የአለም አቀፍ ህግ መርህ ነው ብለውም ጠቀመዋል።

- መ -

ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ የሴቶች ድርጅቶች ላደረጉት ጥረትና ታዋቂ የሆኑ የዓለም አቀፍ ህግ አዋቂዎች ላቀረቧቸው ሀሳቦች ምስጋና ይግባቸውና ያገቡ ሴቶችን ዜግነት የሚመለከተው ህግ የተለያዩ መንግሥታትን ህግ አውጪ አካላት ትኩረት መሳቡን ቀጥሏል፤ ይህም በተለይ አንደኛው የዓለም ጦርነት ከአበቃ ኋላ የበለጠ ተጠናክርዋል። ይህ የህግ አውጪዎች ትኩረትም የተገፋፋው በጦርነቱ ወቅት ዜግነት የሌላቸውን ሴቶችና ባሎቻቸውን ባጋጠሟቸው ችግሮች መሆኑ አያጠራጥርም።

በዚህ ረገድ ህግ የማውጣት ርምጃ የወሰደችው የመጀመሪያዋ ሀገር የሩሲያ መንግሥት ነበረች። ጋብቻ በራሱ ብቻ በሚስት ዜግነት ላይ ተፅዕኖ እንደማይኖረው የሚያደርግ ህግ በ1918 አውጥታለች።[30] ሆኖም ግን አንድ ዜግነት የሌላት ሴት አንድ ዜጋ ብታገባና የራሷን ዜግነትም ትታ የባሏን ዜግነት ለማግኘት ብትፈልግ ልታገኝ የምትችልበትን የሥነ ሥርዓት ሁኔታ በብቃት የማያስቀምጥ ህግ የተሟላ ሊሆን አይችልም።

ስለዚህ የአገቡ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ የህግ ማውጣት ሥራን በእርግጥ ያንቀሳቀሰው በአሜሪካ ኮንግረስ የፀደቀው የ1922ቱ ህግ ነበር። በዚህ /ኬብል አክት በመባል በሚታወቀው/ ህግ ውስጥ:-

ሀ/ እንዲት የአሜሪካ ዜግነት የሌላት ሴት ከአንድ የአሜሪካዊ ዜጋ ጋር በመጋባቷ ብቻ የአሜሪካን ዜግነት ወዲያውኑ አታገኝም ነበር፣ ዜግነት ልታገኝ የምትችለው ራሱን በቻለ የዜግነት ማግኛ ሂደት /በናችራላይዜሽን/ ብቻ ነበር፤ እንዲሁም

ለ/ የአንዲት አሜሪካዊት ሴት ከአንድ አሜሪካዊ ካልሆነ ወንድ ጋር መጋባቷ ብቻውን ዜግነቷን መተዋን ካልገለፀች በስተቀር የአሜሪካ ዜግነቷን አያሳጣትም[31] የሚሉ አንቀጾች ነበሩበት።

ይህ "ኬብል አክት" በመባል የሚታወቀው ህግም ቀስ በቀስ በብዙ መንግሥታት ሕጎች ላይ ተፅዕኖ አድርጎ ነበር። ቤልጅግ /1922/፣ ሩማንያ /1924/፣ ፈረንሳይ /1927/፣ ኖርዌ፣ ስዊድን፣ ዴንማርክ፣ አይስላንድና ፊንላንድ /1924-27/ የአንድ ሴት ዜግነት በባሏ ዜግነት ይወሰናል የሚለውን መርህ በተለያየ ደረጃ የቀየሩ አዳዲስ ሕጎችን አውጥተዋል።[32]

በተጨማሪም ያገቡ ሴቶችን የዜግነት ጥያቄ በተመለከተ ለሚወጡ ብሄራዊ ህጎች መሪ ሊሆኑ የሚችሉ ፅንሰ ሃሳቦችን በማዳበሩ በኩል ዓለም አቀፍ አካላት በንቃት ይሳተፉ የነበሩትም በዚሁ ወቅት አካባቢ ነበር። የአለም አቀፍ ህግ ማህበር በ1922ቱ ኮንፈረንስ በርሱ እምነት ያገባች ሴትን ዜግነት በስምምነት መወሰን እንደሚያስፈልግ፣ ሆኖም እስከተቻለ ድረስ የራሷን ዜግነት የመምረጡን መብት ለራሷ መጠበቅ እንደሚገባ ገልጿል።[33] በነዚያ የአስተሳሰብ መሥመሮች አኳያ የተዘጋጀው ሞዴል ህግም በተከታዩ ዓመት፣ በ1923፣ በስቶክሆልሙ የማሕበሩ ኮንፈረንስ ፀድቋል።

በ1926 የተካሄደው የጋራ ብልፅግና ኮንፈረንስም እንደዚሁ፣ ጋብቻ፣ በሚያገቡት ሴቶች ዜግነት ላይ የሚያስከትለው ውጤት ያሳሰበው መሆኑን ገልጿል።[34]

በመጨረሻም በመንግሥታቱ ሊግ የተቋቋመው የዓለም አቀፍ ህግ አሻሻይ የኤክስፐርቶች ኮሚቴ ያገቡ ሴቶችንም የሚያጠቃልል የዜግነት ህግ መውጣት ያለበት መሆኑን አምኖበታል።

እነዚህ የተለያዩ ጥረቶችም በ1930 ህግ ላይ የፀደቀውን "ከዜግነት ህጎች አለመጣጣም ጋር በተያያዙ የተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ የተደረገ ስምምነት" አፍርተዋል።

ሆኖም ግን ይህ ስምምነት ያገባች ሴት የራሷን ዜግነት አራሷ የመምረጥ መብቷን እስከ ማስመለስ ደረጃ ድረስ አልሄደም። የስምምነቱ አንቀፅ 8:-

"የሚስትየዋ አገር ዜግነት ህግ ከአንድ የውጪ ዜጋ ጋራ በመጋባቷ ምክንያት ዜግነቷን የሚያሳጣት ከሆነ ይህ ተግባራዊ የሚሆነው የባሏን ዜግነት ካገኘች ብቻ ነው" [35] ይላል።

ስምምነቱ በመጀመሪያው አንቀጽ፣ አንድ መንግሥት እነማን ዜጎቹ እንደሚሆኑ በራሱ ህግ የመወሰን መብት ያለው መሆኑን የሚገልፀውን ደንብ እንደገና አረጋግጧል። ይህም ደንብ አንዱ ከፀደቀ ከኋላ ጋብቻ ወዲያውኑ የሚፈጥረው ውጤት በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲታወቅ መደረጉ የግድ ነበር። አንቀፅ 8፣ 9 እና 11ም በዚህ ዕውቅና ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ስለዚህ፣ በዚህ ረገድ ስምምነቱ በአንቀፅ 1 ከተገለፀው ደንብ መከተላቸው አይቀሬ የሆኑትን የጥንድ ዜግነትንና ሙሉ በሙሉ ዜግነት የማጣትን ችግሮች በመቆጣጠሩ ላይ ራሱን ገድቧል። በመሆኑም ያገቡ ሴቶች የዜግነት ጥያቄ በራሱ እንደጥያቄ አልታየም ነበር፤ ስምምነቱ ባገቡ ሴቶች የዜግነት ህግ ላይ ያተኮረው ሀቅ ጥንድ ዜግነትንና ሙሉ በሙሉ ዜግነት ማጣትን እስካስከተለ ድረስ ብቻ ነበር።

በእርግጥ አጠቃላይ የመንግሥታት ተግባርና ዓለም አቀፍ ስምምነታዊ ህግ "ሚስት በባሏ ሥር በምትቆይበት ጊዜ ውስጥ የእሷ ዜግነት የባሏን ዜግነት ይከተላል" በሚለው ልማዳዊ መርህ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ የ1930ው ስምምነት ተሳታተፊዎች የሴቶችን መብቶች ዕውቅና ለማሻሻልም ሆነ በዜግነት ጉዳዮች ባልና ሚስት ዕኩል መብት እንዲኖራቸው ለማድረግ አልፈለጉም ነበር።[36] ስለዚህ ኮንፈረንሱ ለብሄራዊ ህግ አወጣጥ ሊረዳ የሚችል ሃሳብ አባሪ ማድረጉን አስፈላጊ አድርጎ ወስዶታል። በኮንፈረንሱ የፀደቀው አራተኛው ሃሳብም:-

1/ "መንግሥታት የሌጆችን ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት በዜግነት ጉዳዮች የፆታ እኩልነትን በሕጋቸው ውስጥ ለማስገባትና፣ በተለይም

2/ በመርህ ደረጃ የሚሰጥ ዜግነት ያለፈቃዷ ፈቃድ በጋብቻም ሆነ በባሏ የዜግነት መለወጥ ምክንያት ሊለወጥ እንደማይችል ለመወሰን፣ ይቻላል ወይም አይቻልም የሚለውን ጥያቄ እንዲያጠኑ ኮንፈረንሱ ሃሳቡን ይሰጣል"[37] ይላል።

ስምምነቱ የፀደቀው በጣም ዘግየቶ /በመንግሥታቱ ሊግ ዋና ፀሐፊ ቢሮ የተመዘገበው ጁላይ 1/1937/ እና በጣም በጥቂት አገሮች/ ስምምነቱን ከፈረሙት ከ32ቱ በ11 ብቻ/ ነበር። ይህ ቢሆንም ቅሉ ስምምነቱ እራሱና በተለይም ከስምምነቱ ጋር አባሪ የሆነው ሃሳብ 4/ Recommendation IV/ ከዚያ በኋላ በወጡ የመንግሥታት ሕጎች ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ ይመስላሉ። ስለዚህ በአገር ውስጥ የተወለደችና የውጪ ሰው ያገባች ሴትን በተመለከተ ጥቂት መንግሥታት ዜግነቷን መተዋን በወቅ እስካልገለፀች ድረስ የመጀመሪያውን ዜግነቷን እንደያዘች ለመቆየት እንደምትችል ለማድረግ ፈቃደኝነታቸውን አሳይተዋል። ሆኖም ግን በጣም ከጥቂቶቹ በስተቀር፣ በተግባር ሁሉም መንግሥታት ማለት ይቻላል፣ ከዜጋቸው ጋር ለተጋባች የውጪ ሴት ለራሳቸው ዜጋ የሰጡትን ያህል መብት ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም።"[38]

በዚህ መሠረት ከዜጎች ጋር የሚጋቡ የውጪ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ እጂ ፈቀደችም አልፈቀደችም ያገባች ሴት ዜግነት የባሏን ዜግነት ይከተላል የሚለው ጥንታዊ ደንብ መተግበሩ ቀጠለ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የተለያዩ የሴቶች ድርጅቶች፣ የዓለም አቀፍ ህግ ሊቃውንት፣ እንዲሁም አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ አካላት ያገቡ ሴቶችን የጾታ እኩልነት የሚያረጋግጡ የዜግነት ህግ መርሆዎች እንዲወጡ ለማድረግ ጥረታቸውን ቀጠሉበት።

የ1933ቱ የሞንቴ ቪዲዮ የሴቶች ዜግነት ስምምነት፣ ዜግነትን በተመለከተ ለጾታዎች እኩልነት ዕውቅና የሰጠ የመጀመሪያው በብዙ ሐገሮች መሐከል የተደረገ ስምምነት እንደመሆኑ እዚህ ላይ በተለይ መታየት ይገባዋል።[39] የስምምነቱ አንቀፅ 1 ተዋዋይ አገሮች "ዜግነትን አስመልክቶ በሕጎቻቸውም ሆነ በተግባር ምንም ዓይነት በጾታ ላይ የተመሠረተ ልዩነት አይኖርም፤"[40] የሚለውን አባባል እንዲቀበሉ ያስገድዳቸዋል። በ1945 በተካሄደው በሳንፍራንሲስኮ የዓለም አቀፍ ድርጅት ኮንፈረንስ የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር መውጣት ባገሩ ሴቶች የዜግነት ህግ አዝጋሚ ለውጥ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድርዋል። የቻርተሩ የመጀመሪያው ቁጥር 3ኛው አንቀፅ ሰብዓዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶችን ለሁሉም የሰው ልጅ ያለምንም የጾታ፣ የዘር፣ ወይም የሃይማኖት ልዩነት ለማዳበርና በትክክል እንዲከበሩ ለማበረታታት ዓለም አቀፍ ትብብርን መፍጠር ከተባበሩት መንግሥታት ዓላማዎች አንዱ እንደሆነ ይገልፃል።[41] የቻርተሩን አንቀጽ 55፣ 56፣ 62፣ 68 እና 76 በተጨማሪ ይመለከቷል።

በ1984 ዓ.ም. ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ ወጣ። የዚህ ድንጋጌ አንቀጽ 15 እና 16 ከብዙ ሌሎች ጉዳዮች መካከል ማንኛውም ሰው የዜግነት መብት እንዳለው፣ ማንም ዜግነቱን በዘፈቀደ እንደማይነጠቅና ዜግነቱን የመለወጥ መብቱም እንደማይነፈገው፣ ወንዶችና ሴቶች ጋብቻ ሲፈፀም በጋብቻ ጊዜና ጋብቻው ሲፈርስ እኩል መብት እንዳላቸው ይገልፃሉ።[42]

በዚህ መካከል በሴቶች ድርጅቶችና ሌሎች ቡድኖች ጫና የሴቶች ከብር ጉዳይ ኮሚሽን የሚባልና በወንዶችና በሴቶች መሐከል እኩልነትን ማስገኘት ዋና ተግባሩ የሆነ አካል በተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚና ማሀበራዊ ምክር ቤት ተቋቋመ። የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ምክር ቤቱ የመጀመሪያ ሃሳብ ለዓለም አቀፍ ህግ ኮሚሽን የስምምነቱን ረቂቅ የማዘጋጀቱን ኃላፊነት ለመስጠት የነበረ ቢሆንም የሚወስደው ጊዜ ግን ያገቡ ሴቶች የነበሩበት ሁኔታ ሊፈቅድ ከሚችለው ጊዜ አንፃር ሲታይ በጣም እንደሚረዝም ታመነበት። በዚያ ሁኔታ ይህን ረቂቅ ስምምነት የማዘጋጀቱ ሥራ ለሴቶች ክብር ጉዳይ ኮሚሽን ተሰጠው።[43] ከአሥር ዓመታት አካባቢ ጥናትና ውይይት

በኋላም ኮሚሽኑ ያገቡ ሴቶች ስምምነትን ረቂቅ ይዞ ቀረበ። ረቂቅ ስምምነቱም በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ፀድቆ በጃንዋሪ 28/1957 ለአባል አገሮች ፊርማ ክፍት ተደረገ።[44] ኦገስት 11 ቀን 1958 ዓ.ም. በሥራ ላይ ዋለ።

ይህ የ1957ቱ ያገቡ ሴቶች የዜግነት ስምምነት፣ ያገቡ ሴቶች ዜግነት ሴቶች እንደ ግለሰብ ካላቸው ክብርና ነፃነት ጋር የሚያያዝ ጥያቄ በመሆኑ ዕውቅና በመስጠት ላይ የተመሠረተ ነው። በመሆኑም ስምምነቱ የጥያቄው ዋና ክፍል የሆነውን ጋብቻ በአገባች ሴት ዜግነት ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ በቀጥታ ይመለከታል።

የስምምነቱ ቁጥር 1:-
"ማንኛውም የዚህ ውል ተዋዋይ መንግሥት ከዜጎቹ አንዱ ከውጪ አገር ሰው ጋር ጋብቻ ቢፈፅም ወይም የፈፀመው ጋብቻ ቢፈርስ ወይም ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ባልየው ዜግነቱን ቢለውጥ የሚስትየዋን ዜግነት ወዲያውኑ አያውከውም በማለት ተስማምቷል" የሚለውን ጠቃሚ አንቀፅ ይዟል /አፅንኦት የተጨመረ/

በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የተሰበሰበው የዓለም ማሕበረሰብ በዚህ ስምምነት ላይ አንድ ዓይነት አቋም በመያዝ ያገባች ሴት የራሷን ዜግነት ራሷ የመምረጥ መብቷን አውቆላታል። ስምምነቱም ለተሳሚዎቹ መቶ ዓመታት የተደረጉት የሴቶች ድርጅቶችና የዓለም አቀፍ ህግ ሊቃውንት ትግል በድል የመደምደሙ ዋና ምልክት ነው። ስምምነቱ ለፍትሕ በአሸናፊነት መውጣትም ዋና ምልክት ነው በማለት በተጨማሪ መናገር ይቻላል።

ሆኖም ግን ያገቡ ሴቶች የዜግነት ጥያቄ እስከአሁን ድረስም በጥያቄነት በመነሳት ላይ ነው። በ1979 አካባቢ ስምምነቱን ያፀደቁት ተዋዋይ መንግሥታትም ሆኑ ተዋዋይ ያልነበሩ ሆነው ስምምነቱ ውስጥ የገቡት መንግሥታት በጣም ጥቂት ናቸው።[45] ከነዚሁም እንኳን ስምምነቱን ለመተግበር የሚያስችል ብሄራዊ ህግ ያወጡት መንግሥታት ቁጥር ብዙ አይመስልም።

ስምምነቱ በሥራ ላይ ከዋለ ከአምስት ዓመታት በኋላ በተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ በ1963 የቀረበው ሪፖርት ይህን ጉዳይ ግልፅ ያደርገዋል።[46] በሪፖርቱ መሠረት የመንግሥታት የሕግ ሥርዓቶች በሦስት ዋና ዋና ምድቦች ይመደባሉ።

ሀ/ የመጀመሪያው ምድብ የሚስት ዜግነት የባሏን ዜግነት ወዲያውኑ የሚከተልበትን የህግ ሥርዓቶች ያካትታል። ማለትም ጋብቻ እራሱ፣ የጋብቻ መፍረስ እና ጋብቻው ፀንቶ በአለበት ጊዜ ባልየው ዜግነቱን ሲለውጥ በሚስት ዜግነት ላይ ቀጥተኛ የሆነ ውጤት ያስከትላል። የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ በዚሁ ሥር እንደሚገባ በሪፖርቱ[47] ተመልክቷል። ኢትዮጵያን፣ ጣሊያንን፣ አውስትሪያን፣ ግሪክን፣ ኔዘርላንድን፣ ስዊዘርላንድን፣ ፖርቹጋልንና ቱርክን ጨምሮ ወደ ሃያ ሰባት መንግሥታት በዚህ ምድብ ሥር ይወድቃሉ።

ለ/ ሁለተኛው ምድብ ደግሞ ጋብቻ የአንዲትን ባዕድ ሚስት ዜግነት ወዲያውኑ የሚነካበትን ሁኔታ የሚከተሉ የህግ ሥርዓቶችን ያጠቃልላል። ሆኖም ግን ሙሉ በሙሉ ዜግነት ማጣትንና ጥንድ ዜግነትን ለማስወገድ በማሰብ የቤተሰብ አህጻዊነት መርህን ከባልየው መንግሥት የህግ አንቀጾች ጋር እንዲስማማ በማድረግ በመጠኑ ለውጥ ተደርጎበታል። ቻይናን፣ ቤልጅግን፣ ቱኒዝያን፣ ቦሊቪያንና ካሜሩንን ጨምሮ ወደ 13 መንግሥታት በዚህ ምድብ ሥር ይወድቃሉ።

ሐ/ የመጨረሻው ምድብ ደግሞ ጋብቻ በአንዲት የውጪ አገር ሚስት ዜግነት ላይ፣ ካለእራሷ ፍቃድ፣ ምንም ተፅዕኖ እንደሌለው የሚደነግጉ የህግ ሥርዓቶችን ያካትታል። ከነዚህም ውስጥ በግምት 24ቱ መንግሥታት ባዕዷ ሚስት የባሏን ዜግነት የማግኘት መብት እንዳላት ብቻ ዕውቅና ይሰጣሉ፤ ወደ 24 መንግሥታት ዜግነት ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ጉዳዮች ቀላል አድርገው ሲያቀርቡ ሌሎች ወደ 12 የሚሆኑ መንግሥታት ደግሞ ጋብቻ በባዕዷ ሚስት ዜግነት ላይ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ እንዳለው ዕውቅና አይሰጡም።[48]

የአንዲት ዜጋ የሆነች ሴት ከውጪ ባል ጋር መጋባትን በተመለከተ ያለው ሁኔታ ግን በጣም የተለየ ቅርፅ የያዘ ነው።[49] ስድስት መንግሥታት ባዕድ ባል ያገባችን ሴት ዜጋ ወዲያውኑ ዜግነቷን ያሳጧታል፤ የኢትዮጵያ የዜግነት ህግም፥ እንደሪፖርቱ አባባል፥ የሚጠቃለለው በዚሁ ምድብ ሥር ነው። ሆኖም ግን አንዲት ኢትዮጵያዊት የኢትዮጵያዊነት ዜግነቷን የምታጣው የባሏን ዜግነት ከአገኘች ብቻ ነው። ወደ አሥራ ሰባት መንግሥታት ደግሞ የውጪ አገር ወንድ ያገባች ሴት ዜጋ የባሏን ዜግነት ማግኘት ወዲያውኑ ዜግነቷን የሚያሳጣ ህግ አላቸው። ወደ ሰባ መንግሥታት ግን ሴቶች ዜጎቻቸው የውጪ አገር ወንዶችን ቢያገቡም ዜግነታቸውን ይዘው የመቆየት መብታቸውን ይጠብቁላቸዋል።

ከዚህ እንደሚታየው፥ ምንም እንኳን የ1957ቱ ስምምነት ራሱን የቻለ ድል ቢሆንም የስምምነቱ ቅርፅና ይዘት በሁሉም መንግሥታት ዘንድ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊነትን እንዲያገኝ ብዙ መደረግ ያለበት ነገር አለ።

- ሠ -

ጋብቻ ባገባች ሴት ዜግነት ላይ ከሚኖሩት ተፅዕኖዎች ውስጥ አንዱ በውጼታም ይሁን በግጼታ ሴትዮዋ ጥንድም ብቻ ሳይሆን ብዙ ዜግነት የማግኘት ዕድሏን መጪመሩ ነው። አብዛኛውን ጊዜ መንግሥታት ዜጎቻቸው እነማን እንደሆኑ ለመወሰን በሚከተሏቸው የተለያዩ መርሆች መካከል ግጭት ሲፈጠር ጥንድ ዜግነት ለማንኛውም ሰው ይከሰታል። ስለዚህ አንድ አሜሪካ ውስጥ ከኢትዮጵያውያን ወላጆች የተወለደ ሰው የእንግሊዝን ዜግነት ቢያገኝ ሰውየው ጥንድ ብቻ ሳይሆን ብዙ ዜግነት ይኖረዋል ማለት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያትም ኢትዮጵያ የምትከተለው መርህ ዩስ ሳንግዊኒስ የሚለውን ሲሆን አሜሪካ ግን ዩስ ሶሊ የሚለውን መርህ ስለምትጠቀም ነው። የእንግሊዝ የዜግነት መስጫ ህግም አንድ ሰው የእንግሊዝን ዜግነት ለማግኘት የመጀመሪያ ዜግነቱን እንዲለቅ አይጠይቅም።[50] ስለዚህ አንዲት አሜሪካ ውስጥ የተወለደችና የእንግሊዝን ዜግነት ያገኘች ኢትዮጵያዊት ሴት የጀርመን ዜጋ ብታገባ /የጀርመን ህግ የጀርመን ዜጋ ላገባች የውጪ ሴት የጀርመን ዜግነት ወዲያውኑ

ይሰጣል፣[51]/ ሴትዮዋ የአራት መንግሥታት ዜግነት ባለቤት ሆና ታርፈዋለች ማለት ነው።

ጥንድ ዜግነት የሚፈጠረው ዩስ ሳንጉዊኒስ እና ዩስ ሶሊ የተባሉት መርሆች በሚጋጩበት ሁኔታ መንግሥታት በመጠቀማቸው ምክንያት ብቻ ሳይሆን መንግሥታት ዜጎቻቸው ራሳቸውን ከዜግነት እንዳያገለሉ /ዜግነታቸውን እንዲተው/

ስለማይፈቅዱላቸውና ጥቂት መንግሥታት ደግሞ የራሳቸውን ዜግነት ለውጪ ሰዎች ከመስጠታቸው በፊት ሰዎቹ ከቀድሞ ዜግነታቸው ወይም ተገዢነታቸው መልቀቂያ እንዲያቀርቡ ስለማይጠይቋቸውም ጭምር ነው።[52]

ጋብቻ ባገቡ ሴቶች ዜግነት ላይ ፈጣን ለውጥ የማስከተሉ ሁኔታ የጥንድ ወይም የብዙ አገር ዜግነት የመከሰትን መጠን ይጨምረዋል። በዚህ ጽሁፍ መጀመሪያና ወደ በኋላ ላይ የተጠቀሰው የእቤት ባይዋ ጉዳይ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። እቤት ባይዋ ዜጋ በሆነችበት በሶቭየት ሕብረት የዜግነት ህግ፣ ጋብቻ የሶቭየት ሴትን ዜግነት አይለውጠውም፤[53] የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ግን ከአንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ ለፈፀመች የውጪ አገር ሴት የኢትዮጵያን ዜግነት ይሰጣታል። እዚህ ላይ እንደተመለከተው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ የተመሠረተው የአንዲት የውጪ አገር ዜግነት ያላት ሚስት ዜግነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የባሏን ዜግነት ይከተላል በሚለው ጥንታዊ መርህ ላይ ሲሆን፣ በሶቭየት ህብረት ህግ ግን አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ያገባች የሶቭየት ሴት የግድ ጥንድ ዜግነት ይኖራታል።

አንድ ሰው ያለውን ጥንድ ወይም የብዙ አገር ዜግነት ዜግነታቸውን ከያዘው ከአንዱ መንግሥት ወደ ሌላው በመንቀሳቀስ ህጋዊ ግዴታዎቹን ላለመወጣት፣ ወይም ጥቅሞች ለማግኘት ሊጠቀምበት ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ጥንድ የብዙ አገር ዜግነት ያለው ሰው ግዴታዎቹን ዜጋ በሆነባቸው መንግሥታት የተለያዩ የህግ ሥርዓቶች ውስጥ ሁሉ እንዲወጣ ሊገደድ

ይችላል። የውትድርና አገልግሎት የመስጠትና ግብር የመክፈል ግዴታዎች እንድ ባለጥንድ ወይም የብዙ አገር ዜግነት ያለው ሰው ዜጋቸው በሆነባቸው መንግሥታት ሁሉ እንዲፈፅም በአብዛኛው የሚገደድባቸው ጥና ጥና ምሳሌዎች ናቸው። ይህም የሰውየውን ህይወት ከባድ ሊያደርገው መቻሉ ግልፅ ነው።

ሆኖም ግን ጥንድ ወይም የብዙ አገር ዜግነት ባለው ሰው ላይ የሚያጋጥሙ- ፅውነተኛ ችግሮች የሚከሰቱት እንዲህ ዓይነቱ ሰው በአንድ መንግሥት በደል ሲደርስበት ነው። ይህ ሲፈጠር የተበደለው ሰው እራሱ በደል በደረሰበት መንግሥት ላይ ዓለም አቀፍ አቤቱታ ሊያቀርብ አይችልም፤ ምክንያቱም ግለሰቦች የዓለም አቀፍ ህግ ተገዢዎች /subjects/ ባለመሆናቸው ዓለም አቀፍ ቦታ የላቸውም የሚል አጠቃላይ የሆነ ስምምነት በመኖሩ ነው።[54] የተበደለው ሰው በበደለው መንግሥት ላይ ዓለም አቀፍ አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችለው ዜግነት ከያዘባቸው ከአንዱ ወይም ከሌላው መንግሥት ዲፕሎማሲያዊ ከብካቤ እንዲደረግለት በመጠየቅ ብቻ ነው። ዜግነት በአንድ ሰውና በአንድ መንግሥት መካከል የሚፈጠር፣ የዚያ መንግሥት ሥልጣን ከክልሉ ውጪ እንዲሄድና የመንግሥቱ ህግም በግለሰቡ ላይ እንዲሠራ የሚያደርግ ህጋዊ ግንኙነት እንደመሆኑ ባለጥንድ ወይም የብዙ አገር ዜግነት ያለው ሰው የሥልጣንና የዲፕሎማሲያዊ ከብካቤ ጥያቄ ይህ ሰው ዜጋቸው የሆነውን የሁሉም መንግሥታት ፍላጎት ይነካል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ጥንድ ወይም የብዙ አገር ዜግነት ላለው ሰው የሥልጣንና የዲፕሎማሲያዊ ከብካቤ
የመስጠት ጥያቄ ግጭት ጉዳዩ በሚመለከታቸው መንግሥታት መሐከል መከሰቱ የግድ ነው።

ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ዜግነት ያለው ሰው ዲፕሎማሲያዊ ጥበቃ ይደረግለት ዘንድ በሀገሮች የሚቀርቡ ጥያቄዎች እንዴት ይፈታሉ?

እነዚህ ጥያቄዎች አለም አቀፋዊ ባህሪ ያላቸው እንደመሆኑ መጠን የሚፈቱትም በአለም አቀፍ ልማዳዊ ህግ በአለም አቀፍ ስምምነቶች ነው።

በአሁኑ ወቅት እያንዳንዱ ሀገር የዜጎቹን ማንነት የመወሰን ሥልጣን ያለው መሆኑ ተቀባይነት ያለው የአለም አቀፍ ህግ መርህ ሆኗል። የዚህ መርህ ተቀባይነት በቋሚው አለም አቀፍ ፍርድ ቤት /ፐርማነንት ኮርት ኦፍ ኢንተርናሽናል ጀስቲስ/ እንዲሁም በአሁኑ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት[57] ውሳኔ በተሰጣቸው በርካታ ጉዳዮች ላይ ተረጋግጧል። ይኸው መርህ በ1930ው የሀግ ኮንቬንሽንም ተቀባይነትን አግኝቷል፤ በውስጥ ህጎች አማካይነት የዜጎቹን ማንነት መወሰን የእያንዳንዱ ሀገር ሥልጣን ነው።[58]

አለም አቀፉ ፍርድ ቤት በኖትቦህም ጉዳይ ከደረሰባቸው ግኝቶች በሃሳብ የሚለዩት ሻን ፓንሁይሰና ጆሴፍ ኤል ኩንዝን የመሳሰሉት ጸሐፍት እንኳ እያንዳንዱ ሀገር ላለው የዜጎቹን ማንነት የመወሰን መብት አለም አቀፍ ህግ እውቅና የሚሰጥ በመሆኑ ላይ ይስማማሉ።[59] ስለዚህም፣ አንድ ሀገር በውጪ የሚኖሩ ዜጎቹን በተመለከተ በዜጎቹ ላይ ያለውን የዳኝነት ሥልጣን ወይም ሉአላዊነትን እስከምን ድረስ ሊያሰፋ እንደሚችል በዚያው ሀገር ህግ የሚወሰን ነው።[60]

እንግዲህ እያንዲንዱ ሀገር በአለም አቀፍ ህግ መሠረት በራሱ የውስጥ ህግ እየተመራ የዜጎቹን ማንነት የመወሰን መብት ካለው ሌሎች ሀገሮችም ይህንኑ ውሳኔ የመቀበል ግዴታ አለባቸው ማለት ነው። በእርግጥ ከላይ የተጠቀሰው የሔግ ኮንቬንሽን በአንቀጽ 1 እንደሚያስቀምጠው እያንዳንዱ ሀገር የዜጎቹን ማንነት የሚወስንበት የውስጥ ህግ /የዜግነት ህግ/ "ከአለም አቀፍ ኮንቬንሽኖች፣ ከአለም አቀፍ ልማድ፣ እንደዚሁም ዜግነትን በተመለከተ አጠቃላይ ተቀባይነት ካላቸው የህግ መርሆች ጋር የሚጣጣም እስከሆነ ድረስ በሌሎች ሀገሮች ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት አለበት።"

የዜግነትን ጉዳይ በተመለከተ ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ 1 የአንድ ሀገር የህግ አውጭው አካል የሥልጣን ክልል ከዚህም ጋር የሕጉ አስገዳጅነት በዚያው ሀገር የግዛት ክልል ውስጥ የተወሰነ ነው ከሚለው መርህ ጋር የሚስማማ ነው።

ከዚህ በማያያዝ "ምንም ዓይነት አስም አቀፍ ውል ወይም ሌላ ዓይነት አለምአቀፍ ግዴታ በሌለበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ከኢትዮጵያ ህግ በቀር በሌላ ህግ ለመዳኘት አሻፈረኝ ለማለት ይችላሉ"[62] ቢባል ስህተት አይሆንም።

በሌላ አነጋገር አንድ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ምንጊዜ ከሶቪየት ለሆነ አንድ ግለሰብ በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ መሠረት የኢትዮጵያ ዜግነት ለመስጠት አሻፈረኝ ማለት አይችልም። ለዚህም በኢትዮጵያና በሶቪየት የዜግነት ሕጎች መካከል ያለው ልዩነትና በዚሁም ሳቢያ ግለሰቡ ዜግነት ሊኖረው መቻሉ ለክልከላው እንደምክንያት ሊቆጠር አይችልም።[63] የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ከኢትዮጵያ ህግ ጋር የማይጣጣመውን የሶቪየት ህግ በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ የማዋል ግዴታ የለባቸውም። ስለዚህ ፍርድ ቤቶቹ የሶቪየትን ህግ ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ ግለሰቡ ኢትዮጵያዊ ዜግነት እንዳለው ሊወስኑ ይችላሉ። የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ጣምራ ዜግነትን የማይቀበል በመሆኑ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች አንድን የውጭ ሀገር ዜጋ፥ በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ መሠረት ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ከሆነ እንደውጭ ሀገር ዜጋ ሊመለከቱት አይችሉም።

ከዚህ በላይ የተመለከተው በሄግ ኮንቬንሽን አንቀጽ 3 ሥር የተደነገገው መርህ ነው። ይኸው አንቀጽ "በዚህ ኮንቬንሽን የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዜግነት ያለው ሰው የዜግነት መብቱን ያገኘበት የእያንዳንዱ ሀገር ዜጋ ሆኖ ሊቆጠር ይችላል"[64] ይላል።

አንድ ግለሰብ ጣምራ ዜግነት በሚኖረው ጊዜ ለግለሰቡ የዜግነት መብት በሰጡት ሁለት ሀገሮች መካከል አንዱ ከሌላው ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ለግለሰቡ ዲፕሎማሲያዊ ከለላ /ጥበቃ/ ሊሰጥ አይችልም። ይህ መርህ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት በኖተቦህም ጉዳይ ላይ በሰጠው ውሳኔ ተቀባይነቱ የተረጋገጠ ከመሆኑም ባሻገር በሄግ ኮንቬንሽን አንቀጽ 4 ሥር ተደንግጓል። ስለዚህ "አንድ ሀገር ጣምራ ዜግነት ላለው ግለሰብ፥ ግለሰቡ ሁለተኛ ዜግነቱን ላገኘበት ሀገር ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ዲፕሎማሲያዊ ጥበቃ ሊሰጥ አይችልም።[65]

ሶስተኛ ሀገሮችን በተመለከተ የሀገሮች አሠራር ካንዱ ወደ ሌላው ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ በብሪታኒያ እንግሊዛዊ ዜግነት ያገኘ ሰው ከቀድሞ ዜግነቱ በህጋዊ መንገድ ባልተላቀቀበት ሀገር ከልል ውስጥ ካልሆነ በቀር በሌላው ቦታ ሁሉ በእንግሊዝ ዜግነት ይታወቃል።[66] ይሁን እንጂ ሌሎች ሀገሮች ተጨማሪ የሌላ ሀገር ዜግነት ያለውን ግለሰብ እንደ እንግሊዛዊ ላይቆጥሩት የችላሉ። ይህን አስመልክቶ አንድ እንግሊዛዊ የአለም አቀፍ ህግ ምሁር ሀሳብ ሲያቀርቡ "በዚህ ጉዳይ ... ላይ ከአለም አቀፍ ዉሎች ከሚመነጩ ግዴታዎች ባሻገር ሀገሮች ሊከተሉት የሚገባው ትክክለኛው መመዘኛ ግለሰቡ ለመጨረሻ የመረጠውን ሀገር ዜግነት ማወቅ ነው" [67] ብለዋል።

በዚህ ነጥብ ላይ የሄጉ ኮንቬንሽን በይበልጥ ተጨባጭ የሆነ መመዘኛ የወሰደ ይመስላል። በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 5 ሥር የሚከተለው ሰፍሯል፤

"በአንድ በሦስተኛ ሀገር ውስጥ ከአንድ በላይ ዜግነት ያለው ሰው የአንድ ሀገር ዜግነት ብቻ እንዳለው መቆጠር አለበት። ... ሶስተኛው ሀገር ግለሰቡ ካለው የተለያየ ዜግነት ውስጥ ግለሰቡ አዘውትሮና በዘላቂነት የሚኖርበትን ሀገር ዜግነት ወይም እንደሁኔታው ግለሰቡ በይበልጥ ቅርበት ያለው መስሎ የሚታየውን ሀገር ዜግነት በክልሉ ውስጥ ሙሉ በሙሉ መቀበል አለበት።"[68]

ሁለት ወይም በላይ የሆኑ ሀገሮች የእነርሱ ዜግነት ላለው ግለሰብ ዲፕሎማሲያዊ ጥበቃ ለመስጠት ያላቸውን መብት አስመልክቶ የሚፈጠር አለመግባባት ብዙውን ጊዜ እጅግ አወዛጋቢ ይሆናል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሚስተር ኖተቦህም ለተባለ ግለሰብ ዲፕሎማሲያዊ ጥበቃ ወይም ከለላ መስጠትን አስመልክቶ በጓቴማላና ሊክተንስታይን መካከል በተነሳው ውዝግብ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ከግለሰቡ ጋር ቀጥተኛና ግልፅ የሆነ ግንኙነት /ጄኑዊንሊንክ/ ያለው ሀገር ዲፕሎማሲያዊ ጥበቃ የመስጠት መብት አለው በማለት ወስነዋል።[69]

ይህ የ "ቀጥተኛና ግልፅ ግንኙነት" /ጄኑዊን ሊንክ/ ፅንሰ ሃሳብ በብዙ የአለም አቀፍ ህግ ምሁራን ዘንድ ተቀባይነትን አላገኘም። በርግጥም ይህ ፅንሰ ሃሳብ በሄግ

ኮንቬንሽን አንቀጽ 3 ውስጥ ከተጠቀሰውና በየሀገሮቹ የውስጥ ህግ መሠረት አንድ ሰው የሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሀገሮች ዜግነት በሚኖረው ጊዜ ከግለሰቡ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ኖረውም አልኖረው እያንዳንዱ ሀገር ግለሰቡን እንደራሱ ዜጋ ሊቆጥረው ይችላል ከሚለው መሠረታዊ መርህ ጋር የሚቃረን ነው። የ "ጁስ ሳንጉዊን" መርህን የሚከተል አንድ ሀገር ለምሳሌ ከዜጎቹ የተወለደ ማንኛውንም ግለሰብ ከዚህ ቀደም ሀገሩን ፈፅሞ አይቶ የማያውቅ እንዲሁም በግለሰቡና በሀገሩ መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው ቢሆንም እንኳ እንደራሱ ዜጋ ይቆጥረዋል። በዚህ ረገድ ሻን ፓንሁይስም ሆነ ጂ.ኤል. ኩንዝ "የቀጥተኛና ግልፅ ግንኙነት" መርህ /ጂኑዊን ሊንክ/ ከአለም አቀፍ ልማዳዊ ህግ ውስጥ የሚመደብ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ እንደሌለ አበክረው ተከራክረዋል።[70] ይልቁንም በአንድ ሀገርና በአንድ ግለሰብ መካከል አነስተኛም ቢሆን ግንኙነት እስካለ ድረስ ግለሰቡ የዚሁ አገር ዜጋ ነው የሚል አስተያየት ይሰነዝራሉ።

ይሁን እንጂ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት በኖተቦህም ጉዳይ ላይ የጠቀሰው የቀጥተኛና ግልፅ ግንኙነት /ጂኑዊን ሊንክ/ መርህ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሀገሮች የእነርሱን ዜግነት ለያዘ ግለሰብ የሚሰጡትን ዲፕሎማሲያዊ ጥበቃ አስመልክቶ በሀገሮች መካከል ለሚነሳው ክርክር እንደመፍትሄ የሚያገለግል መርህ መሆኑ አጠቃላይ ስምምነት የተደረሰበት ነው።[71]

ጣምራ ዜግነትና ዜግነት አልባነት የመሳሰሉ ሁኔታዎች አለም አቀፍ ማህበረሰብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊያስወግዳቸው የማይችል ችግሮች ይመስላሉ። የሀገሮች የዜግነት ሕጎች አለመመሳሰልና እንዲሁም ከዜግነት መላቀቅን የሚገዙት ሕጎች መለያየት ችግሮቹ ወደፊትም በተደጋጋሚ እንዲከሰቱ ያደርጋል። ጦርነትና አብዮት /ለውጥ/ የመሳሰሉ ክስተቶች አንድን ሀገር የተወሰነ የግዛት ክልል ሊያሳጡ ወይም የዚያን ሀገር ጠቅላላ መበታተን ሊያስከትሉ ይችላሉ። ይህ በበኩሉ ደግሞ ጥቂቶች ጭርሱን ዜግነት አልባ /ዜግነት የለሽ/፥ ሌሎች ደግሞ ከአንድ በላይ ዜግነት ያላቸው የሚሆኑበትን ሁኔታ ይፈጥራል።[72]

በዜግነት ሕጎች መካከል ያለው ግጭት ከ "ብሔራዊ አገር" /ኔሽን ስቴትስ/ መርህ ግቶችቶች ጋር የተከሰተ አዲስ ችግር በመሆኑ ለችግሩ አግባብ ያላቸው ኮንቬንሽኖችና ልማዳዊ የአለም አቀፍ ህግ መርሆች እስኪዳብሩ ድረስ ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስድ ይመስላል። ምናልባት የአውሮፓ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብን የመሳሰሉ ልዕለ መንግሥታዊ /ሱፕራናሽናል/ ድርጅቶች ወደ ከፍተኛ የውህደት ደረጃ መድረስ የአንድ ግለሰብ የትውልድ ቦታ እንዲሁም የወላጆች ማንነት ከግምት ውስጥ ወደ ማይገባበት አዲስ ዓይነት አሠራር ሊያመሩ ይችላል። ከዜግነት ጋር ተያይዞ የሚከሰተው ችግር ሀገሮች ስለሉአላዊነታቸው ያላቸው አመለካከት በአዲስ አመለካከት ሲተካ ብቻ የሚወገድ ይመስላል።

እስከዚያ ድረስ ግን አለም አቀፍ ህግ ለጣምራ ዜግነትና ዜግነት አልባነት መኖር እውቅና እንደሰጠ ይቆያል። የ1930 ዓ.ምቱ የሄግ ጉባዔ እንዲሁም በጉባዔው የፀደቀው ኮንቬንሽን የጣምራ ዜግነትና ዜግነት አልባነት ክስተቶችን ይቀበላል። ነገር ግን ጉባዔውም ሆነ ኮንቬንሽኑ የችግሮቹን ምልክቶች እንጂ መንስኤያቸውን አልመረመሩም። ይህም የሆነበት ምክንያት ሀገሮች የዜጎቻቸውን ማንነት የመወሰን መብት ያቀዳጃቸውን ሉአላዊነት ለድርድር ለማቅረብ ፈቃደኛ ሆነው ባለመገኘታቸው ነው።[73]

ዜግነት አልባነትና ጣምራ ዜግነት በግለሰቦች ላይ ውስብስብ ችግሮች ከማስከተላቸውም በላይ አልፎ አልፎም በሀገሮች መካከል ግጭቶችን ይፈጥራሉ። ስለዚህ እነዚህን ክስተቶች ማስወገድ አስፈላጊ ነው። ይህን ከግብ ለማድረስ ... ጆሴፍ ኤል ኩንዝ በ1960 ዓ.ም. ከሰነዘረው ሃሳብ የተሻለ አማራጭ ያለ አይመስለኝም። ይህንኑ አስመልክቶ ኩንዝ የሚከተለውን ብሏል፡

"... አለም አቀፍ ህግ ከዜግነት ጋር ተያይዞ የሚፈጠረውን ችግር ሥርዓት ባለው መንገድ ሊፈታው ይገባል። ይህም የሚሆነው ችግሩን የመፍታት ሥልጣንና ኃላፊነት ለሀገሮች አሳልፎ በመስጠት ሳይሆን የዜግነትን አሰጣጥም በተመለከተ መብትና ግዴታዎችን የሚደነግጉ አንድ ወጥ መርሆችን በማውጣት ነው። ይህም

ቢሆን በራሱ በቂ አይደለም። ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ አለም አቀፍ ውል ቢፈረምና ቢፀድቅም እንኳን በቋንቋዎችና በየሀገሮቹ ፍርድ ቤቶች በሚሰጡ ትርጓሜዎች ልዩነት ሳቢያ ሌላ ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ ነው። ስለዚህ አለም አቀፍ ዉሉን አንድ ወጥ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ የሚያውል አለም አቀፍ የዜግነት ፍርድ ቤት በተጨማሪ ማቋቋም ያስፈልጋል።"[74]

ነገር ግን ይህ አመለካከት ሰፊ ተቀባይነትን ከማግኘቱ በፊት ረዘም ያለ ጊዜ ይጠይቃል። እስካሁንም ድረስ ሀገሮች በውስጥ ሕጎቻቸው መሠረት ያላቸውን የዜጎቻቸውን ማንነት የመወሰን ሰፊ ሥልጣን እንደያዙ ናቸው። የዜጎቻቸውን ማንነት በመወሰኑ ሂደት የአለም አቀፍ ውል ገዴታዎችን ጨምር የሚከተሉዋቸው መመሪያዎች አሉዋቸው። በዚህም ለዜጎቻቸው ጣምራ ዜግነት ሊሰጡ የሚችሉና ዜግነት አልባነት ሊያስከትሉ የሚችሉ ድንጋጌዎችን ከሕጎቻቸው ውስጥ ያስወግዳሉ። ከ1930 የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ አንቀጽ 4ን የመሳሰሉ ድንጋጌዎች እንደዚህ ባሉ ግንዛቤዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። አንዲት ኢትዮጵያዊት ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ባልዋን ዜግነት ብታገኝ ወዲያውኑ ኢትዮጵያዊ ዜግነትዋን ታጣለች። ይህ ሴቲቱ በአንድ ጊዜ ኢትዮጵያዊ ዜግነትና የባልዋን ዜግነት የምታገኝበትን ሁኔታ ያስወግዳል። በሌላ በኩል የባልዋ ሀገር የዜግነት ህግ የባልዋን ዜግነት የማይሰጣት ከሆነ ወዲያውኑ ኢትዮጵያዊ ዜግነትዋን ትይዛለች። ይህ አንዲት ከውጭ ሀገር ዜጋ ጋር ጋብቻ የፈፀመች ኢትዮጵያዊት የባልዋን ዜግነት ሳታገኝ ኢትዮጵያዊ ዜግነት እንዳታጣና በዚሁም ሳቢያ ዜግነት አልባ የምትሆንበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ለማድረግ የታቀደ ነው።

ሀገሮች እነዚህን መርሆች በሕጎቻቸው ውስጥ ሊያስገቡዋቸው ይችላሉ። ነገር ግን በዚህ ረገድ በሌሎች ሀገሮች የውስጥ ህግ ላይ ምንም ዓይነት ተፅእኖ ማሳደር አይችሉም። በሌላ አነጋገር ሌሎች ሀገሮች የድርብ ዜግነትን መከሰት የሚያመቻቹ ህጎችን ከማውጣት እንዲታቀቡ ማድረግ አይችሉም። ይህም በዜግነት ሕጎቻቸው ውስጥ ጋብቻ በሴቶች ዜግነት ላይ ምንም የተለየ ውጤት አያስከትልም ብለው

በሚደነገጉ ሀገሮች ውስጥ ሊከሰት የሚችል ሲሆን የሶሺየት ሀብረት የዜግነት ህግ ከነዚህ አንዱ ነው።[75]

እንዲህ ባለው ሁኔታ አንዲት ሴት ፍላጎት ቢኖራትም እንኳ የባልዋን ዜግነት ማግኘት አትችልም። ስለዚህ አንዲት የሶሺየት ዜጋ አንድ ኢትዮጵያዊ ብታገባ ጣምራ ዜግነት ይኖራታል። ነገር ግን አንዲት የዮርዳኖስ ዜጋ አንድ የሶሺየት ዜጋ ብታገባ ምንም ዜግነት አይኖራትም ማለት ነው። ምክንያቱም በዮርዳኖስ ህግ መሠረት ከውጭ ዜጋ ጋር ጋብቻ የፈፀመች ዮርዳኖሳዊት ወዲያውኑ ዜግነትዋን የምታጣ ሲሆን[76] በሶሺየት ህግ መሠረት ደግሞ ዜግነትዋ በጋብቻ የተነሳ የማይለወጥ በመሆኑ ነው።[77]

የየሀገሮቹን የውስጥ ሕግጋት የሚወስኑት መሠረተ ሀሳቦችና ግንዛቤዎች የተለያዩ በመሆናቸው አንድ አገር የሀጉን ገዥነትና የሚያስከትለውንም ውጤት በቀላሉ ከሌሎች ሀገሮች ሕጎች ጋር የሚስማማ እንዲሆን ለማድረግ አይችልም። ይህንንም ለማድረግ ከአለም አቀፍ ውል ከሚመነጩ ግዴታዎች በቀር ምራላዊም ሆነ ሕጋዊ ግዴታ የለበትም። ይሁን እንጂ ሀገሮች ዜግነትን በተመለከተ ስፈ ተቀባይነት ካላቸው መርሆች ራሳቸውን ነፃ ማድረግ ይችላሉ ማለትም አይደለም።[78]

ከዚህ በላይ በሚገባ የተብራሩትና ዜግነትን በተመለከተ በሰፊው የሚሠራባቸው መርሆች በይበልጥ ግልፅ ይሆኑ ዘንድ በአጭሩ ይቃኛል።

ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ዜግነትን አስመልክቶ ለተደረገ አለም አቀፍ ውል ተዋዋይ የሆነ ሀገር የውሉን ድንጋጌዎች ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት። የዚያው ሀገር ፍርድ ቤቶችም እንዲሁ ድንጋጌዎችን በሥራ ላይ ማዋል አለባቸው። የዚህ ዓይነቱን አለም አቀፍ ውል ድንጋጌዎች አለማክበር በአለም አቀፍ ህግ ሥር ያለ ማንኛውንም ዓይነት ቅጣት ሊያስከትል ይችላል።

ከአለም አቀፍ ውል የሚመነጭ ምንም ዓይነት ግዴታ በሌለበት ሁኔታ የዜግነት ጥያቄ በሀገሮች የውስጥ ህግ መሠረት ይፈታል። በአለም አቀፍ ህግ ዘንድ አንድን

ግለሰብ በዜግነት መቀበል ወይም ግለሰቡን ካለው ዜግነት ማላቀቅ የሀገሮች የውስጥ ህግ ጉዳይ መሆኑ ተቀባይነት ያለው አሠራር ነው። በሰፊው የሚሠራባቸውና ሀገሮች ለግለሰቦች የዜግነት መብት ለመስጠት የሚጠቀሙባቸው መርሆች "<u>ዩስ ሳንጉዊንስ</u>" እና "<u>ዩስ ሳሊ</u>" ናቸው። "<u>ዩስ ሳንጉዊንስ</u>" በግለሰቡ ወላጆች ዜግነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን "<u>ዩስ ሳሊ</u>" ደግሞ በግለሰቡ የትውልድ ቦታ ላይ የተመሠረተ መርህ ነው። ጋብቻ በሴቶች ዜግነት ላይ የሚያስከትለው ውጤት ደግሞ ሀገሮች በዜግነት ሕጎቻቸው ውስጥ በሰፊው የሚጠቀሙበት ሌላው መርህ ነው።

የአንድን ግለሰብ ዜግነት አስመልክቶ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሀገሮች መካከል ክርክር በተነሣ ጊዜ በፍተቦህም ጉዳይ የተጠቀሰውና ከግለሰቡ ጋር ቀጥተኛና ግልፅ ግንኙነት ያለው ሀገር ዜጋ ነው የሚለው መርህ ተግባራዊ ይሆናል። ግለሰቡ በርግጥም ከዚያ ሀገር ጋር ቀጥተኛና ግልፅ ግንኙነት ያለው መሆን አለመሆኑ በርካታና የተለያዩ ጠቋሚ ያላቸው ሁኔታዎችን በመመልከት ይወሰናል። /እነዚህም ሁኔታዎች የግለሰቡን የዘወትር መኖሪያ፣ የጥቅም ምንጮች፣ የቤተሰብ ትስስር፣ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ያለው ተሳትፎ፣ ከአንድ ሀገር ጋር ያለው ትስስር ወይም ቅርበት እንዲሁም ይኸው ትስስር በልጆቹ ሥነ ልቡና ላይ ያለውን ተፅዕኖ ... ያካትታል/። በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት የኖተቦህም ጉዳይ ላይ የተጠቀሰው የቀጥተኛና ግልፅ ግንኙነት /ጄኑዊን ሊንክ/ ንድፈ ሀሣብ ምንም እንኳ በአንዳንዶች ዘንድ ተቃውሞ ቢገጥመውም አለም አቀፍ ህግ ወደመሆን ደረጃ ያደገ ይመስላል።

- ፈ -

ጋብቻ የፈፀሙ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ በ1930 የወጣው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ በወቅቱ ማለትም ከአንደኛው የአለም ጦርነት በኋላ ባሉት ጊዜያት ዜግነትን በተመለከተ በሰፊው ይሠራባቸው ከነበሩት መርሆች የሚለይ አይደለም። በርግጥ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ጋብቻ የፈፀሙ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ የሕጉ ድንጋጌዎች በ1930 አካባቢ ከኢትዮጵያ ጋር ዲፕሎማቲካዊና ልዩ ልዩ ግንኙነቶች

በነበራቸው በአብዛኞቹ ሀገሮች ዘንድ በሚሠራበትና በቤተሰባዊ ተምረት /አንድነት/ መርህ ላይ የተመሠረተ መሆናቸውን ይገነዘባል።

ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ በፊት ብዙ ኢትዮጵያውያን በውጭ ሀገር ያለመኖራቸውና ብዙ የውጭ ዜጎችም በኢትዮጵያ ያለመኖራቸው ጉዳይ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት። በዚህም ሳቢያ የግለሰቦችን ዜግነት አስመልክቶ ከዚህ ቀደም በተጨባጭ የተነሳ ችግር ካለመኖሩም ባሻገር መልክ የያዙ ሀገራዊ ዜግነት ፅንሰ ሀሳቦችም ሊዳብሩ አልቻሉም። የ1930ው የዜግነት ህግ ከዜግነት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የወጣ የመጀመሪያው ህግ ነው።

በክፍለ ዘመኑ መባቻ ላይ በርካታ የውጭ ኃይሎች በኢትዮጵያ ወኪሎች ነበሩዋቸው። ከእነዚሁ ኃይሎች አብዛኞዎቹ እንዱን ወይም ሌላውን የሀገሪቱን ክፍል በቅኝ ግዛት የመያዝ ምኞት እንደነበራቸው መገንዘብ ይቻላል። ባጠቃላይ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ በሌጋሲዮኖች የተወከሉ ሰባት የሚሆኑ ሀገሮች ሲኖሩ /አሜሪካ፣ ብሪታኒያ፣ ቤልጅየም፣ ፈረንሳይ፣ ግሪክ ጀርመን/ እንዲሁም በቆንስላዎች የተወከሉ ሁለት ሀገሮች፣ ስዊድንና ቱርክ ነበሩ።[79]

በ1908 ፈረንሳይ ክሉቡኮውስኪ በተባለው ወኪልዋ በኩል የክሉቡኮውስኪ ውል በመባል የሚታወቀውን ስምምነት ከአጼ ምኒሊክ ጋር ተፈራረመች። ይህ ውል ሌሎች ጉዳዮችን ጨምሮ በፈረንሣይ ዜጎች መካከል እንዲሁም በፈረንሳይና በኢትዮጵያ ዜጎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የሚሰማ ልዩ ፍርድ ቤት ለማቋቋም የተደረገ ስምምነት ነው።[80] በጊዜው የነበሩት ብዙዎቹ የውጭ ኃይሎችም በተናጠል ከኢትዮጵያ ጋር ... የወዳጅነት ስምምነት ተፈራርመው ስለነበር የክሉቡኮውስኪ ውል ድንጋጌዎች ለሌሎችም ሀገሮች በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

የፍርድ ቤቱን አወቃቀር በተመለከተ ምንም እንኳ ፈረንሳይ በቆንስላ የሚመሩ ፍርድ ቤቶች እንዲኖሩ አጥብቃ ብትሻም አጼ ምኒሊክ ይህንን ሀሳብ ፈፅሞ አልተቀበሉትም።[81] በዚህም የተነሣ ዜጎቻቸው በክርክሩ ተሳታፊ የሆኑ ሀገሮች

ወኪሎች በአባልነት የሚገኙበትና ኢትዮጵያውያን ዳኞችን የያዘ አንድ ልዩ ፍርድ ቤት ተቋቋመ።

ከካፒቱሌሽን ውል ድንጋጌዎች አንዱ የልዩ ፍርድ ቤቱ አባል የሆነ ኢትዮጵያዊ የብሪታኒያን፥ የፈረንሳይንና የኢጣሊያን ሕጎች የማወቅ ግዴታ አለበት የሚል ነው።[82] ከዚሁ ጋር በማያያዝ በ1930 ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተብለው የነገሡትና በዚያው ዓመት የኢትዮጵያን የዜግነት ህግ ያወጡት ራስ ተፈሪ መኮንን በልዩ ፍርድ ቤቱ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ አባል በመሆን ማገልገላቸውን መጠቆም አስፈላጊ ነው።[83]

የካፒቱሌሽን ውል በኢትዮጵያ ውስጥ ለዘመናዊ የሕግ ፅንሰ ሀሳቦች እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል። ልዩ ፍትድ ቤቱም በውጭ ዜጎች መካከል የውጭውን ሕግ፥ እንዲሁም በኢትዮጵያውያን ተከራካሪዎች መካከል የኢትዮጵያን ሕግ በመጠቀም ይሠራ ነበር።[84] ስለዚህም በልዩ ፍርድ ቤቱ ፊት ኢትዮጵያዊ የሕግ ፅንሰ ሀሣቦች ከዘመናዊው የአውሮፓ የሕግ አስተሳሰብ ጋር መጋጨታቸው አልቀረም። ከዚሁ ጋር በተያየዘ መልኩ ፍርድ ቤቱ አውሮፓዊ የሕግ ፅንሰ ሀሣቦች ወደ ኢትዮጵያ ሥርዓተ ሕግ ውስጥ እንዲገቡ በቀዳሚ መድረክነት አገልግሏል።

ከኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ አንፃር ሲታይ የካፒቱሌሽን ውል ጠቃሚ አስተዋጽኦ የልዩ ፍርድ ቤቱን የዳኝነት ሥልጣን ለመከለል የኢትዮጵያውያን ዜጎችን ማንነት የመወሰን አስፈላጊነት ማሳየቱ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ልዩ ፍርድ ቤቱ የወደፊቶቹ ኢትዮጵያዊያን ሕግ አውጭዎች በወቅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ተወክለው ከነበሩ ሀገሮች በተለይም ከብሪታኒያ ከፈረንሳይና ከኢጣሊያ የዜግነት ሕግ ፅንሰ ሀሳቦችና መርሆች ጋር የሚተዋወቁበትን አመቺ መድረክ ፈጥሯል።

በ1930 ዓ.ም. ያገቡ ሴቶችን በተመለከተ የዜግነት ሕጎቻቸው ለቤተሰባዊ አንድነት ቅድሚያ በሚሰጥ መርህ ላይ የተመሠረቱ እንዲሁም የዜግነት ሕጎቻቸው በጾታዎች እኩልነት መርህ ላይ የተመሠረቱ ሀገሮች ኢትዮጵያ ውስጥ ተወክለው

ነበር። ከነዚህም ውስጥ የአሜሪካና የፈረንሳይ የዜግነት ሕጎች በጾታዎች እኩልነት መርህ ላይ የተመሠረቱ ሲሆን የሌሎች ሕጎች ደግሞ በቤተሰብ አንድነት መርህ ላይ የተመሠረቱ ነበሩ።

በነሐሴ 10/1927ቱ የፈረንሳይ ሕግ መሠረት "አንዲት የውጭ አገር ዜጋ የሆነች ሴት አንድ ፈረንሳዊ ሰው ስታገባ የፈረንሳይ ዜጋ የምትሆነው ራሷ በይፋ በምታመለክትበት ጊዜ ወይም በአገርዋ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የግድ የባሏን ዜግነት እንድትይዝ የምትደረግ ሲሆን ብቻ ነው። ..." እንዲሁም

"የባዕድ ዜጋ የሆነ ሰው የምታገባ አንድ ፈረንሣዊት በባሏ አገር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የባሏን ዜግነት እንድትይዝ በግልጽ ካላስታወቀች በስተቀር የፈረንሣይ ዜግነቷን ይዛ ትቆያለች።"

የሴፕቴምበር 22/1922ቱ የዩናይትድ ስቴትስ ሕግ ከፈረንሣይ ሕግ ጋር በጣም ይመሳሰላል፤

"ይህ ሕግ ከወጣ በኋላ የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ የሆነን ሰው የምታገባ ማንኛዋም ሴት በዚህ ጋብቻ ምክንያት ብቻ የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ አትሆንም ... ሆኖም ለዜግነት ብቁ ሆና ከተገኘች የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ ልትደረግ ትችላለች

..." እንዲሁም "አንዲት የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ የሆነች ሴት ዜግነቷን ስለመተዋ በጽሁፍ ካልገለጸች በስተቀር ይህ ሕግ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በጋብቻዋ ምክንያት የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ መሆንዋ አይቋረጥም ..."።

የ1922ቱ የዩናይትድ ስቴትስ ሕግና የ1927ቱ የፈረንሳይ ሕግ ያገባች ሴት የራሷን ዜግነት እንድትመርጥ የሚያስችላት መብት ለሚጠብቁ ሕጎች ዓይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው።

እዚህ ላይ ሁለቱ መንግሥታት በነዚህ ሕጎች አማካይነት ያገቡ ሴቶችን ዜግነት በሚመለከት ቀድሞ የነበራቸውን አቋም ሙሉ በሙሉ መገልበጣቸው ትኩረትን የሚስብ ነው። የ1855ቱ የዩናይትድ ስቴትስ ሕግ፣ በ1907ቱ ሕግ እንደተጠናከረው፣ እንዲሁም የ1804ቱ የናፖሊዮን ሕግ አንቀጽ 12 እና 19፣ በ1889ኙ ሕግ እንደተሻሻለው፣ ያገቡ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ ከአሁኑ የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ ጋር አንድ ዓይነት ነበሩ። ሕጎቹ ጋብቻ ለሴቷ የባሏን ዜግነት የማስጠት ውጤት በነበረው የቤተሰብ አንድነት መርህ ላይ የተመሠረቱ ነበሩ። በግልጽ እንደሚታየው የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ ከ1922ቱ የዩናይትድ ስቴትስ ሕግና ከ1922ቱ የፈረንሳይ ሕግ ጋር በቃልም ሆነ በመንፈስ ምንም ዓይነት ተመሳሳይነት የለውም። ለ1930ው ሕግ አውጭ እነኝህ ሕጎች ከሚገባው በላይ ዘመናዊ የሆኑበት ይመስላል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ የተወከሉ የሌሎች አገሮች የዜግነት ሕጎች ውስጥ በሚታዩ ጽንሰ ሃሳቦችና መርሆዎች ላይ የተመሠረተ መሆኑ ግልጽ ነው። ከነኝህ መሐል የቤልጅግ፣ የጣልያን እና የግሪክ[87] የዜግነት ሕጎች ከኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ ጋር ጉልህ ተመሳሳይነት አላቸው።

የሜይ 15/1922ቱ የቤልጅግ ሕግ እንዲህ ይላል፣

"አንድ ቤልጅጋዊ ሰው የምታገባ የውጭ አገር ሴት ... የባሏን ዜግነት ትወስዳለች" እንዲሁም

"የሚከተሉት ሰዎች የቤልጅግ ዜግነታቸውን ያጣሉ፣

በባሏ አገር ሥራ ላይ በዋለው ሕግ መሠረት የባሏን ዜግነት የምታገኝ ከሆነ፣ የተወሰነ ዜግነት ያለው አንድ የውጭ አገር ዜጋ የምታገባ ቤልጅጋዊት ሴት።"

ይህ ሕግ ቤልጅጋዊቷ ሴት ዜግነቷን ይዛ መቆየት መፈለጓን በምታስታውቅበት ጊዜ ዜግነቷን ይዛ የመቆየት መብቷን ይጠብቅላታል።

የጁን 13/1912ቱ የጣልያን ሕግ እንዲህ ይላል፣

"አንድን ዜጋ የምታገባ የውጭ አገር ዜጋ የሆነች ሴት የጣልያን ዜግነት ታገኛለች ..." እንዲሁም "የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ሰው የምታገባ ዜጋ በጋብቻው ምክንያት ለእርሷ የሚተላለፍ ዜግነት ባሏ ያለው ከሆነ የጣልያን ዜግነቷን ታጣለች።"

በመጨረሻ በኦክቶበር 29/1856 የወጣው የግሪክ ሕግ ቁጥር 391 እንዲህ ይላል፣ "ግሪካዊ ሰው የምታገባ እንዲት ባዕድ ሴት ግሪካዊት ትሆናለች"። እንዲሁም "የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ሰው የምታገባ.ግሪካዊት ሴት ጋብቻዋ የባሏን ዜግነት የሚያሰጣት ሲሆን ብቻ የግሪክ ዜግነቷን ታጣለች።" የ1931ዱ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በጃፓኑ የሜጂ ሕገ መንግሥት መልክ ስለተቀረጸ[88] የኢትዮጵያው ሕግ አውጭ ለጃፓን የሜጂ ዘመን መንግሥት የሕግ ሥርዓት ልዩ ትኩረት የሰጠ ይመስላል። ምንም እንኳን በ1930 ጃፓን በኢትዮጵያ ውስጥ ለጋሲዮን ወይም ቆንስላ ያልነበራት ቢሆንም የማርች 1899ኙ[89] ሕግ ቁጥር 66 ከኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ ጋር ትልህ ተመሳሳይነት አለው።

የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች እንደሚሉት፣

"አንድ ባዕድ የሆነች ሴት በሚከተሉት ሁኔታዎች የጃፓንን ዜግነት ታገኛለች፣ /1/ የአንድ ጃፓናዊ ሚስት በመሆን"፤ ነገር ግን፣ "አንዲት ጃፓናዊት አንድ ባዕድ የሆነ ሰው በማግባቷ የባሏን ዜግነት ያገኘች እንደሆነ የጃፓን ዜግነቷን ታጣለች።" የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ እንዲህ ይላል፣ አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከአንድ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነች ሴት ጋር የሚያደርገው ሕጋዊ ጋብቻ ለሴትዮዋ ኢትዮጵያን ዜግነት ያሰጣታል። ..." እንዲሁም "አንድ ኢትዮጵያዊት ሴት ከአንድ የውጭ አገር ዜጋ ጋር በውጭ አገር የምትፈጽመው ሕጋዊ ጋብቻ የባሏን ዜግነት የሚያሰጣት ከሆነ ይኸው ጋብቻ የኢትዮጵያ ዜግነቷን ያሳጣታል። ይህ እስካልሆነ ድረስ የኢትዮጵያ ዜግነቷን ይዛ ትቆያለች"።

በ1940ዎቹ እንዲሁ የ1922ቱ የዩናይትድ ስቴትስና የ1927ቱ የፈረንሳይ ህጎች ያገባች ሴት የራሷን ዜግነት የመምረጥ ነፃነት አላት በሚለው አዲስ ጽንሰ ሃሳብ ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው እንዳልተለመደ እንግዳ ነገር ይቆጠሩ ስለነበር[90] እንደልዩ ሁኔታ ይታዩ እንደነበር እዚህ ላይ ሊገለጽ ይገባዋል።

በ1930 ዓ.ም. በሥራ ላይ የዋለው በኢትዮጵያ ውስጥ በጊዜው ተወክለው የነበሩት የሌሎች ኃይሎች የዜግነት ሕግ ውስጥ ይንፀባረቅ የነበረው መርህ ነበር። በጊዜው በሥፋት ሥራ ላይ ውሎ በነበረው መርህ መሠረት ባገባች ባዕድ ሴት ዜግነት ላይ ጋብቻ የሚያስከትለው ውጤት ያለጥያቄ ተቀባይነት ያገኘ ነበር።[91] ከላይ የተመለከተው የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንቀጽ 2 የዚህ መርህ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው።

- ሰ -

ያገቡ ሴቶችን የዜግነት ህግ አመጣጥና ዕድገት የተመለከተ ከዚህ በላይ የቀረበው አጭር ሐተታ መንግሥታት በዜግነት ህጎቻቸው ውስጥ ሁለት ጽንሰ ሃሳቦችን ሥራ ላይ እንደሚያውሉ አሳይቷል። የመጀመሪያውና ነባሩ ጽንሰ ሃሳብ በቤተሰብ አንድነት መርህ ላይ የተመሠረተ ሲሆን የመርሁ መሠረት ጋብቻ ለሚስት የባሏን ዜግነት የማሰጠት ውጤት አለው። ሁለተኛውና የቅርቡ ጽንሰ ሃሳብ ያገባች ሴት የራሷን ዜግነት የመምረጥ ነፃነት አላት በሚለው መርህ ላይ የተመሠረተ ሲሆን በመርሁ መሠረት ጋብቻ በራሱ በሚስቲቱ ዜግነት ላይ የሚያስከትለው ምንም ውጤት የለም።

የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ በግልጽ የተመሠረተው በነባሩ ጽንሰ ሃሳብ ላይ ነው። ይህም በመሆኑ አንድ ባዕድ ሴት ከአንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ጋር የምትፈጽመው ጋብቻ ለሚስቲቱ የኢትዮጵያን ዜግነት የማሰጠት ውጤት አለው፤ ማለትም በጋብቻው ምክንያት ብቻ የኢትዮጵያ ዜጋ ትሆናለች። በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንቀጽ 2 መሠረት ባዕድ ለሆነችው ሴት የኢትዮጵያን ዜግነት የሚሰጣት ጋብቻ ነው።

ስለዚህ መረጋገጥ የሚገባው ነገር ባዕድ የሆነችው ሴት ከአንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ መፈፀሟ ብቻ ነው። ይህ ከተረጋገጠ ደግሞ በቂ ሆኖ የኢትዮጵያ ዜጋ ትሆናለች። የኢትዮጵያ ዜጋ የመሆንን ምርጫ አለመቀበል ባዕድ ለሆነችው ሴት አልተፈቀደላትም። እንዲሁም በሕጋዊው ጋብቻ ሥነ ሥርዓት ምክንያት የኢትዮጵያ ዜጋ መሆንዋን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉትን ሰነዶች የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች፣ የመከልከል ምርጫ የላቸውም። ባዕድ ለሆነችው ሴትዮ በኢትዮጵያ ዜግነት የሚሰጣት ጋብቻ በመሆኑ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች የሚችሉት ባዕድ የነበረችው ሴት የኢትዮጵያ ዜጋ መሆንዋን በይፋ መግለፅ ብቻ ነው። ባለሥልጣኖቹ ሴትዮዋ የኢትዮጵያ ዜጋ እንድትሆን መወሰን አይችሉም። በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ የባለሥልጣኖቹ ተግባር ባዕድ የሆነችውን ሴት የኢትዮጵያ ዜጋ ማድረግ ሳይሆን፣ ዜጋ መሆንዋን በይፋ ማረጋገጥ ነው። ባዕድ የሆነችውን ሴት በተመለከተ የባለሥልጣኖቹ ውሳኔ የሚኖረው ውጤት በአገር ተወላጅ የኢትዮጵያ ዜጎች ላይ ካለው ውጤት የተለየ አይደለም።

በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነን ሰው ያገባች ባዕድ ሴት የኢትዮጵያን ዜግነት የምታገኘው የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን የምትፈልግ መሆንዋን በይፋ ስትገልፅ ወይም ስትስማማ ነው ማለት ጋብቻ ብቻውን በሴትየዋ ዜግነት ላይ የሚያስከትለው ምንም ውጤት የለም የሚለውን አዲስ መርህ ሥራ ላይ ማዋል ይሆናል። አሁን የሚቀረው የስዊትላና ማማዶቫና የአሜሪካን ኮሚኒቲ ት/ቤት ጉዳይ በሚመለከት የውራጃው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ከዚህ ሁኔታ ጋር መስማማቱን መመርመር ነው።

በአንዲት ስዊትላና ማማዶቫ /ከዚህ በኋላ "አቤት ባይ"/ በሚባሉ ሴት እና በአሜሪካን ኮሚኒቲ ት/ቤት /ከዚህ በኋላ "መልስ ሰጭ" በሚባለው/ መሐል እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ በዚህ ጽሁፍ በገጽ 1 ላይ በተጠቀሰው የሥራ ክርክር ያገቡ ሴቶች ዜግነት በኢትዮጵያ ህግ የሚል ጭብጥ ተነስቶ ነበር።

አቤት ባይዋ የሶቪየት ሀብረት ዜጋ ሲሆኑ በሶቪየት ሀብረት ህግ መሠረት ከአንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከሆነ ሰው ጋር በ1979 ሞስኮ ውስጥ ተጋብተዋል። አዋጅ 64/68 በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች በሚያዘው መሠረት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሥራ ፈቃዳቸውን በየጊዜው ማደሱ እንደተጠበቀ ሆኖ አቤት ባይዋ በ1982 እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ በመልስ ሰጭ ተቀጥረው ነበር።

መልስ ሰጪ የሥራ ፈቃዱን ለማሳደስ ፈቃደኛ ባለመሆኑና አቤት ባይዋ ለሥራው በቂ አይደሉም በሚል ምክንያት የቅጥር ውሉን በመሠረዙ አቤት ባይ ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስማሚ አቤቱታቸውን አቀረቡ። በአቤቱታቸው ውስጥ ያቀረቡት አንዱ ክርክር የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነን ሰው በማግባታቸው በ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ መሠረት እራሳቸው የኢትዮጵያ ዜጋ ስለሆኑ የሥራ ፈቃድ እንደማያስፈልጋቸውና የሥራ ፈቃዱ አለመታደስ ለቅጥር ውሉ መሠረዝ ምክንያት መሆን አይችልም የሚል ነው።

የአቤት ባይዋን ዜግነት በሚመለከተው ጉዳይ ላይ ከአንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከሆነ ሰው ጋር በፈፀሙት ጋብቻ ምክንያት ብቻ የኢትዮጵያ ዜጋ ሆነዋል ሲል አስማሚው ወሰነ።

ጉዳዩ በይግባኝ ሲቀርብለት የአውራጃው ፍ/ቤት የሠራተኛ ጉዳይ ችሎት የአስማሚውን ውሳኔ ገልብጦታል። ለዚህም ከተሰጡት ምክንያቶች መሐል የሚከተሉት አጠያያቂ ምክንያቶች ይገኙበታል።

ሀ/ በ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንቀጽ 2 መሠረት ከአንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከሆነ ሰው ጋር የተጋባች ባዕድ ሴት የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ይህንኑ በይፋ ካላስታወቀችና የመጀመሪያውን ዜግነቷን ካልተወች በስተቀር የኢትዮጵያ ዜግነት አታገኝም።

ለ/ የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ጣምራ ዜግነት ስለሚከለክል አቤት ባይዋ በአንድ ጊዜ የሶቪየት ሀብረትና የኢትዮጵያ ዜጋ መሆን አትችልም። አቤት

ባይዋ ጉዳዩ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቀርቦ በሰበር እንዲታይላቸው ወይም ውሣኔው እንዲሻርላቸው ለዐቃቤ ህግ ጽ/ቤት ማያቁ ሲያቀርቡ የአውራጃው ፍ/ቤት ውሣኔ ከ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ጋር የሚስማማ ስለሆነ ጉዳዩን ወደ ጠቅላይ ፍ/ቤት ለማቅረብ በቂ ምክንያት የለም በማለት ጽ/ቤቱ ማያቄውን ሳይቀበለው ቀርቷል።

የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንቀጽ 2 የሚከተለውን ይደነግጋል፣ "አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ ሰው ከአንድ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነች ሴት ጋር የሚያደርገው ሕጋዊ ጋብቻ ለሴትዮዋ የኢትዮጵያ ዜግነት ይሰጣታል።"[92] /የዚሁ አንቀጽ የአማርኛ ቅጂ ምንም እንኳን ቃል በቃል ሲተረጎም ከእንግሊዝኛው ጋር አንድ ባይሆንም በውጤቱ ከእንግሊዝኛው ጋር አንድ ነው/።

ይህ አንቀጽ የውጭ አገር ዜጋ ለሆነች አንዲት ሴት ዜግነት ለመስጠት ሕጋዊ ጋብቻ በቂ ለሆነባቸው የዜግነት ህጎች ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። አንቀጹ "የቤተሰብ አንድነት" በሚለው መርህ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ መሠረት ጋብቻ በአንድ የውጭ አገር ዜጋ በሆነች ሴት ዜግነት ላይ ውጤት እንዳለው ግልጽ ነው።

ይህ አንቀጽ የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ሰው ያገባች አንዲት የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነችን ሴት ከሚመለከተው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንቀጽ 4 ጋር ይጣጣማል። አንቀጽ 4 የሚከተለውን ይላል፣

"በአንዲት የኢትዮጵያ ዜጋ በሆነች ሴት የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ ሰው ጋር በውጭ አገር የሚፈፀም ጋብቻ ለሴትዮዋ የባሏን ዜግነት የሚያሰጣት ከሆነ የኢትዮጵያ ዜግነት እንድታጣ ያደርጋታል። ይህ ካልሆነ ግን የኢትዮጵያ ዜግነቷን ይዛ ትቆያለች።

እዚህም ላይ ለቤተሰብ አንድነት መርህ በድጋሚ ትድሚያ የተሰጠ ሲሆን የሴትዮዋ ስምምነት ግምት ውስጥ ሳይገባ ጋብቻው የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነችውን ሴት የኢትዮጵያ ዜግነቷን ያሳጣታል። ይህ የሚሆነው ባሏ ዜግነት ባለው መንግሥት ህግ መሠረት የባሏን ዜግነት የምታገኝ ሲሆን ነው። የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነች ሴት የኢትዮጵያን ዜግነት ማጣቷ ወይም ይዛ መቆየቷ የሚከሰተው የሴትዮዋ ስምምነት ግምት ውስጥ ሳይገባ ነው።

በአንቀጽ 2 መሠረት አንዲት የውጭ አገር ዜጋ የሆነች ሴት የኢትዮጵያን ዜግነት የምታገኘው እንዲሁም በአንቀጽ 4 መሠረት አንዲት የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነች ሴት የኢትዮጵያን ዜግነት የምታጣው ከጋብቻው አስቀድሞም ሆነ በኋላ ስለሁኔታው በይፋ ከማስታወቋ ወይም ስምምነቷን ከመግለጿ ጋር በተያያዘ ምክንያት አይደለም። ስለዚህ በኢትዮጵያ ህግ ያገቡ ሴቶች የኢትዮጵያን ዜግነት ማግኘትና ማጣት የጋብቻ ቀጥተኛ ውጤት ሆኖ ይቆጠራል።

በዚህም ምክንያት የአውራጃው ፍ/ቤትም ሆነ የዐቃቤ ህግ ጽ/ቤት የአቤት ባይን ዜግነት ለመወሰን የጾታዎችን እኩልነት መርህ ሥራ ላይ ያዋሉት በተሳሳተ መንገድ ነው። ምክንያቱም የ1930ውን የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ያወጣው ህግ አውጭ የደነገገው ስለቤተሰብ አንድነት መርህ በመሆኑ ነው። የጾታዎች እኩልነት ለአገቡ ሴቶች የዜግነት ህግ መርህ ሆኖ ማገልገል የጀመረው በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሲሆን መርሁ ራሱ ገና በመዳበር ላይ የሚገኝ ነው። በሌላ በኩል፥ የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ያገቡ ሴቶችን ዜግነት በሚመለከት የሴትየዋ ዜግነት የባልየውን ዜግነት ይከተላል የሚለውን አርጌውን መርህ ያቀፈ በመሆኑ ከአዲሱ መርህ ወደኋላ የቀረ ነው።

አሁን ፀንቶ ባለው ህግ ላይ ተመስርተንስንናገር የአውራጃው ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጠው ውሣኔ በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንቀጽ 2 ላይ የተመሠረተ አይደለም። ባዕድ ለሆነችው ሴት የራሷን ዜግነት የመምረጥ ነፃነት በሚሰጣት ልምድ የተለየ መርህ ላይ በቆመና ፍጹም አዲስ በሆነ ህግ ላይ የተመሠረተ ነው። ፋኛ በሠራው አዲስ ህግ ላይ የተመሠረተ ነው።

በኮመን ሎው ሥርዓትና በሲቪል ሎው ሥርዓት እንደሚደረገው ሁሉ የኢትዮጵያ ዳኛም ህግ አውጭው ለጉዳዩ አግባብ የሆነውን ህግ ሲያወጣ አስቀድሞ ማየት ከተሳነው ሁኔታዎች ጋር ለማስማማት በአዋጅ የወጣውን ህግ በአተረጓጎም የማብራራትና የማዳበር ሚና እንዳለው ይህ ፀሐፊ ይገነዘባል። ሆኖም ዳኛው የህጉን ዕድገት ሲያበረታታ በዳኝነት ሥራው ክልል ውስጥ መወሰን አለበት።

ዳኛው መከተል ያለበት የመጀመሪያው መርህ ዳኛ ህጉን እንዳገኘው ሥራ ላይ ማዋል አለበት የሚለውን መርህ ነው። ዳኛው የህጉን ትርጉም ማግኘት እንጅ ህጉ መሆን ያለበትን አስቀድሞ መገመት አይገባውም። ከዚህ ጋር በተያያዘ የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አርጌ ዕንስ ሀሳብ ላይ የተመሠረተ ህግ መሆኑን መቀበል አማራጭ የለውም።

ይህም ቢሆን ግን ዳኛው ማድረግ የሚችለው ህጉን እንዳገኘው ሥራ ላይ ማዋል ብቻ ነው። ህጉ እንዲጠብቃቸው የወጣበትን ዓላማዎች በመቃወም ብቻ ዳኛው ህጉን ወደጎን መተው አይችልም። ህጉን በሚተረጉምበት ጊዜም ድንጋጌዎቹ መታየት ያለባቸው ህግ አውጭው በአሰበውና በፈለገው መሠረት መሆን አለበት የሚለውን መርህ በሚገባ መገንዘብ አለበት። እንዲሁም ከራሱ ከህጉ መንፈስ ውጭ የሆነን ነገር የህግ አውጭው ፍላጎትና ሃሳብ ማድረግ እንደማይችል መገንዘብ አለበት። "ህግ አውጭው የአሰበውን ነገር በትክክል መግለጽ አልቻለም የሚያሰኝ በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር የፍቤ/ቱ ኃላፊነት በህጉ ላይ ምንም ነገር መጨመር ወይም ከህጉ ላይ መቀነስ አይደለም።[95] በዚህ ጉዳይ የ1930ው የኢትዮጵያ ህግ አውጭ አዲሱን ዓይነት ህግ ለመደንገግ ፈልጎ ሳይሳካለት ቀርቷል ለማለት አይቻልም።

የዳኝነት ሥራን ሰበብ በማድረግ ፍ/ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ አዲስ ህግ ይዞ የሚወጣ ከሆነ የእኛን የህግ ሥርዓት በሚመለከት የህጉ ነገር ያበቃለታል። ምክንያቱም ህግ የማውጣት ተግባር ህግ የሚፈልገውን ነገር ለህብረተሰቡ የማመልከት ውጤት ስለአለው ነው።

ህብረተሰቡ የዕለት ተዕለት ተግባሩን የሚያካሂደው የወጣው ህግ ከሚፈልገው ሁኔታ ጋር ራሱን በማስማማት ነው። የፍ/ቤቱን ውሳኔ መገመት የማይቻል ከሆነ ህጉ የሚፈልገውን ነገር መፍጠሩና ለህብረተሰቡ ማመልከቱ ይቀራል። ስለዚህም ከዋና ዋና ዓላማዎቹ አንዱን ማስገኘት ይሳነዋል። ፍርድ ቤቱ የሕጉን መሠረታዊ ባህርይና ዓላማ መገንዘብ አለበት፤ ምክንያቱም "በአዋጅ የሚወጣ ህግ የህግ አውጭው ሃሳብና ፍላጎት ውጤት ስለሆነ ነው።[96]

ያገቡ ሴቶችን ዜግነት የሚመለከቱት የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ድንጋጌዎች የጾታዎች እኩልነት ለተረጋገጠበት ለአሁኑ ዘመን ኋላ ቀር በሆኑ ጽንሰ ሃሳቦች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ቢቻል ያገቡ ሴቶችን ዜግነት በሚመለከት በ1957 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት ካወጣው ስምምነት ጋር በሚያጣጥማቸው ሁኔታ እንደገና መጠናት ያስፈልጋቸዋል። ፀሐፊው በህጉ ላይ የሚደረጉ ለውጦች በዳኝነት ውሳኔ ሳይሆን በመደበኛው የህግ አወጣጥ ሂደት ቢደረጉ የኢትዮጵያን የህግ ሥርዓት ይጠቅማል ብሎ ያምናል።

ማስታወሻዎች

1. ከሣሽ ስዚትላና ማማዶቫ፤ ተከሣሽ የአሜሪካን ኮሚዩኒቲ ት/ቤት፣ አዲስ አበባ አውራጃ ፍርድ ቤት፣ የሥራ ክርክር ችሎት፣ የፍትሐብሄር መዝገብ ቁጥር 1272/77፤ በተጨማሪ ሕጋዊነት፣ ቮልዩም 1፣/የኢትዮጵያ ዐቃቤ ህግ ጽ/ቤት፣ ሚያዝያ 1989/ ገጽ 63ና የሚከተሉትን ይመልከቱ።

2. ክሊቭ ፓሪ፣ "ፐሉረል ናሽናሊቲ ኤንድ ሲትዝንሽፕ ዊዝ ስፔሻል ሬፈረንስ ቱ ዘኮመን ዌልዝ"፣ ብሪቲሽ ይር ቡክ ኦቭ ኢንተርናሽናል ሎው፣ ቮልዩም 30/1953፣ ገጽ 244።

3. ዣን ፓንሁይስ፣ <u>ዘ ሮል ኦቭ ናሽናሊቲ ኢን ኢንተርናሽናል ሎው</u> /ሌይደን፣ ኤ.ዳብሊው ሲትሆፍ፣ 1959/ ገጽ 150።

4. ክሊቭ ፓሪ፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ 249።

5. ከታች በማስታወሻ ቁጥር 59ና 60 የተጠቀሱትን ይመልከቱ።

6. ለዚህ ነጥብ ጠለቅ ያለ ውይይት፣ ቢሩ ቢክኔል፣ ዘ ናሽናሊቲ ኦቭ ሜሪድ ውሜን"፣ <u>ትራንዛክሽንስ ኦቭ ዘ ግሮቲየስ ሶሳይቲ</u>፣ ቮልዩም 20 ገጽ 118 - 211 ይመልከቱ።

7. ለምሳሌ፣ ከ <u>ናሽናሊቲ ኦቭ ሜሪድ ወሜን /ሪፖርት ኦቭ ዘ ሴክሬታሪ ጀኔራል/</u>- ዩናይትድ ኔሽንስ፣ ኒውዮርክ፣ 1963 ጋር ተያይዞ ያለውን <u>ዘ ሰርቬይ ኦቭ ናሽናሊቲ ሎውዝ</u>፤ በተጨማሪም ከታች በማስታወሻ ቁጥር 32 በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ የተጠቃለሉትን የዜግነት ህጎች ይመልከቱ።

8. አር ኤስ ፍሬዘር፣ "ኤክስፓትሪሽን አዝ ፕራክቲስድ ኢን ግሬት ብርቴይን" <u>ትራንዛክሽንዝ ኦቭ ዘ ግሮትዩስ ሶሳይቲ</u>፣ ቮልዩም 16፣ ገጽ 78 ።

9. በዚያው ጽሁፍ፣ ገጽ 74 ።

10. ጂ ሻን ግልሐን፣ <u>ሎው አመንግ ኔሽንስ አን ኢንትሮዳክሽን ቱ ፓብሊክ ኢንተርናሽናል ሎው</u> /ዘ ማክሚላን ኮምፓኒ፣ 1972/ ገጽ 104 <u>ኮርፐስ ጁሪስ ሰከንደም</u>፣ ገፅ 1138።

11. <u>ኮርንፐስ ጁሪስ ሰከንደም</u>፣ ገፅ 1138።

12. ኢዩ ሊወሊን፣ "ዘ ናሽናልቲ እቭ ሚሪድ ውሜን"፣ ትራንዛክሽንዝ እቭ ዘ ግሮቲዩስ ሶሳይቲ፣ ቮልዩም 15፣ ገጽ 122።

13. እዚያው በታ።

14. በዚያው ጽሁፍ ገጽ 123።

15. እዚያው በታ።

16. በዚሁ ጽሁፍ፣ ገጽ 122።

17. እዚያው በታ።

18. ኮርፐስ ጁሪስ ሰከንዳም፣ ገጽ 1139፣ በተጨማሪም ፋሲል ናሆም፣ "/ኢትዮጵያን/ ናሽናልቲ ሎው ኤንድ ፕራክቲስ"፣ ገፅ 1 /ያልታተመ/፣ ህግ ቤተ መፃህፍት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ። ህጋዊነት፣ ገፅ 64፣ 68ን ይመልከቱ።

19. ኮርፐስ ጁሪስ ሰከንዳም፣ ገጽ 1138።

20. ሃርቫርድ ሎው ሪቪው፣ ቮልዩም 50፣ ገጽ 831።

21. ኮርፐስ ጁሪስ ሰከንዳም ገጽ 1138።

22. "ዴቨሎፕመንት ኢን ዘ ሎው፤ ኢሚግሬሽን ኤንድ ናሽናልቲ"፣ ሃርቫርድ ሎው ሪቪው፣ ቮልዩም 34፣ገጽ 867።

23. ሃርቫርድ ሎው ርቪው፥ ቮልዩም 63፥ ገጽ 886።

24. ፓል ዌስ፥ ናሽናሊቲ ኢንድ ስቴትለስነስ፥ የ2ኛ እትም /1979/ ፓሲም፤ ቶሲል ናሆም፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ቻርት።

25. ኮርፐስ ጁሪስ ሰከንዳም፥ ገጽ 1138፤ ፓል ዌስ፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ ገጽ 3ና የሚከተሉትን ይመልከቱ።

26. ለምሳሌ፥ ሃርቫርድ ሎው ርቪው፥ ቮልዩም 50፥ ገጽ 83 ይመልከቱ።

27. ኤፍ ሌውሊን፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 106ና የሚከተሉትን ይመልከቱ።

28. ሌውሊን፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 134 ውስጥ እንደተጠቀሰው።

29. ክሊቭ ፓሪ፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 254።

30. ቢክኔል፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 12፤ በተጨማሪም ሺ ጄ ቫሶቭ፥ ሲትዝንሽፕ ኦቭ ዘ ዩ ኤስ ኤስ አር፥ ፐርጋሞን ፐብሊሸርስ፥ ሞስኮ፥ 1979፥ ገጽ 82።

31. ዘ ኮሌክሽን ኦቭ ናሽናሊቲ ሎወዝ ኦቭ ቫሪየስ ካንትሪስ አዝ ኮንቴይንድ ኢን ኮንስቲቲዩሽንስ፥ ስታቲዩትስ ኤንድ ትሪቲስ። /ሪቻርድ ዳብሊው ፍሎርኖይ፥ ጁ አር ና ማንሌይ ኦ ሐድሰን/፥ ኒውዮርክ፥ 1929፥ ገጽ 608።

32. ቢክኔል፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 112፤ ሌውሊን ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 121ና በሚከተሉት።

33. ሌውሊን፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 125።

34. በዚያው ጽሁፍ፥ ገጽ 127።

35. ሌግ ኦቭ ኔሽንስ ትሬቲ ሲሪስ፥ ቮልዩም 179፥ ገጽ 89።

36. ኮንቬንሽን ኦን ዘ ናሽናሊቲ ኦቭ ማሪድ ውሜን፥ ሂስቶሪካል ባክግራውንድ ኤንድ ኮመንታሪ፥ ዩናይትድ ኔሽንስ፥ ኒውዮርክ፥ 1962፥ ገጽ 9።

37. ይኸው ጽሁፍ፥ ገጽ 11።

38. ይኸው ጽሁፍ ገጽ 7፥ በተጨማሪም ቤከኔል፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 113 ።

39. ኮንቬንሽን ኦን ዘ ናሽናሊቲ ኦፍ ማሪድ ውሜን ...፥ ገጽ 11።

40. ይኸው ጽሁፍ፥ ገጽ 12።

41. ቤዚክ ዶኪዩመንትስ ኢን ኢንተርናሽናል ሎው /ሕትመት ኢያን ካርውሊን፥ 3ኛ ሕትመት/ ክላሬዶን ፕሬስ፥ ኦክስፎርድ፥ 1984 ገጽ 2 ና በሚከተሉት።

42. ይኸው ጽሁፍ፥ 251ና በሚከተሉት።

43. ኮንቬንሽን ኦን ዘ ናሽናሊቲ ኦቭ ማሪድ ወሜን ...፥ ገጽ 17።

44. ዮናይትድ ኔሽንስ ትሪቲ ሲሪስ፣ ቮልዩም 309፣ /1958/ ገጽ 68ና የሚከተሉት።

45. ሺ. ሺ.ቫሶቫ፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ 105።

46. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 8 ውስጥ የተጠቀሰውን ይመልከቱ።

47. ኮንቬንሽን ኦን ዘ ናሽናስቲ ኦቭ ሜሪድ ውሜን ...፣ አኔክስ።

48. እዚያው።

49. እዚያው፣ በተጨማሪም ቢክኔል፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 112-3።

50. ፍሬዘር፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 85 ውስጥ እንደተጠቀሰው።

51. ቢክኒል፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥሪ፣ ገጽ 114፤ ሊውሌን ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 115፤ ከሌክሽን ኦቭ ናሽናልቲ ሎውዝ ፣ ገጽ 306።

52. ፍሬዘር፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 85፤ ጆሴፍ ኤል ከንፍ፣ "ዘ ኖትቦም ጃጅመንት፣" አሜሪካን ጆርናል ኦቭ ኢንተርናሽናል ሎው፣ ቮልዩም 54 /1960/፣ ገጽ 543፣ 553።

53. "ሎው ኦቭ ዘ ዩኒየን ኦቭ ሶሻሊስት ሪፐብሊክስ ኦን ሲትዚንሽፕ ኦቭ ዘ ዩ ኤስ ኤስ አር፣ ዲሴምበር 1፣ 1978"፣ ሌጅስሌቲቭ አክትስ ኦቭ ዘ ዩ ኤስ ኤስ አር፣ 1977-1979፣ ፕሮግረስ ፐብሊሸርስ፣ ሞስኮ፣ ገጽ 353ና በሚከተሉት።

54. በዚህ ነጥብ ላይ የአለም የሕግ አዋቂዎች የተለያየ አመለካከት አላቸው። ለዚህ ጽሁፍ የሚያገለግለን ግን ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 42 ውስጥ በተጠቀሰው

ቤዚክ ዶክመንት ውስጥ በስታቲዩት ኦቭ ኢንተርናሽናል ኮርት ኦቭ ጀስቲስ አንቀፅ 34 እንደተሰጠው "ፍርድ ቤት ፊት ከሣሽ ወይም ተከሳሽ ሆነው የሚቀርቡት መንግሥታት ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ"፣ በተጨማሪም ዳንኤል ቲ መርፊ፣ "ዘ ሪስቴትመንት /ተርድስ/ ኦቭ ሂዩማን ራይትስ ፕሮቪዥንዝ፣ ናቲንግ ኒው፣ ባትቬሪ ዌልካም "፣ ዘ ኢንተርናሽናል ሎውየር፣ ቮልዩም 24/1990/ና የሚከተሉትን ይመልከቱ።

55. ለምሳሌ፣ ሾብሶቭ፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 21 ይመልከቱ።

56. አንዳንድ የሕግ አዋቂዎች መንግሥታት ብሄርቻቸውን በመወከል አለም አቀፋዊ ጥያቄዎችን የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው ይናገራሉ። ለምሳሌ ዳብሊው አር ቢሾፕ፣ "ናሽናልቲ ኢን ኢንተርናሽናል ሎው"፣ አሜሪካን ጆርናል ኦቭ ኢንተርናሽናል ሎው፣ ቮልዩም 57 /1943/ ገጽ 323፤ ሾቭሶቭ፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 31ና የሚከተሉትን ይመልከቱ።

57. የቱኒስና ሞሪኮ ናሽናልቲ አዋጅ ክስ፣ ፐርማነንት ኮርት ኦቭ ኢንተርናሽናል ጀስቲስ ሪፖርትስ ሲሪስ ቢ፣ ቁጥር 4፣ ገጽ 24። ዘ ኖትቦም ኬዝ፣ ኢንተርናሽናል ኮርት ኦቭ ጀስቲስ ሪፖርት፣ ገጽ 1955።

58. ሊግ ኦቭ ኔሽንስ ትሪቲ ሲሪስ፣ ቮልዩም 179፣ ገጽ 29፣ አንቀጽ 1።

59. ቫን ፓንሁይስ፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ 55፣ 150 ፓሲም፤ ከንዝ፣ በተጠቀሰው ጽሁፍ፣ ገጽ 545።

60. ማክማሃን ከዜር፣ "ሳብጀክት ሲቲዝን" ናሽናል ኤንድ ፐርማነንት አለጂያንስ"፣ የል ሎው ጆርናል፣ ቮልዩም 56 /1946-7/፣ ገጽ 70።

61. ኤፍ ኤ ማን፣ ሬኩዊደ ኮር፣ ቮልዩም 111/1964/፣ ገጽ 9ና በሚከተሉት፤ ኢያን ብርውንሊ፣"ፐብሊክ ኢተንተርናሽናል ሎው"፣ ብሪቲሽ ይርቡክ ኦቭ ኢንተርናሽናል ሎው፣ ቮልዩም 39/1965፣ ገጽ 432/3።

62. አር ኢ ሴድለር፣ ዘ ኮንፍሊክት ኦቭ ሎውዝ ኢን ኢትዮጵያ፣ የሕግ ፋኩልቲ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፣ 1965፣ ገጽ 6። በተጨማሪም ሾቭሶቭ፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ 49 ላይ እንደሚለው፣ "አንዱ የመንግሥት ሉአላዊነት መሰረታዊ ክፍል /ዜግነትን በሚመለከት ያለ ነፃነት/ ማንኛውም ሉአላዊ መንግሥት ዜጎቹን የሚመለከቱ ማናቸውንም ነገሮች ከማንኛውም ዓይነት የውጭም ሆነ የውስጥ ባለሥልጣን ነፃ ሆኖ ራሱ ይቆጣጠራል" የሚለውን እውነታ ከሁሉም በላይ ይገልጣል።

63. ዘ ሎው ኦቭ ዘ ዩኒዩን ኦቭ ሶቭየት ሶሻሊስት ሪፐብሊክስ ኦን ሲትዝንሽፕ አንቀጽ 4 ዲሴምበር 1፣ 1978 ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 54 እንደተጠቀሰው፣ በዚህም መሠረት ጋብቻ በተጋቢዎች ዜግነት ላይ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ የለውም። በ1930ው የኢትዮጵያ ዜግነት ሕግ መሠረት ግን ጋብቻ ለሚስት የባልየውን ዜግነት ያስገኛል።

64. ዮናይትድ ኔሽንስ ትሪቲ ሲሪስ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 44 እንደተገለፀው።

65. በዚሁ ሥራ።

66. ፍሬዘር፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ገፅ 82።

67. እዚያው።

68. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 57 የተጠቀሰውን ይመልከቱ።

69. ኢንተርናሽናል ኮርት ኦቭ ጄስቲስ ሪፖርት፣ 1965፣ ገጽ 22-23።

70. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 60 የተገለፀውን ይመልከቱ።

71. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 57 የተጠቀሰውን ይመልከቱ።

72. ቢስኮፕ፥ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፥ ገጽ 321።

73. በዚያው ጽሁፍ ገጽ 324።

74. ከንዝ፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ገጽ 563-4።

75. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 53 የተጠቀሰውን ይመልከቱ።

76. ኮንቬንሽን ኦን ዘ ናሽናሊቲ ኦቭ ሜሪድ ውሜን ... አኔክስ።

77. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 54 የተጠቀሰውን ይመልከቱ።

78. ለምሳሌ ከንዝ፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 546፥ ቫን ፓንሁይስ፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ በየቦታው፤ ኮስሌር፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 48።

79. ሄንሪች ሾሌር፥ ዘ ስፔሻል ኮርት ኦቭ ኢትዮጵያ፥ 1920-1935፥ ስቱትጋርት፥ 1985 ገጽ 48።

80. በዚሁ ጽሁፍ፥ ገጽ 45።

81. እዚያው በታ።

82. እዚያው በታ።

83. እዚያው በታ።

84. እዚያው ቦታ።

85. ኮሌክሽን ኦቭ ናሽናል ሎውዝ ... ገጽ 245።

86. በዚሁ ጽሁፍ፣ ገጽ 608።

87. በዚሁ ጽሁፍ፣ ገጽ 29፣ 363፣ 316።

88. ጀምስ ሲ ኤን ፓል እና ክርስቶፈር ክላፋም፣ ኢትዮጵያን ኮንስቲቲዩሽናል ዲቨሎፕመንት፤ ኤ ሶርስ ቡክ፣ የሕግ ፋኩልቲ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፣ 1ኛ ቮልዩም ገጽ 336።

89. ኮሌክሽንስ ኦቭ ናሽናል ሎውዝ ...፣ ገጽ 382።

90. ሻን ፓንሁይስ፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ 161።

91. ለምሳሌ፣ ሌውሊን፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ 133፤ ቢክኔል፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ113፣ ኮንቬንሽን ኦን ዘ ናሽናሰቲ ኦቭ ሜሪድ ውሜን፤ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 32 የተጠቀሰው፤ ኮሌክሽን ኦቭ ናሽናል ሎውዝ ፣ ፓሲም ይመልከቱ።

92. የተጠቃለሉ የኢትዮጵያ ሕጎች፣ 6ኛ ቮልዩም፣ በተጨማሪም ባላምባራስ ማህተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ዝክረ ነገር፣ 1939፣ ገጽ 183ና የሚከተሉትን /በአማርኛ የተፃፈ/ ውስጥ ይመልከቱ፤ ኤን ግሬይን፣ ዘ ኢትዮጵያን ኢምፓየር ፌደሬሽን ኤንድ ሎውዝ፣ ሆተርዳም፣ 1954፣ ገጽ 61ና በሚከተሉት/በእንግሊዝኛ የተፃፈ/ የ1930ው የኢትዮጵጵያ የዜግነት ሕግ ከጣሊያን ወረራ በፊትና የ1931ዱ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሕገ መንግሥት ተፅፎ ከመውጣቱ ከአንድ ዓመት በፊት ከወጡት ሕጎች አንዱ ነው።

93. ሲ ኬ አላን፣ ሎው ኢን ዘ ሜኪንግ፣ ኦክስፎርድ፣ /7ኛ ሕትመት/፣ 1964፣ ገጽ 491።

94. ኤም ፋራኒ፣ ዘ ኢንተርፕርቴሽን አቭ ስታቲዩትስ፣ ላሆር ሎው ታይምስ ፓብሊኬሽንስ፣ 1970፣ ገጽ 33።

95. በዚሁ ጽሁፍ ገጽ 107።

96. አለን፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 427።

<u>የኢትዮጵያ አበይት የገቢ ግብር ሕግጋት</u>
<u>ዋና ዋና ገጽታዎች</u>[1]

በቀለ ኃይለሥላሴ*

1. <u>መግቢያ</u>

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ሦስት የገቢ ግብር አዋጆች ሥራ ላይ ውለው ይገኛሉ። እነዚህም፥

1. ተፈፃሚነቱ ከንዳጅ ሥራዎች በሚገኝ ገቢ ላይ የሆነው አዋጅ ቁጥር 296/1979

2. ተፈፃሚነቱ ከግብርና ሥራዎች የሚገኘውን ገቢ የሚመለከተው አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ እና

3. ከንዳጅና ከግብርና ሥራዎች የሚገኘውን ገቢ ሳይጨምር ተፈፃሚነቱ ከማናቸውም ሌሎች ምንጮች በሚገኙ ገቢዎች ላይ የሆነው አዋጅ ቁጥር 173/1953 እንደተሻሻለው ናቸው።

ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ሦስት ሕግጋት መካከል በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ስለመጀመሪያው ምንም የተነገረ ነገር የለም። ይህ የሆነበት ምክንያት በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዳጅ ለገበያ በሚቀርብበት መጠን ገና መመረት ባለመጀመሩ አዋጁ ሥራ ላይ ሊውል ስላልቻለ ነው።

* ሌክቸረር፥ ሕግ ፋኩልቲ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የዚህ ጽሁፍ ዋና ትኩረት የኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሥርዓትን በአጠቃላይ መልኩ ለአካባቢ ማስታዋወቅ ነው። በዚህም መሠረት ዓበይት የሆኑትን የገቢ ግብር ሕግጋት ዋና ዋና ገጽታዎች ያብራራል።

ጽሁፉ "ገቢ" ለሚለው ቃል በህግ የተሰጠውን ትርጓሜ በመግለጽ ጀምሮ፣ የገቢ ግብር ህግጋት የሚመለከቱት እነ ማንን ነው? ዋና ዋና ገጿታዎቻቸውስ ምንድን ናቸው? የገቢ ግብር አሰባሰብና አወሳሰን እንዴት ይከናወናል? የግብር ገጿታዎች መከበራቸውን አስተማማኝ ለማድረግ ሊወሰዱ የሚችሉት እርምጃዎች ምንድን ናቸው? ግብር ከፋዮች በሚወሰንባቸው ግብር ቅር ሲሰኙ ምን ማድረግ ይችላሉ? በገቢ ግብር ሕግጋት ውስጥ ከግብር ነፃ የመሆን መብት ለነማን ተሰጥቷል? ለሚሉትና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራል። የጽሁፉ መደምደሚያ አንዳንድ በአፈጻጸም ላይ ፋይዳ ያላቸውን የተመረጡ ጥያቄዎችን ያነሣል። በዚህም ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባል። ይህ ጽሁፍ ወደፊት በርዕስ ጉዳዩ ላይ ለሚደረጉ ጥናቶችና ምርምሮች መነሻ ሆኖ እንደሚያገለግል ተስፋ ይደረጋል።

2. <u>የገቢ ሕገ ባህርያት</u>

ገቢ ለሚለው ቃል ትርጓሜ ለመስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ስለጉዳዩ በቀረቡ በርካታ ጽሁፎችና ጥናቶች በተደጋጋሚ የተገለጸ ነገር ነው። ብዙውን ጊዜ የተለያዩ የምርምር መስኮች ምሁራንና ጠበብት ዝንባሌ ለዚህ ቃል ከየራሣቸው ሙያ አንፃር ትርጉም የመስጠት በመሆኑ ለቃሉ ሁሉም የሚስማሙበት ትርጉም ማግኘት ቀላል አይደለም። ስለዚህ የገቢ ግብርን ሥራ ላይ ለማዋል ሲባል ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ችግር ለማስወገድ ለቃሉ ሕጋዊ ትርጉም መስጠት የተለመደ ሆኗል።

የኢትዮጵያ ሕግ "ገቢ" ለሚለው ቃል የሰጠው ትርጉም በአገር ውስጥ ከሚገኙ ምንጮች እስከተገኙ ድረስ፣ ተቀባዩ የሚገኝበት ቦታ ግምት ውስጥ ሣይገባ፣ ማናቸውንም የገንዘብ ክፍያዎችና በዓይነት የሆኑ ጥቅሞች ሁሉ ያጠቃልላል።[2]

በዚህም የተነሣ ከኢትዮጵያ ውጭ ካሉ ምንጮች የሚገኙ የገንዘብ ክፍያዎችንና በዓይነት የሆኑ ጥቅሞችን ገቢ አድርጎ መውሰድ እንደ ልዩ ሁኔታ የሚቆጠር ነው።[3]

"ምንጭ" ለሚለው ቃል ሕጉ የሰጠው ሌላ አቻ "የሥራ እንቅስቃሴ" የሚለው ሐረግ ነው። "የሥራ እንቅስቃሴ" ትጥርን፥ የሙያና የዝንባሌ ሥራዎችን፥ የግብርና ሥራዎችንና ማናቸውንም ዓይነት የንግድ ሥራን ይጨምራል። ስለዚህ በመሠረቱ "ገቢ" የሚለው ቃል ከሥራ እንቅስቃሴ ለሚገኙ የገንዘብ ክፍያዎችና የዓይነት ጥቅሞች አግባብነት አለው። እንዲሁም ከመሠረተ ሀሳቡ በተለየ ሁኔታ ከአክሲዮን ባለመብትነት የሚገኙ የትርፍ ክፍያዎች፥ በግኝትና በኪነጥበብ ላይ ካሉ መብቶች የሚገኙ የገንዘብ ጥቅሞች /royalties/ እንደ ሎተሪ ባሉ በዕድል የሚገኙ ሽልማቶች በገቢ ክልል ውስጥ ይወድቃሉ።[5]

በተለምዶ አነጋገር እንደነገሩ አገባብ አንድ ሰው የሚከፈለው ወይም የሚያገኘው ገንዘብ የተለያየ መጠሪያ ሊኖረው ይችላል። ለምሣሌ ደሞዝ፥ ምንዳ፥ ጉርሻ፥ ዓበል፥ ወለድ፥ ትርፍ፥ ወዘተ ...። በዓይነት የሚሰጥ ወይም የሚገኙ ጥቅሞች እንዲሁ የንግድ ዋጋ ባላቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች መልክ የሚሰጡ ሊሆኑ ይችላል። የሆነ ሆኖ በአገላለፅና በስያሜ ረገድ ያለው ይህ ልዩነት ለሕጉ የገቢ ትርጓሜ ምንም አግባብነት የለውም። ስለዚህ በመሠረቱ በሕግ ነፃ ካልተደረጉ በስተቀር በሁሉም ግብር ይከፈልባቸዋል።[6]

3. <u>የገቢ ግብር የሚመለከታቸው፥</u>

ሐረጉ እንዲያመለክት የታቀደው ግብር የመክፈል ግዴታ ያለባቸውን ብቻ ሣይሆን በግብር አሰባሰብ ሥራ የግብር አሸጋጋሪ የሆኑትን ጭምር ነው። በአጠቃላይ አነጋገር ግብር የሚጣልበትን ገቢ የሚከፍሉ ወይም የሚቀበሉ ሰዎችና ድርጅቶች የገቢ ግብር የሚመለከታቸው ሲሆን እነዚህም በቀጥታ ግብር የመክፈል ግዴታ ያለባቸው ወይም በግብር አሰባሰብ ሥራ የግብር አሸጋጋሪ የሆነ ወይም ሁለቱንም ባህርያት የያዙ ሊሆኑ ይችላሉ።

"ሰው" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተተማሪ፣ ነጋዴ፣ የሥራ ተቋራጭ፣ ገበሬ፣ የሥነ ጽሁፍ ደራሲ፣ የሙዚቃ ደራሲ፣ የዕድል አሸናፊ፣ ባለአክሲዮን ወዘተ በመሆን ገቢ የሚያገኙትን ግለሰቦች ነው።[7] "ድርጅት" ማለት እንደ መንግሥት እርሻ፣ የጋራ የንግድ ማኅበር፣ ኮርፖሬሽን፣ የአክሲዮን ማኅበር፣ ያሉትን በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸውን የንግድ ሥራ የሚሠሩ የመንግሥትና የግል አካላትን የሚጨምር ነው።[8]

የገቢ ግብር የሚመለከታቸው ሁሉ ሁለት መሠረታዊ ግዴታዎችን መፈጸም አለባቸው። እነዚህም ገቢን ማሳወቅና ግብርን መክፈል ናቸው። የገቢ ግብር ከሚመለከታቸው መካከል የተወሰኑት ሌላ ተጨማሪ ግዴታ አለባቸው። ይኸውም የሂሣብ መዛግብትንና ደጋፊ ሰነዶችን መያዝ ነው።[9]

4. <u>የግብር አሰባሰብ ስልቶች፣</u>

ገቢን የማሳወቅና ግብርን የመክፈል ግዴታዎች የተጣሉት የግብር አሰባሰብን አስተማማኝ ለማድረግ መሆኑ ግልጽ ነው። ለዚህም ግብርን ከሌሎች ገቢ ላይ በመቀነስ ይዞ የማስተላለፍ ስልትና ስለራስ ገቢ መግለጫ የማቅረብ ስልት ሥራ ላይ ውለው ይገኛሉ።

ግብርን ከሌሎች ገቢ ላይ በመቀነስ ይዞ የማስተላለፍ ስልት ተፈጻሚ የሚሆነው ከቅጥር፣ ባለአክሲዮን ከመሆን፣ ከዕድል አሸናፊነትና የግኝትና የድርሰት መብቶች ከመጠቀም ገቢ በሚገኝበት ሁኔታ ላይ ነው። በተጨማሪ ከአገር ውጭ ሰተሰጠ አገልግሎት ክፍያ በሚደረግበትም ሁኔታ ላይ ተፈጻሚነት አለው። በነዚህ ሁኔታዎች አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት ለሌላ ገቢ በሚከፍልበት ጊዜ በግብር አሰባሰብ ሥራ የግብር አሸጋጋሪ ይሆናል። ምክንያቱም ክፍያውን በፈጸመ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን የከፈለውን ገቢ እንዲያስታውቅና ግብሩን እንዲያስተላልፍ በሕግ ስለሚገደድ ነው። በዚህም የተነሳ እንዲህ ያለው ግለሰብ ወይም ድርጅት ከሚከፍለው ገቢ ላይ ግብሩን ቀንሶ እንዲይዝ በሕግ ሥልጣን ተሰጥቶታል።[10]

ይህ ሥልት ሥራ ላይ የሚውልበት ሌላው ሁኔታ ለገንዘብ አበዳሪ ድርጅቶች በአበደሩት ገንዘብ ላይ ከሚከፈለው ወለድ ጋር የተያያዘ ነው። በእንዲህ ያለ ሁኔታ ተበዳሪው ግለሰብ ወይም ድርጅት ግብር ከፋይ ከሆነ ከራሱ ገቢ ጋር የተያያዙትን የግብር ግዴታዎች በሚያሟላበት ጊዜ የአበዳሪ ድርጅቱን የወለድ ገቢ ለገቢ ግብር ባለሥልጣን የማሳወቅና በዚሁም ገቢ ላይ የሚጣላውን ግብር ራሱ የማድረግ ግዴታ አለበት። ተበዳሪው ግብር ከፋይ ካልሆነ ግን ግዴታው ከኢትዮጵያ የበጀት ዓመት መጨረሻ አንስቶ በአራት ወራት ውስጥ መሟላት አለበት።[11]

ሌሎች ግናቸውንም የገቢ ምንጮች በሚመለከትና በልዩ ሁኔታዎች ትኩርን በሚመለከት ተፈጻሚ የሚሆነው ስለ ራስ ገቢ መግለጫ የማቅረብ ስልት ነው። በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከአንድ በላይ ለሆኑ ቀጣሪዎች የሚሠሩ ተቀጣሪዎች ወይም የውጭ መንግሥትን ዲፕሎማሲያዊ ጥቅም በሚወክሉ አካላት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ግለሰቦች ገቢያቸውን የማሣወቅና ግብሩን በግንባር ቀርበው የመክፈል ግዴታ አለባቸው።[12] በሙያና በዝንባሌ ሥራዎችና በማናቸውም ዓይነት የንግድ ሥራ የተሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች የተመደቡበትን የግብር ከፋዮች ደረጃ መሠረት በማድረግ ከኢትዮጵያ በጀት ዓመት መጨረሻ አንስቶ ከአንድ እስከ አራት ወራት ውስጥ በተወሰነው ጊዜ ገቢያቸውን የማሣወቅና ግብሩን የመክፈል ግዴታ አለባቸው።[13] ንብረትን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከማከራየት ገቢ ሲገኝ ለግብሩ አከፋፈል ከፋዩ ገቢው ከተገኘበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ገቢውን ማሣወቅ አለበት።[14]

ከግብርና ሥራ እንቅስቃሴ የሚገኘን ገቢ በተመለከተ የገበሬ ማህበራት በግብር አሰባሰብ ሂደት ውስጥ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ በሕግ ተደንግጓል። ማህበራቱ በዓመት እስከ ብር 600 በሚደርስ ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ግብሩን የመሰብሰብ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል።[15] በአጠቃላይ ገቢን የማሣወቅና ግብሩን የመክፈል ግዴታ በየዓመቱ ከታህሳስ አንድ ቀን እስከ ሚያዝያ ሰላሳ ቀን ድረስ መሟላት አለበት። ይህም የተደረገው በኢትዮጵያ አዝመራ የሚሰበሰብበትን ወቅት በመከተል ነው።

5. የግብር አወሳሰን፣

የግብር አወሳሰን አንድ የግብር ልክ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ግብር የሚከፈልበት ገቢ ለመለየት የሚደረገው የስሌት ሂደት ነው። ገቢን ለመደበቅ ሲባል በግብር አሰባሰብ ሥራ የግብር አሽጋጋሪ በሆነውና በራሱ በግብር ከፋዩ መካከል መመሳጠር ካልኖረ በስተቀር ከዕድል አሸናፊነት፣ የግኝትና የምርምር። እንዲሁም የሥነ ጽሁፍ ድርሰት መብትን ከመጠቀም ባጠቃላይ ግብርን ከሌሎች ገቢ ላይ በመቀነስ ይዞ የማስተላለፍ ስልት ተፈፃሚ ከሚሆንባቸው ምንጮች ገቢ ሲገኝ የግብር አወሳሰኑ ተግባር አስቸጋሪ አይሆንም። ሌሎች የገቢ ምንጮችን በተለይ ደግሞ የትርፍ ግብር የሚጣልባቸውን ምንጮች በሚመለከት የግብር አወሳሰን ተግባር እንደሚመስለው ቀላል ተግባር አይሆንም።

በኢትዮጵያ የግብር ሥርዓት የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ የሚወሰነው አንድም የሂሣብ መዛግብትንና ደጋፊ ሰነዶችን መሠረት በማድረግ ወይም በግምት ነው። የሂሣብ መዛግብትንና ደጋፊ ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ግብር ከፋዮች ለምርመራ በተጠየቁ ጊዜ መዛግብቱንና ደጋፊ ሰነዶቹን ለገቢ ግብር ባለሥልጣን ማቅረብ አለባቸው።[17] ይህን ካደረጉና የሂሣብ መዛግብቱና ደጋፊ ሰነዶቹ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኙ የሚከፍሉት ግብር ባቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶች መሠረት ይወሰናል።[18] በሌላ በኩል ግብር ከፋዮች የሂሣብ መዛግብትንና ደጋፊ ሰነዶችን ሣያቀርቡ ቢቀሩ ወይም ባለሥልጣኑ በግናቸውም ምክንያት ሰነዶቹን ሣይቀበላቸው ቢቀር የሚከፈለው ግብር የሚወሰነው በግምት ይሆናል። እንዲሁም በሕግ የሂሣብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶች የመያዝ ግዴታ የሌለባቸው ግብር ከፋዮች የሚከፍሉት ግብር የሚወሰነው በግምት ነው።[19]

ብዙውን ጊዜ አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ በሚያገኘው ጠቅላላ ገቢና ግብር በሚከፍልበት ገቢ መሃል ልዩነት ይኖራል። ይህ ልዩነት በተለይ

ገቢ ከቅጥር፣ ከሙያና ከዝንባሌ ሥራዎች፣ ከግብርና ሥራዎችና ከማናቸውም የንግድ ሥራዎች በሚገኝበት ሁኔታ ይታያል። የዚህ ምክንያት ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ከልል ውጭ የሆኑ ጥቅሞችንና መቀነስ የሚገባቸውን ወጭዎችንና ኪሳራዎችን የሚዘረዝሩ የሕግ አንቀጾች መኖር ነው።

በኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሥርዓት ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ከልል ውጭ የሆኑ ጥቅሞች የሚለው አነጋገር የሚያመለክተው ከቅጥር በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ሲወሰን ግብር የማይጣልባቸውን የተወሰኑ ክፍያዎችንና በዓይነት የሚገኙ ጥቅሞችን ነው። በሌላ በኩል "ተቀናሽ ሂሳብ" የሚለው ሐረግ በአንድ የግብር ዘመን ከተገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ የሚቀነሱትን ገቢውን ለመፍጠር በሚደረግ የሥራ ሂደት ውስጥ የተደረጉ ወጭዎችንና የሚደርሱ ኪሳራዎችን ያመለክታል።

በመሠረቱ አንድ ተቀጣሪ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚቀበለው ጠቅላላ ገቢ ግብር ይከፈልበታል።[20] ሆኖም ተቀጣሪውን የሚጠቅሙና ለቀጣሪው ወጪን የሚያስከትሉ አራት ዓይነት ክፍያዎች ተቀጣሪው ግብር የሚከፍልበት ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ከልል ውጭ ሊደረጉ ይችላሉ። እነዚህም የህክምና አገልግሎትን ከሚመለከተው ውጭ በተጨማሪ ቀጣሪው ለተቀጣሪው መጓጓዣንና ትዞን አስመልክቶ የሚያደርጋቸው ክፍያዎች ናቸው።[21]

በትርፍ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት፣ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማግኘት በአንድ የግብር ዘመን ከተገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ ገቢውን በመፍጠር ረገድ የተደረገው ወጭና የደረሰው ኪሳራ ሁሉ ይቀነሳል። ተቀናሽ የሚሆኑና የማይሆኑ የወጭና የኪሳራ ዓይነቶች ዝርዝር በሕጉ ተመልክቷል።[22] ይህ አቀራረብ ተቀናሽ ሂሳቦችን በመለየት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው።

በኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሥርዓት ገቢን ማጣመር ይቻላል። ሆኖም የሚከተለው ጥቅላዊ ዘዴን ሳይሆን ሠንጠረዥያዊ ዘዴን ነው። በኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሥርዓት ውስጥ ሦስት ዋና ዋና ሠንጠረዦች አሉ። እነሱም፣ አንደኛው ከቅጥር የሚገኙትን

ገቢዎች፣ ሁለተኛው ከግብርና ሥራዎች የሚገኙትን ገቢዎች፣ ሦስተኛው ደግሞ ከሌሎች ማናቸውም የንግድ ሥራዎችና ንብረትን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከማከራየት የሚገኘውን ገቢ ጨምሮ ከሙያና ከዝንባሌ ሥራዎች የሚገኙትን ገቢዎች የሚመለከቱ ናቸው።[23] በተለያዩ ሠንጠረዦች ውስጥ ከሚወድቁና ከአንድ በላይ ከሆኑ ምንጮች ገቢዎች በሚገኙበት ጊዜ በጥቅላዊ ዘዴ እንደሚደረገው ግብር የሚከፈልባቸውን ገቢዎች አንድ ላይ መደመርና ግብሩን በድምሩ ላይ ማስላት አይቻልም። ግብር የሚከፈልባቸውን ገቢዎች ማጣመር የሚቻለው ገቢዎቹ የሚገኙበት ምንጭ በአንድ ሠንጠረዥ ውስጥ የሚወድቅ ሲሆንና ገቢዎቹ የተገኙት በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ ሲሆን ብቻ ነው።[24]

ከገቢ ምንጮች አንጻር፣ ማለትም ቅጥርን ብቻ በሚመለከት ገቢውን ለግብር ወቅቶች በማከፋፈል ግብሩ እንዲሰላ በግልጽ የሚደነግግ አንቀጽ አለ። ለምሣሌ አንድ ተቀጣሪ የሦሥት ወር ደሞዙን በአንድ ጊዜ የሚቀበልበት ሁኔታ ቢያጋጥም የሚከፈለው ግብር የሚሰላው በሦሥት ወር ደሞዙ ድምር ላይ አይደለም። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ መጀመሪያ ጠቅላላው ገቢ ገቢው ለተገኘባቸው ወራት ይካፈልና የሚጠየቀው ግብር ይሰላል።[25]

በአጠቃላይ ከግብርና የሚገኘውን ገቢ በሚመለከት የሚጠየቀው ግብር የሚወሰነው ወደፊት ይገኛል ተብሎ የሚገመተውን ገቢ መሠረት በማድረግ ነው። ግብር በግምት ከሚወሰንባቸው መንገዶች አንዱ በሆነው በዚህ ዘዴ ሰብሉን በቆመ በመመልከት አንድ ገበሬ ያገኛል ተብሎ የሚገመተው ገቢ የአወሳሰኑ መሠረት ይሆናል። ሆኖም እንዲህ ዓይነቱ የግብር አወሳሰን የመጨረሻ ላይሆን ይችላል። ከምርቱ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ ይገኛል ተብሎ ከተገመተው ገቢ በታች ለመሆኑ የሚያሣምን ማስረጃ በማቅረብ ግብሩን ማስተካከል ይፈቀዳል።[26]

ግብር በግምት የሚወሰንበት ዘዴ ሥራ ላይ ሲውል ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማግኘት ከጠቅላላ ገቢ ላይ ተቀናሽ የሚሆንና የማይሆን ሂሣብ ብሎ መለየት አስቸጋሪ ሆኖ ይገኛል። ግብር በግምት በሚወሰንበት ጊዜ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ

ለማስላት በሕግ የተፈቀዱትን ግብር የማይከፈልባቸውን ወጪዎችንና ኪሣራዎች በትክክል መለየት እንደማይቻል ግልጽ ነው። በሌላ በኩል የሚከፈለው ግብር በግምት የሚወሰንበት ግብር ከፋይ ሀቱ የፈቀዳቸውን ተቀናሽ ሂሳቦች በሚመለከት ሚዛናዊ አስተያየት ጨርሶ ሊነፈገው አይገባም። ይህ ሁኔታ ከርትዕ ጋር የሚጣጣሙ ውጤቶች የሚያስገኙ ዘዴዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ያስገድዳል። በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ የሥራ ዓይነት ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው የትርፍ መተመኛ የመቶኛ ልኮች አጠቃላይ ደረጃዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ በአስተዳደሩ ተዘጋጅተዋል። ይህም ሲዘጋጅ በሕጉ መሠረት ተቀናሽ የሚሆኑና የማይሆኑ ወጭዎችንና ኪሣራዎችን እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። እያንዳንዱ የትርፍ መተመኛ የመቶኛ ልክ ተፈፃሚ በሚሆንበት የሥራ ዓይነት ላይ የተሠማሩትን ግብር ከፋዮች በሙሉ ይመለከታቸዋል። በመሆኑም ግብር በግምት ሲወሰን አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዘመን ግብር የሚከፍልበት ገቢ በትርፍ መተመኛ መቶኛው ልክ ከጠቅላላው ገቢ ላይ ተሠልቶ የሚገኘው የትርፍ መጠን ነው።

ግብርን በግምት የመወሰን ተግባር በአንድ በኩል አግባብ ያለውና በተግባር ሊገለፅ የሚችል የትርፍ መተመኛ ልክን በአንድ በተወሰነ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ እንዩራዊ ጥናቶችን በማድረግ ለማበጀት በሌላ በኩል አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዘመን ያገኘውን ትርፍ ለመወሰን የሚያስችሉ መረጃዎችን አለመታከት የመሰብሰብ ጥረትን ይጠይቃል። እነዚህ ሁለት የጥረት አቅጣጫዎች ብቁ የሆኑ የምርምር ስልቶችንና አስተማማኝ የሆነ የመረጃ ትንተና ችሎታን ይጠይቃሉ።

የግብር አወሳሰን ተግባር ተፈፃሚ ከሆኑት በህጉ ከተመለከቱት የግብር ልኮች ጋር በሚገባ መተዋወቅን እንደሚሻ ግልጽ ነው። በኢትዮጵያ የገቢ ግብር ህጎች ውስጥ የግብር ልኮች በሦስት መልክ ተቀርጸዋል።

በቀርጥ የተወሰኑት የመቶኛ ልኮች የእርሻ የአምራቾች የህብረት ሥራ ማህበራትን ሳይጨምር የመንግስት እርሻዎችንና የማናቸውንም ድርጅቶች ግብር የሚከፈልባቸውን ገቢዎች ይመለከታሉ። ከጋራ ልማት ማህበራት በስተቀር እንዲሁ

ያሉ ድርጅቶች ግብር ከሚከፈልበት የዓመት ገቢያቸው 50%ውን ግብር ይከፍላሉ።[27] በቁርጥ የተወሰኑት የመቶኛ ልኮች ከድርሰትና ከግኝት መብት በሚገኘው ክፍያ፣ በአክሲዮን ድርሻና በሽልማት ላይ ተፈፃሚነት አላቸው። ልኮቹም እንደቅደም ተከተሉ 40%፣ 10%፣ 10% ናቸው። ሌላው በቁርጥ የተወሰነ የመቶኛ ልክ የሚታየው ከውጭ አገር ለተሰጠ አገልግሎት የሚፈፀመውን ክፍያ በተመለከተ ሲሆን ልኩም 10% ነው።[28]

በቁርጥ የተወሰነ የመጠን ልክ ተፈፃሚነቱ የሚታየው ከግብርና ሥራ በሚገኘው ገቢ ላይ ነው። በእንዲህ ያሉ ሁኔታ ግብር የሚከፈልበት የዓመት ገቢ ከብር 600 ያልበለጠ ሲሆን ብር 10 ግብር ይከፈልበታል።[29]

መቶኛ እርከናዊ ልኮች ከቅጥር የሚገኝን ገቢ በሚመለከት ተፈፃሚ ይሆናሉ። እንዲሁም ከግብርና ሥራ የሚገኘው ዓመታዊ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ከብር 600 በላይ ሲሆንና ከሌሎች የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚገኘው ዓመታዊ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ከብር 300 በላይ ሲሆን ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።[30] የሚከፈለውን ግብር ለመወሰን እያንዳንዱ መቶኛ እርከናዊ ልክ በሚመለከተው ዓመታዊ ግብር የሚከፈልበት ዝቅተኛና ከፍተኛ የገቢ ድንበሮች መካከል ተፈፃሚ ሲሆን ጠቅላላውን ግብር ለማግኘት በየእርከኑ የተገኙት ውጤቶች የሚደመሩ ይሆናል።

በአጠቃላይ አነጋገር ከመደና ከዝንባሌ ሥራዎችና ከሌሎች ማናቸውም የንግድና የግብርና ሥራዎች የሚገኙ ገቢዎችን በሚመለከት ግብር ከፋዩ ገቢውን ካሳወቀበት ጊዜ አንስቶ በአምስት ዓመት ውስጥ የግብር አወሳሰን መፈጸም አለበት። የገቢ ግብር ባለሥልጣን በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ግብሩን ካልወሰነ ገቢያቸውን ያስታወቁ ግብር ከፋዮችን በሚመለከት የመወሰን ሥልጣኑ በይርጋ ይታገዳል።[31] ይሁን እንጂ የይርጋ ገደብ ማናቸውንም የማጭበርበር ሁኔታ የተፈጸመበትን ገቢና ሀብት በተመለከተ ተፈፃሚ አይሆንም።[32]

ግብሩ ከተወሰነ በኋላ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ተብሎ በሚታወቅ ጽሁፍ ላይ ተገልጾ ግብር ከፋዩ እንዲደርሰው ይደረጋል።[33] የውሳኔ ማስታወቂያው ተከፋይ

የሚሆነው ግብር እንዴት እንደተሰላ በግልጽ በሚያሳይበት መንገድ መዘጋጀት ይኖርበታል። እንዲሁም የሚጣሉ መቀጮዎች ካሉ መጠናቸውንና ዓይነታቸውን መዘርዘር አለበት።[34]

6. የግብር ግዴታዎችን በአስተማማኝ ለማስከበር ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎች

ከዚህ ቀደም ሲል የተጠቀሱት ሦስት የገቢ ግብር ዋና ዋና ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል አለመከበራቸው የግብሩ አካል ሆነው የሚጣሉ መቀጮዎችን እንዲያስከትል ተደርጓል።[35] የሂሳብ መዛግብትንና ደጋፊ ሠነዶችን አለመያዝ በመጨረሻ የተወሰነውን ግብር 20% የመክፈል ቅጣት ያስከትላል።[36] ከንግድ ሥራዎችና ከሙያና ከዝንባሌ ሥራዎች የሚገኙ ገቢዎችን በወቅቱ አለማሳወቅም ይህንኑ መቀጮ ያስከትላል።[37] የግብርና ገቢ ግብርን በተመለከተ ገቢን በወቅቱ አለማሳወቅ የሚያስከትለው መቀጮ በመጨረሻ እንዲከፈል ከተወሰነው ግብር 25% ነው።[38] ግብርን በተገቢው ወቅት አለመክፈል የሚያስከትለው መቀጮ የሚሰላው ለየት ባለ የወለድ አሰተሳሰብን በሚፈነጥቅ መንገድ ነው።

የግብርና ሥራ ገቢን በተመለከተ ግብርን በወቅቱ አለመክፈል ለእያንዳንዱ ሳይከፈል ለዘገየበት ወር ያልተከፈለውን ግብር 25% መቀጮ ያስከትላል።[39] የመቀጮው ጣሪያ ያልተከፈለው ግብር 50% በመሆኑ የሚታሰበው ለሁለት ወራት ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው። ከሌሎች ምንጮች የሚገኙትን ገቢዎች በተመለከተ መቀጮው ግብሩ ሳይከፈል ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር ያልተከፈለውን ግብር 2%ሲሆን ጣሪያው ከላይ እንደተገለጸው ያልተከፈለው ግብር 50% ነው።[40]

በተጨማሪ የግብር ግዴታዎችን አለማክበር ሥራዎቹ የሚካሄዱበትን የንግድ ፈቃድ ወረቀቶች ሊያሰርዝ ወይም ሊያስነጥቅ ይችላል። የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ማዘጋጃ ቤቶችና ሌሎች አግባብ ያላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች የግብር ግዴታዎቻቸውን የማያከብሩትን ግብር ከፋዮች የንግድ ፈቃድ ወረቀቶች እንዲሰርዙ በህግ ግዴታ ተጥሎባቸዋል።[41]

በፍርድ ቤቶች አማካኝነትም የግብር ግዴታዎች እንዲከበሩ ማድረግ ይቻላል። የአፈጻጸም ክስ በመመሥረት የግብር ግዴታቸውን ያላከበሩ ግብር ከፋዮችን ንብረት በመያዝና እንዲሸጥ በማድረግ ያልተከፈለው ግብር ከሽያጩ ገቢ እንዲከፈል ማድረግ ይቻላል። በተጨማሪ የግብር ሕጎች መጣስ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ሊያስቀጣ ይችላል።[43] ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶችም ግብር ከፋዮች በሕጉ የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎች ካለማክበር ይታቀባሉ ተብሎ ይገመታል።

እነዚህ አካላትና መ/ቤቶች ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ለግብር ከፋዮች ማቅረብ ወይም መስጠት ያለባቸው ከአገር ውስጥ ገቢ አስተዳደር መ/ቤት በጽሁፍ ይኸው ሲገለጽላቸው ብቻ እንደሆነ በመመሪያው ታዟል። ምንም እንኳን በአሃዝ የተደገፈ መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንም ይህ እርምጃ የግብር ግዴታዎች እንዲከበሩ በማድረግ ረገድ ጉልህ አስተዋፅዖ እንዳለው አያጠራጥርም።

7. <u>ቅሬታዎች፥</u>

በመሠረቱ አንድ ግብር ከፋይ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ እንደደረሰው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የገቢ ግብር ባለሥልጣን መ/ቤት ዘንድ በመቅረብ ሂሣቡን ተሳስቦ ግብሩን መክፈል አለበት።[44] ሆኖም አንድ ግብር ከፋይ በግብር አወሳሰኑ ቅር ከተሰኘ ቅሬታውን የሚያሰማበት ሁለት አማራጮች አሉት።

የመጀመሪያው ጉዳይ በአስተዳደር እንዲታይለት መምረጥ ይችላል። ይህን መንገድ ከመረጠ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያው እንደገና እንዲታይለት ያመለክታል። የተያቄውም አግባብነት ብዙውን ጊዜ ሦስት አባላት ባሉት ኮሚቴ ይመረመራል። በአጠቃላይ የምርመራው ሂደት የግብር ከፋዩን ፋይል መመልከትና ሥራውን የሚያካሂድበትን ቦታና ሁኔታ ማየትንና መገምገምን ያጠቃልላል። የኮሚቴው ግኝት የግብር ውሳኔው ማስታወቂያው መከለስ ያለበት መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሆነ ይኸው ይፈጸምና ሌላ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ተዘጋጅቶ ለግብር ከፋዩ እንደ አዲስ

እንዲደርሰው ይደረጋል። ሁለተኛው ግብር ከፋዩ ቅሬታው በዳኝነት እንዲታይለት ሊመርጥ ይችላል። ይሀም የገቢ ግብር ባለሥልጣን መ/ቤት በሰጠው የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ ይግባኝ ለማለት በሀግ ከተሰጠው መብቱ ይመነጫል። የይግባኝ መብትን መጠቀም እንዲቻል ግን ሁለት ሁኔታዎች በቅድሚያ መሟላት ይኖርባቸዋል። የመጀመሪያው ይግባኙ መቅረብ ያለበትን ጊዜ ይመለከታል። ይኸውም የግብር ውሳኔ ማስታወቂያው ለግብር ከፋዩ ከደረሰበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ወር ውስጥ ይግባኙ እንዲቀርብ የሚያስገድደው ነው። ሁለተኛው በሀጉ የተገለጸውን የገንዘብ መጠን ለገቢ ግብር ባለሥልጣን መ/ቤት በመያዣ መስጠት ነው። ከሁለቱም ቅድመ ሁኔታዎች አንደኛው እንኳን ሳይሟላ ቢቀር የይግባኝ መብትን መጠቀም አይቻልም። በእንዲህ ያለ ሁኔታ የውሳኔ ማስታወቂያው እንደመጨረሻና ትክክለኛ ሆኖ ይቆጠራል። በአጠቃላይም በፍ/ቤቶች ትእዛዝ ተፈፃሚ ይሆናል።[45]

ይግባኙ በመጀመሪያ ደረጃ የሚቀርበው ለዚሁ ጉዳይ ለተቋቋመው ልዩ የዳኝነት አካል ነው።[46] ይህ የዳኝነት አካል በገቢ ግብር ባለሥልጣን መ/ቤት የተወሰነውን ግብር ለመጨመር፣ ለመቀነስ፣ ለማጽናት ወይም ለመሠረዝ እንዲሁም ለጉዳዩ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆነውን ትእዛዝ ሁሉ ለመስጠት ሥልጣን ተሰጥቶታል።[47]

የዳኝነት አካሉ በሰጠው ውሳኔ ቅር ከተሰኙ ሁለቱም ወገኖች፣ ማለትም ግብር ከፋዩና የገቢ ግብር ባለሥልጣን መ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ወደ ፍ/ቤት የማቅረብ መብት አላቸው። ሆኖም ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ላይ የሚነሱ ክርክሮችን ተቀብለው ከማየት በሕጉ የታገዱ ስለሆነ ይህ የይግባኝ መብት በሕግ ነጥቦች ረገድ ያሉ ቅሬታዎችን ብቻ የሚመለከት ነው። ፍ/ቤቶችም በውሳኔው ላይ በህግ ረገድ ተፈጽሟል የሚሉትን ስህተት ብቻ በማቃናት ጉዳዩን መልሰው ለልዩ የዳኝነት አካሉ መላክ ይኖርባቸዋል።[48]

8. <u>ከግብር ነፃ ስለመሆንና ስለማበረታቻዎች፣</u>

በኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሥርዓት ከግብር ነፃ የሚያደርጉ ድንጋጌዎች

ሀ/ በገቢ ግብር አዋጆች
ለ/ በሌሎች የአገሪቱ ሕጎች
ሐ/ በዓለም አቀፍ ውሎችና ስምምነቶች ውስጥ ይገኛሉ።

ቅጥርን በሚመለከት ገቢያቸው ከብር 50 በታች የሆኑ ተቀጣሪዎች የሚያገኙት ገቢ ከግብር ነፃ ነው።[50] በተጨማሪ በአዋጁ በተደነገጉት ሁኔታዎች ልዩ ሙያ የሌላቸው ሠራተኞች የሚያገኙት ገቢ ግብር አይከፈልበትም።[51] እንዲሁም የአንድ በውጭ አገር የሚኖር ሰው ወይም ድርጅት ተቀጣሪ በአመት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቀመጥበት ጊዜ ከ183 ቀናት እስካልበለጠ ድረስና ለሌላ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኖር ሰው ወይም ድርጅት እስካልሰራ ድረስ ከግብር ነፃ ተደርጓል። ሆኖም በውጭ አገር የሚኖረው ቀጣሪ በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራ ያለው ከሆነ እንዲህ ዓይነቱ ተቀጣሪ በተጠቀሰው ገቢ ላይ ግብር እንዲከፍል ይደረጋል።[51]

ሌላው ከግብር ነፃ የሚሆንበት ሁኔታ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ጓዶችን የሚመለከት ነው። የአንድ የውጭ አገር መንግሥትን ጥቅም በሚወክሉ አካሎች ውስጥ የሚሰሩ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ያላቸው የዚሁ መንግሥት ዜጎች የሆኑ ሠራተኞች በዚህ ውስጥ ይጠቃለላሉ። ሆኖም ከግብር ነፃ የሚደረገው መደበኛ ሥራቸውን ለማከናወን የሚከፈላቸው ገቢ ብቻ ነው።[52]

ሌሎች የገቢ ምንጮችን በሚመለከትም ከግብር ነፃ የሚኮንበት ሁኔታ አለ። በአጠቃላይ አነጋገር ከማዘጋጃ ቤቶችና ከከተሞች ከልል ውጭ የሚገኙ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች ከሙያቸው የሚያገኙት ገቢ ከግብር ነፃ ነው።[53] እንዲሁም በሀግ በታወቁ አበዳሪ ድርጅቶች ውስጥ ካላቸው የቁጠባ ሂሣብ ሰዎች የሚያገኙትን ወለድና የውጭ የጠለፋ መድን ሰጭዎች የሚሰበስቡት አረቦን ግብር አይከፈልበትም።[54] በተጨማሪ ከዕድል አሸናፊነት የሚገኙ ከብር 100 ያልበለጡ ገቢዎች ግብር የመክፈል ግዴታ አያስከትሉም።[55] በሠንጠረዥ "ሐ" ሥር ከሚገኙ ምንጮች ገቢ የሚያገኙ ግብር ከፋዮች የዓመት ገቢያቸው ከብር 300 እስካልበለጠ ድረስ ግብር የመክፈል ግዴታ የለባቸውም።[56]

በግብርና ሥራ የተሠማሩትን ሳይጨምር የኅብረት ሥራ ማኅበራት ገቢ ግብር አይከፈልበትም። ሆኖም ገቢው በማህበራቱ አባላት መካከል ከተከፋፈለ እያንዳንዱ አባል ከግብር ነፃ የሚሆነው የዓመት ድርሻው ከብር 500 እስካልበለጠ ድረስ ነው።[57]

ኢትዮጵያ በፊርማ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ውሎችና ስምምነቶች ውስጥ የሚገኙ ከግብር ነፃ መሆንን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የሚከበሩ ሲሆን በአገሪቱ ውስጥ ተፈፃሚነት አላቸው።[58] በዚህ መሠረት በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለምሳሌ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሥር ያሉ ልዩ አካላት /specialized agencies/ ሹማምንት የሚያገኙት ገቢ ግብር አይከፈልበትም።[59]

ከገቢ ግብር አዋጆች በተጨማሪ ሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች መሠረት ከግብር ነፃ መሆን ይቻላል። ለዕርዳታ ማስተባበሪያና ለመልሶ ማቋቋም ኮሚሽንና ለስፖርት ኮሚሽን የተሰጠው ከግብር ነፃ የመሆን መብት ከላይ ለተጠቀሰው ሁኔታ ሁለት ምሳሌዎች ናቸው።[60]

በአዋጅ ቁጥር 32/1981 መሠረት ለተቋቋሙ የጋራ ልማት ማህበራት በገቢ ግብር ረገድ ማበረታቻ ተደርጓል። አዳዲስ ፕሮጀክቶች ሲከፍቱ ሥራ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ለአምስት ዓመታት ከግብር ነፃ እንዲሆኑ ተፈቅዶላቸዋል። ፕሮጀክቶች በሚስፋፉበት ጊዜም ለሦስት ዓመታት ከግብር ነፃ የመሆን መብት ተሰጥቷል። ከዚህም በላይ ግብር በሚከፍሉበት ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የግብር መተመኛ ልክ 40% መሆኑ ተጨማሪ ማበረታቻ መደረጉን ያመለክታል።[61] በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በሆቴል ሥራዎች ላይ ካፒታል የሚያውሉ ሰዎችና ድርጅቶች ለተወሰነ ጊዜ ከግብር ነፃ ይሆናሉ።[62]

የግብርና ሥራዎችን በተመለከተ አንድ ኢንቬስተር ማምረት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ለሁለት፣ ለሦስት ወይም ለአምስት ዓመታት ከግብር ነፃ የመሆን መብት አለው። ይህ የሚሆነው ግን ለልማቱ የሚያውለው ካፒታል እንደቅደም ተከተሉ ሀ/

ከብር ሦሥት መቶ ሺህ በላይ ነገር ግን ከብር ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ ያልበለጠ ለ/ ከብር ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ በላይ ነገር ግን ከብር ሁለት ሚሊዮን ያልበለጠ ሐ/ ከብር ሁለት ሚሊዮን በላይ ሲሆን ነው።

የግብርና ሥራው በሚኒስትሮች ም/ቤት ቅድሚያ እንዲሰጣቸው በተወሰነ ክልሎች የሚካሄድ ከሆነ ከግብር ነፃ የሚሆንበት ጊዜ በአንድ ተጨማሪ ዓመት እንዲራዘም ይደረጋል። በእነዚህ ያሉ ክልሎች ካፒታል ማዋል የካፒታሉ መጠን ብር 300,000 ወይም ከዛ ያነሰ ቢሆንም እንኳን ማምረት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ለሁለት ዓመታት የገቢ ግብር ከመክፈል ነፃ የመሆን መብት ያስገኛል።

ለኢንዱስትሪ ልማት ካፒታል የሚያውል ሰው ማምረት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ለሁለት ለሦሥት ወይም ለአምስት ዓመታት ከግብር ነፃ የመሆን መብት አለው። ይህ እንዲሆን በልማት ላይ የሚያውለው ካፒታል እንደቅደም ተከተሉ ሀ/ከብር አምስት መቶ ሺህ በላይ ነገር ግን ከብር አንድ ሚሊዮን ያልበለጠ፣ ለ/ ከብር አንድ ሚሊዮን በላይ ነገር ግን ከብር አምስት ሚሊዮን ያልበለጠ፣ ሐ/ ከብር አምስት ሚሊዮን በላይ መሆን አለበት።

የኢንዱስትሪ ሥራው በሚኒስትሮች ም/ቤት ቅድሚያ እንዲሰጣቸው በተወሰነ ክልሎች የሚካሄድ ከሆነ ከግብር ነፃ የሚሆንበት ጊዜ በአንድ ተጨማሪ ዓመት ይራዘማል። በእንደዚህ ዓይነት ክልሎች ልማት ላይ የሚውለው ካፒታል ብር አምስት መቶ ሺህ ወይም ያነሰ ቢሆንም ከብር ሃምሳ ሺህ እስካላነሰ ድረስ ማምረት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ለሁለት ዓመታት ከግብር ነፃ የመሆን መብት ያስገኛል።

ቅድሚያ በተሰጣቸው ክልሎች የሆቴል አገልግሎቶች ማቋቋምን ለማበረታታት ሲባል የሚያቋቁሙት የገቢ ግብር ከመክፈል እንዲሁ ለሁለት ዓመታት ነፃ ይደረጋሉ። ሆኖም ከግብር ነፃ ለመሆን የሚቋቋሙት ድርጅቶች የሆቴልና ቱሪዝም ኮሚሽን ያወጣውን መመዘኛ አሟልተው መገኘት አለባቸው። ለሁለት፣ ለሦሥት ወይም

ለአምስት ዓመታት ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ የግብርና ወይም የኢንዱስትሪ ልማቶች ከፍተኛ ማስፋፋት ማድረጋቸው ሲረጋገጥ ተጨማሪው ሥራ የሚያስገኘው ገቢ እንደቅደም ተከተሉ ለአንድ፣ ለሁለትና ለሦሥት ዓመታት ከግብር ነፃ ይሆናል።[63]

9. <u>መደምደሚያ፣</u>

በዚህ ስለ ኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሥርዓት በሚገልጸው አጭር ጽሁፍ መደምደሚያ ላይ አንዳንድ መሠረታዊ ነጥቦችን ማንሳት ጠቃሚ ይሆናል።

<u>ገቢ ለሚለው ቃል ሕጉ የሰጠው ትርጓሜ</u>

"ገቢ" ለሚለው ቃል የኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሕጎች የሰጡት ትርጓሜ ችግር የለበትምን? ከፍ ብሎ ለቀረበው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ "አዎ አለበት" የሚል ነው። በመጀመሪያ ገቢ የሚለው ቃል የተተረጎመበት ቋንቋ ግልጽነት ይጎድለዋል። ይኸውም በኢትዮጵያ ውስጥ መገኘት ያለበት "ገቢው" ራሱ መሆኑ ወይም "ምንጩ" ማለትም ለገቢው መገኘት ምክንያት የሆነው የሥራ እንቅስቃሴ መሆኑ ግልጽ አይደለም። ሁለተኛ በህጉ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደሚያረጋግጡት ሁሉ ገቢ የሚለው ቃል የንግድ ዋጋ ያላቸውን አገልግሎቶች እንደሚሸፍን የሚጠቁም አነጋገር ትርጉሙ አልያዘም። ስለዚህ ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ችግሮችና ሌሎች ጉድለቶች የሚያስተካክል ትርጉም ገቢ ለሚለው ቃል መሻት አስፈላጊ ይሆናል።

<u>የአክሲዮን ድርሻና ከባለመብትነት /royalty/ የሚገኝ ክፍያ፣</u>

በአክሲዮን ድርሻና ከባለመብትነት በሚገኝ ክፍያ ላይ የተጣሉት ግብሮች ያላቸው ተግባራዊነት እስከምን ድረስ ነው? እነዚህ ግብሮች የኢትዮጵያ የቀጥተኛ ግብር ሥርዓት ክፍል ከሆኑ ከአሥር ዓመታት በላይ ሆንዋል። ይሁንና እነዚህን ግብሮች ሥራ ላይ ለማዋል በተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ ችግሮች አጋጥመዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ትርጫፎች ወይም ተገኞች ያሏቸው ድንበር ዘለል ኩባንያዎችን በተመለከተ በሕጉ ውስጥ ምንም ድንጋጌ ባለመኖሩ እነዚህን የአክሲዮን ድርሻ ግብርን ወስና ለማስከፈል የማይቻል ሆንዋል። ኩባንያው በኢትዮጵያ ውስጥ ተቋቁሞ የተመዘገበ ቢሆን እንኳን ግብር የመክፈል ኃላፊነት የሚኖረው ትርፍ መኖሩ ሲገለጽና የአክሲዮን ድርሻው ሲከፋፈል ብቻ በመሆኑ ባለአክሲዮኖች በጠቅላላ ስብሰባዎቻቸው ትርፍ የመከፋፈሉን ጥያቄ ላልተተወሰነ ጊዜ ማስተላለፍ ይችላሉ። ከዚሁ ጋርም ከኩባንያው ጋር መስል የብድር ውል በመፈጸም ወይም ሌላ ዘዴ በመፍጠር ከአክሲዮን ድርሻ የሚያገኙትን ጥቅም ማስጠበቅ ይችላሉ። በዚህ የተነሣ የግብሩ አሰባሰብ ተፈፃሚ እንዳይሆን ማድረግ ይችላሉ። 40% በሆነ ከፍተኛ ልክ የሚሰበሰበው ከባለመብትነት በሚገኝ ክፍያ ላይ የተጣለው ግብር የአእምሮ የፈጠራ ሥራዎችን እንደማያበረታታ ግልጽ ነው። ይህም ሁኔታ ተፈፃሚነቱ ተቀባይነት እንዳይኖረው አድርጓል። በተጨማሪ በገቢ ግብር ሕጋጋት ውስጥ የዚህ ግብር ተፈፃሚነት ያለው ክልል በግልጽ ካለመመልከቱ በላይ ስለግኝትና ስለ ድርሰት መብቶች የሚወስን የተለየ ህግ የለም። እነዚህ ሁኔታዎች ይህንን ግብር ሥራ ላይ ለማዋል አስቸጋሪ አድርገውታል። በመሆኑም ያለውን የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ከላይ የተጠቀሱትን ግብሮች እንደገና መገምገም ግድና አስፈላጊ ይሆናል።

ከውጭ አገር ለተሰጡ አገልግሎቶች የሚደረግ ክፍያ፥

ከውጭ አገር ለተሰጡ አገልግሎቶች በሚደረጉ ክፍያዎች ላይ የተጣለውን ግብር በተግባር ለመተርጎም በሚሞከርበት ጊዜ ቢያንስ ሁለት ችግሮች ይጋረጣሉ። በመጀመሪያ ግብሩ የአገልግሎቱ ከንውን ከኢትዮጵያ ውጭ በሆነበት ሁኔታ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የታቀደ መሆኑ ግልጽ አይደለም። ይህ ታቅዶ ከሆነ የተባለው ግብር ማናቸውም በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የሚገኝ ጥቅም "ገቢ" እንዲባል ምንጩ በኢትዮጵያ ውስጥ መሆን አለበት ከሚለው መሠረተ ሃሳብ በልዩነት የሚታይ ይሆናል። በሁለተኛ ደረጃ ግብሩ በአጋጣሚ የሚሰጥን አገልግሎት ብቻ እንዲመለከት ወይም የተከታታይነት ባህርይ ያለውን ጨምሮ ከውጭ አገር የተሰጠ ማናቸውንም

አገልግሎት እንዲመለከት የታቀደ መሆኑ በእርግጠኝነት አይታወቅም። ስለዚህ ይህንን ግብር የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ማሻሻያ ሊደረግላቸው ይገባል።

<u>መደበኛ ያልሆነ የንብረት ኪራይ፣</u>

ንብረት መደበኛ ባልሆነ መንገድ በማከራየት በሚገኝ ገቢ ላይ የተጣለውን ግብር በተመለከተ በግብሩ አወሳሰንና አከፋፈል መካከል አለመጣጣም ይታያል። ግብሩ ገቢው ከተገኘበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲከፈል ሲደረግ አወሳሰኑ ግን በዓመታዊ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ተመስርቶ በተቀረጸው በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት እንዲሆን ተደርጓል። ይህ አደናጋሪ ሁኔታ ንብረትን መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ በማከራየት በሚገኘው ገቢ ላይ ግብሩን ወስኖ የማስከፈሉን ተግባር አስቸጋሪ አድርጎታል። ይህ ችግር አንድ ግብር ከፋይ ንብረትን መደበኛ ባልሆነ መንገድ በማከራየት ከሚያገኘው ገቢ በተጨማሪ ለምሳሌ ከንግድ ሥራ ገቢ በሚያገኝበት ጊዜ ለግብሩ አወሳሰን ገቢዎቹን የማጣመሩን ተግባር ውስብስብ ያደርገዋል። ከነዚህ ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ችግሮች አኳያና በህግ ተለይቶ ካልተመለከተ ማናቸውም ምንጭ ወይም የሥራ እንቅስቃሴ የተገኘ ገቢ ሁሉ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የሚከፈልበት ከመሆኑ አንፃር ሲታይ ንብረትን መደበኛ ባልሆነ መንገድ በማከራየት ስለሚገኘው ገቢ ግብር አከፋፈልና አወሳሰን የሚደነገጉት አንቀፆች እንዲሻሩ የሚቀርብ ሃሣብ እንኳን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

<u>የመንግሥት የልማትና የገንዘብ ድርጅቶች ግብር የመክፈል ግዴታ፣</u>

የመንግሥት የልማትና የገንዘብ ድርጅቶች ለማዕከላዊ መንግሥት ትርፋቸውን ሁሉ ፈሰስ የማድረግ ግዴታ እያለባቸው ግብር እንዲከፍሉ ማድረግ አግባብ ነውን? አሁን ካሉት ተጨባጭ ሁኔታዎች ራስን በማግለል ነገሩ ሲታይ ከፍ ብሎ የቀረበው ጥያቄ መልስ አሉታዊ መሆኑ አይታበልም። በአንድ ግብር ከፋይና በዛው ባገኘው ገቢ

ላይ ጫና የገቢ አሰባሰብ ሥልቶችን ወይም ዘዴዎችን በአንድ ጊዜ ተፈፃሚ ማድረግ የሰው ኃይልን ጊዜንና ሃብትን የሚያባክን የአሠራር ድርብርቦሽ እንዲሚያስከትል ግልፅ ነው። ይሀም መንግሥትን አስፈላጊ ላልሆነ ከፍተኛ ወጭ ይዳርጋል። ይሁን እንጂ የመንግሥት የልማትና የገንዘብ ድርጅቶችን በሚመለከት የገቢ ግብርን ተፈፃሚ ማድረግ ያለው ጎጂ ገጽታ የሚታወቅ ቢሆንም ሌላውን አመለካከት ማጤን ተገቢ ሆኖ ይገኛል። ጥያቄው የመንግሥትና የገንዘብ ድርጅቶችን አስመልክቶ የገቢ ግብር ተፈፃሚነት የሚያስከትሎበትን ትክክለኛ ወቅት የመወሰን የጊዜ ጥያቄ ነው። ከአንድ የአሠራር ኃይነት ፍጹም አዲስ ወደሆነ ሌላ አሠራር በፍጥነት መዞር ብዙውን ጊዜ ማንኳና የብቃት ጉድለት ያስከትላል። ምናልባትም ይህ የመንግሥት የገንዘብ ፖሊሲዎችን በማስፈጸም ረገድ የበለጠ ጉልህ ሆኖ ይታያል።

አሁን ባሉት ሁኔታዎች በመንግሥት የልማትና የገንዘብ ድርጅቶች ላይ የገቢ ግብርን ተፈፃሚ ማድረግ ተገቢ ነው የሚባልባቸው ምክንያቶች ለቁጥጥር ኃላማዎች ስለሚያገለግልና በተለይ የምጣኔ ሃብት ክንውኖችን ለመገምገም ስለሚጠቅም ነው። ቢሆንም የመንግሥት የልማትና የገንዘብ ድርጅቶች ገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ እስካለባቸው ድረስ ጎጂ ገጽታዎቹን ለመቀነስ ሲባል ሥራዎችን በቅንጅት መምራት ወይም ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑ ግልጽ ነው።

<u>የገቢ ግብር ልኮች፣</u>

ጉልህ የንረት እርከን የሚታይባቸው አሁን ሥራ ላይ ያሉት የገቢ ግብር ልኮች በሀብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የገቢ መራራቅ ለማጥበብ መታቀዳቸው ግልጽ ነው። ገቢው በጨመረ ቁጥር የግብሩ ጫናም ይበልጥ መክበዱን ያሳያሉ።

የአሁኑ የገቢ ግብር ልኮች አወቃቀር ሕጋዊ በሆነ መንገድ ትርፍ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ ለመሠማራት የሚደረገውን የግል ጥረት የማያበረታታ በመሆኑም ለንቀፊታ የተጋለጠ ነው። ትጥርን በሚመለከት ግብር የሚከፈልበት የወር ገቢ ከብር

3,500 በላይ ሲሆን በልዩነቱ ላይ የሚከፈለው ግብር 85% ነው። የግብርና ሥራዎችን በተመለከተ ደግሞ ግለሰብ ገበሬዎችና የእርሻ አምራቾች የህብረት ሥራ ማህበራት የሚያገኙት ግብር የሚከፈልበት የዓመት ገቢ ከብር 36,000 በላይ ሲሆን በልዩነቱ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ልክ 89% ነው። ለሌሎች የሥራ እንቅስቃሴዎች ግለሰቦች የሚያገኙት ግብር የሚከፈልበት የዓመት ገቢ ከብር 24,000 በላይ ሲሆን በልዩነት ተፈፃሚ የሚሆነው 59% ነው። እንግዲህ ከፍ ብሎ ከተገለጸው ለብሔራዊ ዕድገት ጉልህ አስተዋፅዖ እንዲያደርግ በሚጠበቀው ለግል ሥራ በማንግግት ላይ እነዚህ ልኮች ያላቸውን ጎጂ አዝማሚያ በተሻለ መገመት ይቻላል።

የግብር የዳኝነት አካላት፥

የተለዩ የዳኝነት አካላትን ማቋቋም ያስፈለገው በመደበኛ ፍ/ቤቶች ላይ ሊደርስ የሚችለውን የሥራ ጫና በመቀነስ ረገድ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል በሚል አስተሳሰብ እንደሆነ ይገመታል። ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ ተከራካሪ ወገኖች የዳኝነት አካላት በሰጧቸው ውሳኔዎች ላይ ለመደበኛ ፍ/ቤቶች ይግባኝ የሚያቀርቡ ስለሆነ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው አመለካከት ያለውን ጥንካሬ በአመዛኙ ያጣል። በተጨማሪ የመደበኛ ፍ/ቤቶች ሥልጣን በህግ ረገድ በሚነሱ ክርክሮች ላይ ብቻ መገደቡና ፍ/ቤቶቹ ለመጨረሻ ውሳኔ ጉዳዮቹን ለዳኝነት አካላቱ መልሰው እንዲልኩ መደረጉ የፍርድ ሥራ አካሄዱን አለአግባብ ያራዝመዋል።

ስለዚህ የተለዩ የግብር የዳኝነት አካላት መኖራቸው ያለው ጥቅምና ጉዳት በጥንቃቄ መመዘንና እንዲያውም አስከናካቴው እነዚህን አካላት በማስቀረት በምትኩ በመደበኛ ፍ/ቤቶች መዋቅር ውስጥ በአጠቃላይ የግብር ጉዳዮችን ብቻ የሚመለከቱ ችሎቶችን ማቋቋም የሚያስገኘውን ጥቅም መገምገም አስፈላጊ ይሆናል።

የህብረት ሥራ ማህበራት

ህብረት ሥራ ማህበራትን ከግብር ነፃ የማድረግ ሃሣብ መቋቋማቸውን ለማበረታታት ካለው አስፈላጊነት የመነጨ መስሎ ይታያል። በህግ አወጣጡም ቢሆን የግብር ጫና በቁጠባ ላይ አነስተኛ በፍጆታ ላይ ከፍተኛ ሊሆን ይገባል ከሚለው መሠረተ ሃሣብ ጋር ተስማሚ ሆኖ የገኛል፥ ይሁን እንጂ የእርሻ የህብረት ሥራ ማህበራት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆናቸው ነገር አደናጋሪ የመሆኑ ጉዳይ፥ የህብረት ሥራ ማህበራት ዓባላትን አስመልክቶ ያሉት ከግብር ነፃ የሚያደርጉ አንቀፆች በአጠቃላይ አነጋገር ዓላማውን የሚያፈርሱ የመሆናቸው ጉዳይ፥ እንዲሁም ግብር መክፈል ካለባቸው የህብረት ሥራ ማኅበራት ዓባላት ግብሩን ወስኖ ለመሰብሰብ አዳጋች የመሆኑ ጉዳይ ትኩረት የሚሹ ትልህ ችግሮች ሆነው ይገኛሉ።

በግብር አስተዳደር የህዝባዊ ድርጅቶች ተሳትፎ፥

የገበሬ ማህበራት በግብር አስተዳደር ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ የቱን ያህል ጠቀሜታና ቅልጥፍና አስገኝቷል? አግባብነት ያላቸው ህዝባዊ ድርጅቶች የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ተቀጽላ ክንድ በመሆን በግብር አስተዳደር ተሳትፎ ቢያደርጉ የመንግሥት ግብር የመሰብሰብ አቅም የሚጨምር መሆኑ ግልጽ ስለሆነ ይህ ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑ አያስገርምም። ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዚህ ረገድ የገበሬ ማህበራት የመጀመሪያ ተመክሮ አላቸው። በዚህ ልምድ ላይ ትክክለኛ ግምገማ ቢደረግ መሻሻል የሚያስፈልጋቸውን የነገር አካባቢዎች ለይቶ ለማወቅ ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ የተሻሉ ዘዴዎችን በመቀየስ ተመሳሳይ እርምጃዎችን ለመውሰድ ያግዛል። ሆኖም በአጠቃላይ አነጋገር የህዝቡ አጠቃላይ የትምህርት ደረጃና የግብር ንቃት እንዲሁም በህጎችና በመመሪያዎች ውስጥ ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተለይተው መመልከታቸው የእንዲህ ያለውን ዕቅድ ተግባራዊነት ይወስናሉ።

ለማጠቃለል፥ አሁን ባለው የገቢ ግብር ሥርዓት ውስጥ የሚታዩት ችግሮች ከዚህ የበለጠ ብዙና የተለያዩ ናቸው። የገቢ ግብሮች አጥጋቢ የመንግሥት የገንዘብ ፖሊሲዎች ማስፈፀሚያ መሳሪያዎች ሆነው እንዲያገለግሉ ሁኔታዎቹን በአጣዳፊ ማሻሻል አስፈላጊ ነው። የገቢ ግብሮችን ትክክለኛና አንድ ወጥ አፈፃፀም የሚያደናቅፉ ማናቸውንም ችግሮች ማስወገድ አስፈላጊነት አያጠያይቅም። ይህንና ሥርዓቱን የማሻሻሉ ተግባር ብዙ ሥራ ይጠይቃል። በገቢ ግብር ሥርዓት አፈጻጸም ላይ ያሉት ማነቆዎች ከፖሊሲ፥ ከህግ ወይም ከአስተዳደር የመነጩ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ የማሻሻሉ ተግባር ከነዚህ ሦሥት መሠረታዊ ዘርፎች አኳያ መከናወን ይኖርበታል።

ማስታወሻዎች

1. የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ "የገቢና የንብረት ግብሮች በኢትዮጵያ፥ መሠረታዊ ተግባሮችና ዋና ዋና ገጽታዎች" በሚል ርዕስ የመንግሥት የገንዘብ እድገትን በሚመለከት በተዘጋጀው የኢትዮጵያ ብሄራዊ የስልጠና ወርክ ሾፕ ላይ የውይይት ጽሁፍ ለማቅረብ ዕድል አጋጥሞት ነበር። ነገር ግን የተባለውን ወርክ ሾፕ አዘጋጅቶ የነበረው የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ሲሆን የተካሄደው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ 22 እስከ 26 ኦክቶበር 1984 ዓ.ም. ነበር።

   የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ከላይ የተጠቀሰውን ጽሁፍ ያለምንም ለውጥ እንዳለ በዚህ ህግ መጽሄት የማውጣት እቅድ ነበረው። ዳሩ ግን ረጅም በመሆኑ ሰፊ ቦታ የሚጠይቅ ሆኖ ስለተገኘ ማሳጠር ግድ ሆንዋል። በተጨማሪም በመጀመሪያ ጊዜ ጽሁፉ ከቀረበ በኋላ ለጉዳዩ አግባብ ያላቸው የገቢና ሌሎች ሕጎች ስለወጡ በዚሁ መሠረት በጽሁፉ ላይ ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ ሆንዋል።

ከዚህ ጽሁፍ ርዕስ ለመረዳት እንደሚቻለው ለማሳጠር ሲባል በቀድሞው ጽሁፍ ውስጥ ስለንብረት ግብር የቀረበው ገለጻ ሁሉ ቀሪ ሆንዋል። በሌላ በኩል በመጀመሪያው ጽሁፍ ውስጥ ስለ ገቢ ግብር የተገለጸው ባመዛኙ ለውጥ ሳይደረግበት እንዳለ ቀርቧል።

2. አዋጅ ቁጥር 173/1953 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 3ን ይመለከቷል። በዚህ ጽሁፍ በግልጽ ካልተነገረ በስተቀር የተጠቀሱት አንቀፆች በሙሉ የሚመለከቱት ይህንን አዋጅ ነው።

3. በልዩነት የሚታየው ከውጭ አገር ለተሰጡ አገልግሎቶች በሚደረገው ክፍያ ላይ የተጣለው ግብር ነው።

4. የአማርኛውን ቅጂ አንቀጽ 4/"ሀ" እና "ለ"/ን እና የአዋጅ ቁጥር 77/1968ን አንቀጽ 3/9/ ይመለከቷል።

5. አንቀጽ 4 /"ሐ"፥ "መ" እና "ሠ"/ን ይመለከታል።

6. አንቀጽ 6

7. አንቀጽ 3 /ለ/

8. አንቀጽ 3/ሀ/ን ከአዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 3/3/ ጋራ ያነፃፅርዋል። ሀ/ የአምራቾች የህብረት ሥራ ማኅበራት በአዋጅ ቁጥር 173/1953 /እንደ ተሻሻለው/ "ድርጅት" ለሚለው ቃል ከተሰጠው ትርጉም ውጭ ናቸው። ለ/ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ "የጋራ የልማት ማኅበራት" ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 32/1981 የተሰጠ ነው።

9. የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 258/1955።

10. አንቀጽ 31 እና አንቀጽ 34 /"ለ"፣ "ሐ"፣ "መ" እና "ሠ"/።

11. የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 258/1955 አንቀጽ 21 /2፣3 እና 4/።

12. አንቀጽ 32፣ 33 እና 45። ምንም እንኳን ሕጉ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚናገረው ነገር ባይኖርም፣ በልምድ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩና ግብር የመክፈል ግዴታ ያለባቸው ተቀጣሪዎች ራሳቸው በመቅረብ የየወሩን ገቢያቸውን ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን በማስታወቅ በገቢው ላይ የሚጠየቀውን ግብር መክፈል አለባቸው።

13. የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 258/1955 አንቀጽ 25 በተጨማሪ አንቀጽ 35 እና 46ን ይመለከቷል። የኢትዮጵያ በጀት ዓመት ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ ያለው ጊዜ መሆኑን ይገነዘቧል።

14. አንቀጽ 34 /ለ/።

15. አንቀጽ 17 እና 20።

16. አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 13። ገቢን የማሳወቅና ግብሩን የመክፈል ግዴታ ገበሬው ገቢውን ያገኘው ከታሕሣሥ 1 ቀን በፊት ቢሆንም እንኳን ገቢውን ካገኘበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ መፈጸም እንዳለበት ይገነዘቧል።

17. አንቀጽ 22።

18. አንቀጽ 39 እና አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 21።

19. አንቀጽ 40 እና አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 21።

20. አንቀጽ 8።

21. የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 258/1955 አንቀጽ 4።

22. አንቀጽ 16ን ከሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 258/1955 አንቀጽ 16 እና 17 ጋራ በማጣመር እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 77/1968 እንደተሻሻለው አንቀጽ 24ን ይመለከቷል።

23. አንቀጽ 4፣7 /ለ/ /2/ እና 12/"ለ" "ሀ" እና መ"/ እና አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 25/1 እና 2/።

24. አንቀጽ 5ን ከሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 258/1955 አንቀጽ 34 /ሐ/ ጋር በማጣመር ይመለከቷል። እንዲሁም ከአዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 23 ጋር ያነፃፅርዋል።

25. አንቀጽ 7/ሀ/።

26. አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 15። የገበሬ ማህበራት በግብር አወሳሰን ይሳተፋሉ፣ እንዲያውም አብዛኛው ሥራ በእነርሱ ላይ ወድቋል። /አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 16።

27. አንቀጽ 12 "ሐ" እና አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 25/1/።

28. አንቀጽ 17።

29. አንቀጽ 17 እና 20።

30. ለቅጥር አንቀጽ 7 /ሀ/ /2/፣ ለግብርና ሥራ አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 25/2/፣ እና ለሌሎች የገቢ ምንጮች አንቀጽ 12/ሀ/ /2/ን ይመለከቷል።

31. አንቀጽ 41 እና አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 26/1/።

32. አንቀጽ 70 እና አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 26/2።

33. አንቀጽ 47 እና 48።

34. የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 258/1955 አንቀጽ 34/መ/ እና አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 27/1/።

35. አንቀጽ 69 እና አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 40።

36. አንቀጽ 68 እና አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 39/2። የገንዘብ ሚኒስትር እስካሁን ድረስ ደንብ ባለማውጣቱ የግብርና ሥራ ገቢን በተመለከተ የተጣሉትን መቀጮዎች ሥራ ላይ ማዋል አስቸጋሪ ሆኖ መቆየቱን ይገነዘቧል።

37. አንቀጽ 66።

38. አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 39/3/። ወደሌላ ድንጋጌ ከመምራት ይልቅ መቀጮውን በግልጽ ማስፈር የተሻለ በሆነ ነበር።

39. አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 39/1/።

40. አንቀጽ 67።

41. አንቀጽ 27።

42. አንቀጽ 62 እና 63 እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 41።

43. አንቀጽ 70 እና አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 43። አግባብ ያላቸው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥሮች 354-356፣ 362 እና 70 ናቸው።

44. አንቀጽ 46።

45. አንቀጽ 54 እና 55ን ከአዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ ከአንቀጽ 27/2/ እና 28 ጋራ ያነፃፅርዋል።

46. አንቀጽ 49 እና አዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 29።

47. አንቀጽ 56። ከአዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 33 ጋራ ያነፃፅርዋል።

48. አንቀጽ 58-60። ከአዋጅ ቁጥር 77/1968 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 34 እና 35 ጋራ ያነፃፅርዋል። የግብርና ሥራ የገቢ ግብርን በተመለከተ የአውራጃ ፍቤት በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም።

49. አንቀጽ 7/ለ/ /1/።

50. አንቀጽ 18 /ሐ/ ከህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 258/1955 አንቀጽ 10 ጋራ በማጣመር ይመለከቷል።

51. አንቀጽ 18 /መ/ ከሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 258/1955 አንቀጽ 11 ጋራ በማጣመር ይመለከቷል።

52. አንቀጽ 18 /ሰ/።

53. አንቀጽ 18 /ለ/። ከግብር ነፃ የሚያደርጋቸው መብት ተጠቃሚ ለመሆን እንዲህ ያሉት ሰዎች በቋሚነት ወይም በመደበኛነት ሠራተኞች መቅጠር አይኖርባቸውም። ከ1952 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንግድ ህግ ቁጥር 9 ጋራ ያነፃፅርዋል።

54. አንቀጽ 18 /"ሠ" እና "ረ"/።

55. አንቀጽ 17 /ለ/ /1/።

56. አንቀጽ 12/ለ/ /2/።

57. አዋጅ ቁጥር 155/1971 አንቀጽ 2/4/።

58. አንቀጽ 18 /ሸ/።

59. የተባበሩት መንግሥታት ልዩ መብቶችና የማይደፈሩ መብቶች ቃል ኪዳን (ከንቬንሽን) ክፍል 18 አንቀጽ 5 እና የተባበሩት መንግሥታት የተለዩ አካላት ልዩ መብቶችና የማይደፈሩ መብቶች ቃል ኪዳን ክፍል 19 አንቀጽ 6።

60. አዋጅ ቁጥር 203/1973 አንቀጽ 9 እና አዋጅ ቁጥር 92/1968 አንቀጽ 23።

61. አዋጅ ቁጥር 32/1981 አንቀጽ 27/5/ እና /10/።

62. የመንግሥት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ ቁጥር 17/1982 አንቀጽ 11 እና 12።

63. በመንግሥት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ ቁጥር 17/1982 አንቀጽ 2/2/ መሠረት "ከፍተኛ መስፋፋት" ማለት የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ችሎታን 50% ወይም ከዚያ በላይ ማሳደግ ማለት ነው።

64. አንቀጽ 34/ለ/። ከ1952 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አንቀጽ 419 እና 420 ጋራ ያነፃፅርዋል።

አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈጽሟቸው ተግባሮች በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ያለ ኃላፊነት*

በንጋቱ ተስፋዬ**

ጠቅላላ

በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2027 መሠረት አንድ ሰው ሦስት ዓይነት ኃላፊነት ሊመጣበት ይችላል። አንደኛ፥ አንድ ሰው በራሱ ጥፋት[1] በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ኃላፊ ይሆናል። ሁለተኛ፥ ህጉ የሚያዝ ሲሆን፥ አንድ ሰው "የሚያከናውነው ሥራ"[2] ወይም በጠባቂነት ወይም በባለሀብትነት የያዘው "ንብረት"[3] በሌሎች ላይ ላደረሰው ጉዳት ኃላፊ ይሆናል። በመጨረሻም፥ አንድ ሌላ ሰው በፈፀመው ጥፋት ምክንያት ወይም ህጉ በሚያዘው ሁኔታ ኃላፊነት ሲመጣበት ለዚህ ለመጣው ኃላፊነት ሕጉ ኃላፊ ትሆናለህ ሲለው ኃላፊ ይሆናል።

የመጀመሪያው ዓይነት ኃላፊነት፥ ማለትም በራስ ጥፋት ላይ የተመሠረተው ኃላፊነት፥ የሁሉም አገሮች መሠረታዊ የሆነ ውል ሳይኖር የሚደርስ ኃላፊነት ህግ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያትም የፍትሐብሔር ኃላፊነት እንዲኖር ጥፋት /ወይም የበደል ተግባር/የተፈፀመ መሆን አለበት የሚለው አስተሳሰብ ከማናቸውም ኅብረተሰብ የፍትሕ ስሜት ጋራ የሚጣጣም ሆኖ ስለሚገኝ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ፀሐፊዎች ሁለተኛውን ዓይነት ኃላፊነት፥ ማለትም ያለጥፋት ኃላፊ መሆንን፥ እንደ ማህበራዊ የፍትሕ መጓደል አድርገው ይመለከቱታል። "ይህ ዓይነት የፍትሐብሔር

---

* ይህ ጽሁፍ በ1980 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ በዚያው ዓመት ለወቅቱ የመጽሄቱ አዘጋጆች ተሰጥቶ የነበረ ነው።

** ረዳት ፕሮፌሰር፥ ህግ ፋኩልቲ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

አላፊነት በወንጀል ጉዳይ በአንድ ንፁሕ ሰው ላይ ከሚሰጥ የቅጣት ፍርድ ጋራ ተመሳሳይ ነው"[4] በማለት ይነቅፉታል።

<u>በልዩ ሁኔታዎች</u> ያለጥፋት አላፊነት እንዲኖር በሚደገፉትና ይህን ዓይነቱን አላፊነት ፈፅሞ በሚቃወሙት መካከል ያለው ልዩነት የሚመነጨው ሁለቱ ወገኖች ውል ሳይኖር ለሚደርሰው አላፊነት ህግ ካላቸው አመለካከት ይመስላል። ያለጥፋት አላፊ መሆንን ፈፅሞ በሚቃወሙት ሰዎች አመለካከት የውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ህግ ዋነኛ ተግባር ቁጥጥር ማድረግ፥ ማለትም በደል እንዳይፈፀም መከላከልና አጥፊን መቅጣት ነው። ለእነርሱ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች ማስካስ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ የህጉ አላማ ነው።[5] በአንዳንድ ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች ያለጥፋት አላፊነት እንዲኖር የሚደግፉት ሰዎች በበኩላቸው የውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ህግ ተቀዳሚ አላማ ገለሰቦች ለሚደርስባቸው ጉዳት ዋስትና እንዲኖራቸው ማድረግ፥ ማለትም ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ካሣ ማስከፈል፥ ነው ይላሉ። በዚህኛው አመለካከት መሠረት አጥፊዎችን መቅጣት የውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ህግ ዓላማ አይደለም። ይኸኛው የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ የሚያስተናግደው ጉዳይ ነው። የፍትሐብሄር አላፊነት የሚያስከትለው ውጤት ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች ማስካስ ነው። በመሆኑም ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ህግን ጥፋት እንዳይፈፀም እንዲከላከል ሆኖ እንደተቀየሰ የመቆጣጠሪያ መሣሪያ አድርጎ መመልከት ስሕተት ይሆናል።[6]

ይሁን እንጂ የውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ሕግ ተቀዳሚ ተግባር ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ካሣ ማስከፈል ነው ሲባል፥ ያለበቂ ምክንያት ሰዎች አላፊ እንዲሆኑ ይደረጋል ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያሻል። "ቅጣት" የሚለው ቃል ካለው ስሜት አንፃር ጉዳዩ ከታየ ደግሞ፥ በተለይ አላፊነቱ በጥፋት ላይ የተመሠረተ በሚሆንበት ጊዜ፥ አጥፊው ለፈፀመው ጥፋት አይቀጣም ማለትም አይደለም። የገንዘብ መቀጮ አለ። ምንም እንኳን በወንጀል ህግ እንደሚታየው አጥፊው ነፃነቱን የሚያጣ ባይሆንም፥ በራሱ ጥፋት ጉዳት ላደረሰበት ሰው ካሣ እንዲከፍል ይደረጋል። ይህም የሀብቱን መጠን ይቀንሰበታል። በዚህ ስሜቱ አጥፊው ተቀጥቷል ማለት ይቻላል።

ይህም ሁኔታ ግለሰቦች በሌሎች ወገኖች ላይ ጉዳት ለማድረስ እንዳይደፋፈሩ ያደርጋቸዋል። ይኸ ግን በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ የውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ህግ ተግባር ነው።

ሦስተኛው ዓይነት አላፊነት፣ ማለትም ሌሎች ሰዎች ለፈፀሙት ተግባር አላፊ መሆን፣ በአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ብቻ የሚያጋጥም ነው። ጠቅለል ባለ አነጋገር አንድ ሰው በሌሎች ሰዎች ለተፈፀሙ ተግባሮች በፍትሐብሔር አላፊ የሚሆንባቸው ሦስት ሁኔታዎች አሉ። አንደኛ፣ ወላጆች ወይም በወላጆች እግር የሚተኩ[7] ሌሎች ሰዎች አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች[8] ለሚያደርሱት ጉዳት አላፊ ይሆናሉ። ሁለተኛ፣ አንድ አሠሪ ሠራተኛው ለሚያደርሰው ጉዳት አላፊ ይሆናል።[9] ከነዚህም በተጨማሪ አንድ ሰው ለሌላ ሰው ተግባር አላፊ የሚሆንበት ሦስተኛ ሁኔታም አለ። ይኸም የአንድ ጽሁፍ ደራሲ ስም አጥፍቶ የሚገኝበት ጉዳይ ነው። እንዲህ ባለው ሁኔታ ደራሲው በጽሁፉ ውስጥ ለፈፀመው የስም ማጥፋት ተግባር የጋዜጣው መሪ፣ የተባራሪው ማስታወቂያ /ፓምፍሌት/ አታሚ፣ ወይም የመጽሐፉ አውጪ /ፓብሊሸር/ አላፊ ይሆናል።[10] የሁዋለኞቹ ሁለት ሁኔታዎች በዚህ ጽሁፍ ውስጥ አይወሱም። የምናተኩረው አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች በሚኖረው አላፊነት ላይ ብቻ ነው።

ለመሆኑ አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች ያለው አላፊነት መሠረቱ ምንድን ነው? የትኞቹ ሰዎች ናቸው አላፊ የተደረጉት? ለምንስ አላፊነት ተጣለባቸው?

የተለያዩ አመለካከቶች

አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች አላፊነቱን ለመጣል ባጠቃላይ ሁለት አመለካከቶች አሉ። እነሱም /1/ ጥፋት ተፈፅሟል በሚል የሕግ ግምት፣ እና /2/ ጥፋት ለመፈፀሙ ማረጋገጫ ይቅረብ፣ በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። እነዚህንም ተጥለን በየተራ በአጭሩ እንተነትናቸዋለን።

1/ ጥፋት ተፈፅሟል በሚል የሕግ ግምት ላይ የተመሠረተ አላፊነት

በዚህ አመለካከት መሠረት እካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች ያለው አላፊነት የተመሠረተው እካለመጠን ያላደረሰውን ልጅ የሚቆጣጠሩት ሰዎች ጥፋት ፈፅመዋል በሚል የሕግ ግምት ላይ ነው። ይኸኛው አስተሳሰብ የሲቪል የሕግ ሥርዓትን በሚከተሉ አገሮች በአብዛኛው ሲሠራበት ይታያል። ሆኖም ጥቃቅን ልዩነቶች አሉ። የፈረንሳይና የጀርመን የፍትሐብሔር ሕጎች ተፈፃሚ ትኩረት በሚያደርጉባቸው አገሮች የልጁ ወላጆችና ሌሎች አሳዳጊዎች የመጀመሪያ ደረጃ አላፊነት አለባቸው።[11] በአብዛኛዎቹ የምሥራቅ አውሮፓ ሶሻሊስት አገሮችና በሶቪየት ኅብረት እነዚህ ሰዎች የመጀመሪያ ደረጃ አላፊነት የሚኖርባቸው ልጁ የተወሰነ ዕድሜ እስኪሞላው ድረስ ነው። የተለመደው የዕድሜ ገደብም 13 ወይም 15 ዓመት ነው። በነዚህ አገሮች ህጎች መሠረት ልጁ ዕድሜው ከ13 ወይም ከ15 ዓመት በታች ከሆነ ጭራሹኑ አላፊነት አይኖርበትም።[12] ልጁ 13 ወይም 15 ዓመት ከሞላው በኋላ ግን ላደረሰው ጉዳት አላፊ ይሆናል። እንዲሁ ሲሆን የወላጆቹ አላፊነት በሁለተኛ ደረጃ የሚመጣ ይሆናል። ይህም ማለት ወላጆቹ በአላፊነት የሚጠየቁት ልጁ ያደረሰውን ጉዳት ለመካስ የልጁ ሀብት የማይበቃ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው።[13] የኮንቲኔንታል የሕግ ሥርዓቶችን በሚከተሉ ብዙ አገሮች ግን እካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ለሚያደርሰው ጉዳት ከአላፊነት ነፃ እንዲሆን ካለመደረጉም በላይ ልጁ ያለው ሀብት ካሣውን ለመክፈል በቂ ቢሆንም ባይሆንም ወላጆቹ ከአላፊነት አያመልጡም።

ከእንደነዚህ ዓይነቶቹ ጥቃቅን ልዩነቶች በስተቀር በሁለቱም ሁኔታዎች ወላጆቹ ጉዳት ያስከተለው የልጁ ድርጊት እንዳይፈፀም ሊያደርጉ የሚችሉበት ሁኔታ አለመኖሩን ካረጋገጡ ከአላፊነት ነፃ ይሆናሉ። ይህም ማለት ጥፋት አለ የሚለው የሕግ ግምት ተቃራኒ ማስረጃ የማይቀርብበት ነው ማለት አይደለም።[14]

/2/ ጥፋት ለመፈፀሙ ማረጋገጫ ይቅረብ በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ አላፊነት

በኮመን ሎ እና በስካንዲኔቪያን አገሮች የወላጆና ተወላጅ ግንኙነት በመኖሩ ምክንያት ብቻ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ወላጆች ልጃቸው ላደረሰው ጉዳት አላፊ አይደረጉም። አላፊ የሚሆኑት ጉዳቱ የደረሰው እነሱ በፈፀሙት ቸልተኝነት የተሞላበት የቁጥጥር ተግባር ምክንያት መሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ብቻ ነው። በወላጆቹ በኩል የተፈፀመው የመቆጣጠር ተግባር ቸልተኝነት የተሞላበት እንደነበረ የማረጋገጡ ሸክም የወደቀውም በራሱ በተጎጂው ላይ ነው። በዚህ ረገድ ተጎጂውን ለማገዝ የተደነገገ ምንም ዓይነት የሕግ ግምት የለም።[15]

የኢትዮጵያ አመለካከት

በእኛ ሕግ አካለመጠን ያላደረሱ ልጆችን የመቆጣጠር ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች በአማራጭ አባት፣[16] እናት፣ ልጁ ከቤተሰቡ ቤት ውጪ የሚኖር ከሆነ፣ ልጁን በአምነት የተቀበለው የልጁ ጠባቂ፣ የቀለም ትምህርት መምህሩና፣ የሙያ ሥራ አስተማሪ ናቸው።[17] አሠሪውም ከነዚህ ሰዎች ጋራ ተጠቃሏል። ዳሩ ግን ሠራተኛው አካለ መጠን ያላደረሰ ወይም ያደረሰ ቢሆንም ባይሆንም አሠሪው ለሠራኛው ተግባሮች አላፊ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች አንድ ዓይነት[18] ስለሆኑ ይህን ጉዳይ በዚህ ጽሁፍ አናወሳውም።

አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ለመጣበት አላፊነት ሌላ ሰው አላፊ እንዲሆን በመደረጉ ምክንያት ብቻ የኢትዮጵያ ሕግ አካለመጠን ያላደረሰውን ልጅ ከአላፊነት ነፃ ያላደረገው መሆኑ ከመጀመሪያው ሊታወቅ ይገባል። አላፊ ከሚሆነው ሰው ጋራ በመሆን ልጁ ራሱ ላደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍል ይገደዳል።[19]

አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት የመጣበት እንደሆነ አባቱ አላፊ እንደሚሆን በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2124 ተደንግጓል። አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ በሁለት መንገዶች ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ይመጣበታል። ጥፋት ፈፅሞ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። እንዲህ ሲሆን፣ በራሱ ጥፋት አላፊነት ውስጥ ገባ ማለት ነው። እንዲሁም አንድ ለየት ያለ ሥራ ሊያከናውን ይችላል፣ ወይም የአንድ ንብረት ባለሀብት ወይም ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ታዲያ በዚህ በሚያከናውነው ለየት ያለ ሥራ ወይም በባለሀብትነት በያዘው ወይም በሚገለገልበት[20] ንብረት አማካይነት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። በዚህ ጊዜ አላፊነት ውስጥ የሚገባው ጥፋት ስለፈፀመ ሳይሆን ጉዳቱ የደረሰው በሚያከናውነው ሥራ ወይም በባለሀብትነት በያዘው ወይም ለራሱ ጥቅም ሲል በሚገለገልበት ንብረት አማካይነት በመሆኑና በዚህ ዓይነቱ ሁኔታም ያለጥፋት አላፊነት እንደሚኖር ሕጉ ስለሚደነግግ ነው።[21]

ታዲያ ሕጉ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ አላፊነት ሲመጣበት አባት አላፊ ይሆናል ብሎ ሲደነግግ ምን ማለቱ ነው? በጥፋት ላይ ለተመሠረቱት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ዓይነት የልጁ ውል ሳይኖር የሚደርሱ አላፊነቶች አላፊ የሆናል ማለት ነው? ወይስ በሌላ አነጋገር አላፊነቱ የመጣው ልጁ ጥፋት ፈፅሞ ቢሆንም ባይሆንም ልጁ አላፊነት በመጣበት ቁጥር አባቱ ያለጥፋቱ አላፊ ይሆናል ማለት ነው?

በኢትዮጵያ ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ሕግ ላይ ሼጋ መጽሐፍ እንደፃፉት እንደፐሮፌሰር ክሺቺናሺች አመለካከት ከሆነ፣ አካለመጠን ላላደረሰ ልጅ ያለው አላፊነት "በጥፋት ላይ የተመሠረቱትን ብቻ ሳይሆን ውል ሳይኖር የሚደርሱትን አላፊነቶች ሁሉ ያጠቃልላል።"[22] ይህም ማለት፣ ለምሳሌ ማናቸውንም የልጁን አላፊነቶች ሁሉ ያጠቃልላል። ይህም ማለት፣ ለምሳሌ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ የአንድ ሞተር ተሽከርካሪ ባለሀብት ቢሆንና ይኸው የልጁ ሀብት የሆነው ሞተር ተሽከርካሪ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ቢያደርስ፣ የልጁ አባት አላፊ ይሆናል ማለት ነው። ምክንያቱም የእርሱ ንብረት የሆነው ሞተር ተሽከርካሪ በሌላ

ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ልጁ የሞተር ተሽከርካሪው ባለሀብት በመሆኑ ያለጥፋቱ አላፊ ስለሚሆን ነው።[23] ሁኔታው ይኸ መሆኑን ለማብራራት ፐሮፌሰር ክሽቺኖቪች በግርጌ ማስታወሻ የሚከተለውን ምሳሌ ያቀርባሉ።" ልጁ የአንድ እንስሳ ባለሀብት ሊሆንና በቁጥር 2071 ሥር "ጥብቅ" አላፊነት ሊመጣበት ይችላል። ይህ ሁኔታ አባቱን /ቁጥር 2124/ ወይም ሌላ "አሳዳሪውን" /ቁጥር 2125/ አላፊ ለማድረግ በቂ ይሆናል።"[24] ፐሮፌሰር ክሺቺኖቪች እንዳደረጉት ሁሉ አንድ ሰው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2124ን ከቁጥር 2027/3/ ጋራ አጣምሮ በማንበብ እንዲህ ካለው መደምደሚያ ላይ ሊደርስ ይችላል። ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት የመጨረሻው ምንጭ የሆነው ቁጥር 2027/3/ አንድ ሰው አንድ ሌላ ሰው በጥፋት ምክንያት ወይም በህግ በተደነገገው ሁኔታ አላፊነት ሲኖርበትና ሕጉ ለዚህ ሰው አላፊ እንዲሆን ሲያደርገው አላፊ ይሆናል "በማለት ይደነግጋል። እንግዲህ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው ከቁጥር 2028 እስከ 2065 ወይም ከቁጥር 2066 እስከ 2089 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት አላፊነት ሲመጣበት፣ ማለትም በጥፋቱ ወይም ጥፋት በሌለበት ሥራው /ለምሳሌ ቁጥር 2066 እና 2067/ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሲያደርስ፣ ወይም እርሱ ጥፋት ሳይኖርበት የራሱ ሀብት የሆነ ንብረት /ቁ. 2071፣ 2077፣ 2081/፣ ወይም ለግል የሚገለገልበት የሌላ ሰው ንብረት /2072 እና 2082/፣ በሰው ላይ ጉዳት ሲያደርስ ሕጉ ለዚህ ሰው አላፊ ትሆናለህ ያለው ሌላው ሰው አላፊ ይሆናል ማለት ነው። የሆነ ሆኖ፣ ምንም እንኳን ይህ ድንጋጌ የሚናገረውን የሚል ቢመስልም፣ አንድ ሠራተኛ ወይም ደረሲ ከቁጥር 2066 እስከ 2089 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት አላፊነት ሲመጣበት ሌላው ሰው አላፊ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ የለም። እንደእውነቱ ከሆነ ሠራተኞችን በሚመለከት አሠሪው አላፊ የሚሆነው ሠራተኛው የተሰጠውን ሥራ ሲያከናውን /ቁጥር 2129፣ 2130 እና 2131 ተጣምረው ሲነበቡ/ ወይም የተመደበበትን የመንግሥት ሥራ በሚያከናውንበት ጊዜ /ቁጥር 2126/2/ እና ቁጥር 2127/1/ ተጣምረው ሲነበቡ/ ጥፋት ፈፅሞ የተገኘ እንደሆነ ብቻ ነው። ሠራተኛው ለሚፈጽማቸው ሌሎች ጥፋቶች አላፊነት አይኖርም። ደራሲያንን በሚመለከትም ለሌላ ሰው ተግባር አላፊ እንዲሆን የተደረገው ተከሳሽ አላፊ የሚሆነው ለስም ማጥፋት ብቻ ነው /ቁጥር 2135/። እንግዲህ "ልዩነት" ያለው አካለመጠን ያላደረሰ ልጅን በሚመለከት ብቻ ይመስላል። አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ በራሱ ጥፋት

ወይም ያለተፋቱ አላፊነት ውስጥ ሲገባ /ለምሳሌ ከ2066 እስከ 2089 ባሉት ቁጥሮች መሠረት/ በቁጥር 2124 መሠረት በፍትሐብሔር በኩል ላለው ጉዳይ አባቱ አላፊ የሚሆን ይመስላል። በተጨማሪም፥ አንድ ሰው ቁጥር 2124 እና 2027/3/ን አጣምሮ በማንበብ የሚደርስበት ትርጉም ይኸ ከሆነ ደግሞ፥ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ አባት ብቻ ሳይሆን በልጁ ላይ አላፊነቱ በመጣ ጊዜ ልጁ በግን ቁጥጥር ሥር እንደነበር በማየት ብቻ በቁጥር 2125 ሥር የተዘረዘሩት ሌሎች የልጁ "አሳዳሪዎችም" ልጁ አላፊነት ውስጥ በገባ ቁጥር የፍትሐብሔር አላፊነት ይኖርባቸዋል ማለት ነው። ይህም የሚሆንበት ምክንያት የልጁ ሌሎች "አሳዳሪዎች" በልጁ አባት ምትክ በአላፊነት ስለሚጠየቁ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፥ ሕጉ በሁለንተናዊ አቋሙ ሲተረጎም የልጁን አባትና የሌሎቹን አሳዳሪዎች አላፊነት አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ አንድን ድርጊት በገቢር ፈጽሞ አላፊነት ውስጥ በሚገባባቸው ሁኔታዎች ላይ ብቻ የገደበው ይመስላል። ለሌላ ሰው ተግባር[25] አላፊ ስለመሆን የሚለው የክፍል 4 ርዕስ ሲጤንም ትርጉሙ ይኸው ይመስላል። ከዚሁ ጋራ የሚጣጣመው የቁጥር 2124 የአማርኛ ትጅም አባቱንና ሌሎች አሳዳሪዎቹን አላፊ ለማድረግ በልጁ በኩል በገቢር የተፈፀመ ድርጊት እንዲኖር ያዛል። "አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ አላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሠራ እንደሆን ..." በማለትም ይደነግጋል /ሥርዝ የተጨመረ/። እንዲሁም በዚሁ ክፍል ሥር የሚገኘው ቁጥር 2136 የእነዚህን ሰዎች አላፊነት ልጁ ድርጊት ፈፅሞ ጉዳት በሚያደርስበት ሁኔታ ላይ ብቻ ገድቦታል።[26]

የሆነው ይሁንና ለመሆኑ ወላጆችና አካለመጠን ያላደረሰ ልጅን የመቆጣጠር ሥልጣን የተሰጣቸው ሌሎች ሰዎች አላፊ እንዲሆኑ የተደረገበት መሠረታዊ ምክንያት ምንድን ነው? እስቲ በብዙ አገሮች የፍትሐብሔር ህጎች ላይ ተፅዕኖ ያሳደረውን የ1804 ቱን የፈረንሳይ የፍትሐብሔር ሕግ ካረቀቁት ሰዎች መካከል ትሬይልሃርድ የተባሉት ሰው በዚህ ጉዳይ ላይ ብለውት የነበረውን እንመልከት። እርሳቸው

እነዚያ የአላፊነት ሸክም የተጫለባቸው ቢያንስ፥ ገሚሶቹ በልልነት፥ ገሚሶቹ ደግሞ በእትል አመራረጥ፥ ሁሉም ደግሞ በደንታቢስነት ሊነወሩ ይችላሉ። መጥፎ አርአያ ባለመሆንና ጠንቀኛ የሆኑ አስተሳሰቦችን ባለማስተማር ራሳቸውን ከሕሊና ወቀሳ ነፃ ያደረጉ እነዚያ ብቻዎን ናቸው። _ይህ አላፊነት የቤተሰብ አባወራዎችን ይበልጥ አስቱዋይና ጥንቁቅ እንዲሆኑ_ ...፥ _ደግሞም የግዴታቸውን አጥናፍና ቅድስና በይበልጥ እንዲገነዘቡ ያድርጋቸው_! በጎ ሥነ ምግባርን እንዲቀሰሙ በማድረግ መልካም ዜጎች እንዲሆኑ ካላዘጋጁናቸው በቀር ለልጆቻችን የምንቸረው ሕይወት በረከት አይደለም፥"[27] ብለው ነበር /ሰርዝ የተጨመረ/።

እንግዲህ አካለመጠን ያላደረሱ ልጆችን የመቆጣጠር ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ልጆች ለሚፈፅሙት ተግባር በፍትሐብሄር በኩል አላፊ እንዲሆኑ የተደረገው በእነዚህ ምክንያቶች[28] ነበር፥ አሁንም ነው። "እንዲህ ያሉት ሰዎች በልጆቻቸው አዕምሮ ውስጥ የሌሎች ሰዎችን ጥቅም የማክበር በጎ አስተሳሰብ እንዲሰርፅ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፤ በሌሎች ጥቅም ላይ ልጆች ጉዳት ካደረሱሁኔታው እነኚህ ሰዎች ተገቢ ሥነ ሥርዓት የማስተማር ግዴታቸውን አለመወጣታቸውን የሚያንፀባርቅ ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱ ግዴታን አለመወጣት ደግሞ እንደጥፋት ይቆጠራል።"[29]

ከዚህ በላይ ከተገለፀው መሠረተ ሀሳብ ጋራ በመጣጣም ቀደም ሲል እንዳየነው በሲቪል የሕግ ሥርዓት አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ባደረሰ ቁጥር የልጁ ወላጅ ወይም አሳዳሪ የመቆጣጠር ተግባሩን በማከናወን ረገድ ጥፋት ፈጽሟል ተብሎ ይገመታል። ይሁን እንጂ የጉዳቱን መድረስ _ለማስቀረት ፈፅሞ አይቻል እንደነበረ_[30] በማስረዳት ጥፋት ፈፅመሃል የሚለውን የሕግ ግምት ለመቃወምና ከአላፊነት ነፃ ለመሆን ይችላል።

በሶሺየት ኅብረትና በምሥራቅ አውሮፓ የሶሻሊስት አገሮች አንድ ወላጅ እካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ላደረሰው ጉዳት አላፊ የሚሆነው ልጁን በመቆጣጠር ረገድ ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ ነው።

በኮመን ሎ እና በስካንዲኔቪያን አገሮች ወላጅ የወላጅ ተወላጅ ግንኙነት በመኖሩ ምክንያት ብቻ ልጁ ላደረሰው ጉዳት አላፊነት አይኖርበትም። እዚያ የወላጁ አላፊነት የተመሠረተው በራሱ የቸልተኝነት ተግባር፥ ማለትም ተገቢ የሆነ ቁጥጥር ባለማድረግ፥ ላይ ነው። ወላጁ በልጁ ላይ ያለውን የመቆጣጠር ተግባር ችላ ባይል ኖሮ ለልጁ የጥፋት ተግባር በአላፊነት ባልተጠየቀም ነበር።

ተደም ሲል የተገለፀው የሚያረጋግጠው በሁሉም የሕግ ሥርዓቶች የወላጁ ወይም የአሳዳሪው አላፊነት ገደብየለሽ አለመሆኑን ነው። አላፊነቱ ጉዳት በመድረሱ ወይም የወላጅና ተወላጅ ወይም የአሳዳሪና የልጅ ግንኙነት በመኖሩ ምክንያት ብቻ የሚመጣ ሳይሆን፥ ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው እካለመጠን ያላደረሰውን ልጅ በመቆጣጠር ረገድ የፈፀመው ጥፋት መኖሩ ሲረጋገጥ /ወይም ጥፋት ተፈፅሟል የሚል ግምት ሲወሰድ/ ብቻ የሚፈጠር ነው።

ተደም ሲል ከተገለፁት የሕግ ሥርዓቶች የእኛ ሕግ የተለየ ነውን? በተለይ የእኛ የፍትሐብሄር ሕግ የኮንቲኔንታል የሕግ ሥርዓት ተፅዕኖ ያለበት መሆኑ ከግምት ውስጥ ሲገባ፥ ይህን አላፊነት ጥፋት አለ በሚል የሕግ ግምት ላይ ከመሠረቱት የሕግ ሥርዓቶች ልዩ ነው ማለት ይቻላል? በዚህ ጉዳይ ላይ የእኛ ሕግ በመላው ዓለም ካሉት የሕግ ሥርዓቶች ሁሉ ጨርሶ የተለየ ነው በማለት እካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት በመጣበት ቁጥር፥ አላፊነቱ የመጣው በጥፋትም ሆነ ያለጥፋት፥ የልጁ አባት ወይም አሳዳሪ አላፊ ይሆናል የሚል አቋም መያዝ ሁኔታውን ትርጉም የለሽ አያደርገውምን? እካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች ያለው አላፊነት የመቆጣጠር ተግባሩ ቸልተኝነት የተጓላበት ነው በሚል የሕግ ግምት ላይ የተመሠረተ ነው እንደሚል አድርጎ የእኛን ሕግ መተርጎም አይቻልምን?

የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች ያለውን አላፊነት የሚወስኑትን የእኛን የፍትሐብሄር ሕግ ድንጋጌዎች አላፊነቱ የተመሠረተው በሲቪል የሕግ ሥርዓቶች እንደተደረገው በቸልተኝነት የመቆጣጠር ሁኔታ ላይ እንጂ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ አላፊነት ውስጥ የገባ መሆኑን በሚያሳይ ሐቅ ላይ ብቻ፣ ወይም የወላጅና ተወላጅ ወይም የሞግዚትና የልጅ ግንኙነት መኖሩ በመረጋገጡ ሐቅ ላይ ብቻ የተመሠረተ አይደለም ብሎ ለመተርጎም የሚያስችል መንገድ አለ ብሎ ያስባል። በርግጥም ሁኔታው ይህ ለመሆኑ አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች አላፊ እንዲሆኑ የተደረጉት ሰዎች አመራረጥ ፍንጭ ይሰጣል። መጀመሪያ ነገር አላፊነቱ ምትካዊ ሲሆን አካለመጠን ባደረሰው ልጅ ላይ የአባትነት ሥልጣን ወይም የመቆጣጠር ኃላፊነት መኖርን ይጠይቃል። በመጀመሪያ ደረጃ አላፊ የተደረገው አባት ነው። ይህም አባት የቤተሰብ የበላይ አስተዳዳሪ[31] በመሆኑ ሮማውያን _ፓትሪያ ፖተስታስ_ ከሚሉት የአስተዳዳሪነት ሥልጣን ጋራ ግንኙነት ያለው ይመስላል። በርዕሰ ቤተሰብነቱ አባት አካለመጠን ያላደረሱ ልጆቹን ምግባርና እንቅስቃሴዎቻቸውን ብቻ ሳይሆን የሚሰቱንም ተግባሮች ጭምር የመቆጣጠር ሥልጣን አለው።[32] ይህን በተጨባጭ የሚታወቀውንና ሕጋዊም የሆነውን ሥልጣን በመገንዘብ ይመስላል በእኛ ኅብረተሰብ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ልጆች ለአባቶቻቸው የሚሰጡት አክብሮት ለእናቶቻቸው ከሚሰጡት ልቆ የሚታየው። ሕጉም አባትን አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ለሚያደርሰው ጉዳት አላፊ እንዲሆን ያደረገው ይህንኑ አባታዊ ሥልጣን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይመስላል።

እናት ተጠያቂ የምትሆነው በአባት እግር ተተክታ[33] ሲሆን፣ ልጁ አላፊነት ውስጥ በገባበት ጊዜ በልጁ ላይ አባታዊ ሥልጣን የነበራት ከሆነ ብቻ ነው። ብዙውን ጊዜ እናት አባታዊ ሥልጣን የሚኖራት አባት ከሞተ፣ ችሎታ ካጣ፣ ከጠፋ፣ ወይም ቤተሰቡን በትኖ በመሄዱ የተፈረደበት እንደሆነ ነው።[34] ባልና ሚስቱ አብረው በትዳር መኖራቸው በፍቺ ምክንያት አክትሞ የቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች የልጁ ሞግዚት እንድትሆን በሚወስኑበት ጊዜም እናት ይህ የአባታዊ ሥልጣን ይኖራታል።[35] በተጨማሪም፣ ከጋብቻው በፊት በወለደችው ልጅ ላይ ሙሉና ብቸኛ ሥልጣን

አሳት።[36] እንግዲህ በእነዚህ ሁኔታዎች ነው እናት አካለመጠን ያላደረሰ ልጅዋ ለፈፀማቸው ተግባሮች አላፊ የምትሆነው።

ሌሎች የልጁ አሳዳሪዎችም በአባት አላፊነት ምትክ አላፊ እንዲሆኑ ተደርጓል። አላፊነታቸው ግን ልጁ አላፊነት ውስጥ በገባ ጊዜ በልጁ ላይ የመቆጣጠር ሥልጣን የነበራቸው ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። ልጁ ከቤተሰቡ ቤት ውጭ የሚኖር ከሆነ ማድረግ የሚገባውንና የማይገባውን መቆጣጠር ያለበት ልጁን እንዲጠብቅ በእምነት የተሰጠው ሰው ነው። በመሆኑም በጥበቃው ሥር እንዳለ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ አላፊነት ውስጥ ከገባ አላፊ የሚሆነው ይኸው ሰው እንጂ የልጁ ወላጆች አይደሉም።[37] ልጁ በቁጥጥራቸው ሥር ስላልነበረ አላፊነት ውስጥ የገባው ተገቢ ቁጥጥር ባለማድረጋቸው ነው ለማለት አይቻልም።

አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ በትምህርት ቤት ውስጥ እያለ አላፊነትን የሚያስከትል ሥራ ከሠራ አላፊ የሚሆነው የቀለም ትምህርት መምህሩ ነው።[38] አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት የአደጋ ሁኔታዎች ከፍተኛ በሆኑበት በትምህርት ቤቶች ወይም በመሰል የትምህርት መስጫ ተቋሞች መሆኑ ግልፅ ነው። በመሆኑም የቀለም ትምህርት መምህሩ አላፊነት የሚያስነሳቸው ችግሮች ልዩ ትኩረት ሊሠጣቸው ይገባል። የዘመኑ የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ቢያንስ አንድ መምህር መመደብን የሚጠይቅ በመሆኑ፥ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያስተምሩት መምህራን ቁጥር ብዙ ነው። የቀለም መምህሩም የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪም አንድ ሰው ብቻ የነበረባቸው ዘመናት ነጉደዋል። ይህ ዓይነቱን የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት በሥራ ላይ ማዋል ይቻል የነበረው በገጠማት በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ነበር። ስለዚህ፥ አሁን ባለው ሁኔታ የመቆጣጠር ተግባሩን ያጓደለውን መምህር ነጥሎ ማውጣት ቀላል አለመሆኑን ማስተዋል እያዳግትም። የአንድ ትምህርት ቤት መምህራን በሙሉ በጋራ አላፊ ሊሆኑ ይገባል? ወይንስ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም አስተዳዳሪ ብቻውን አላፊ ይደረግ? እንዴት አድርጎ ነው በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ተማሪዎችን በአንድ ጊዜ ሊቆጣጠር የሚችለው?

ብዙውን ጊዜ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እየተናቆሩ አንዱ በሌላው ላይ ጉዳት የሚያደርሰው አስተማሪው በክፍል ውስጥ በሚያስተምርበት ጊዜ ሳይሆን በእረፍት ጊዜያቸው ወይም የክፍል ትምህርት ከመጀመሩ በፊት በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲያምቧቹ ነው። በነዚህ ሰዓታት መምህራኑ በተማሪዎቻቸው የመምቧቻ ሥፍራ እንዲገኙና ተግባሮቻቸውን እንዲቆጣጠሩ ይጠበቅባቸዋል? በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገኙት የግልና የመንግሥት ሠራተኞች አካለመጠን ያላደረሱ ልጆችን የሚያስተምሩ በመሆኑ ብቻ የእንዲህ ያለው አላፊነት ቀንበር ተሸካሚ እንዲሆኑ ማድረግ አግባብ ነውን? ካሣ የመክፈሉን አላፊነት ወደ መምህሩ ቀጣሪ ማዛወር ተገቢ አይሆንም?

በጀርመን አገር መምህራን እንደመንግሥት ሠራተኞች ይቆጠራሉ። በመምህሩ የሚከናወነው የመቆጣጠር ጥፋትም የመንግሥት የሥራ ግዴታዎችን እንደመጣስ የሚታይ ነው። በዚህም መሠረት ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ እያሉ ባደረሱት ጉዳት ምክንያት የሚመጣውን የመምህራን አላፊነት መንግሥት የሚሸከመው ይሆናል።[39] በተጨማሪም በመምህራን በኩል ጥፋት አለ የሚለው የሕግ ግምት በጀርመን አገር ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ተደርጓል። ፈረንሳይም እንዲሁ መምህራንን በሚመለከት ጥፋት አለ የሚለው የሕግ ግምት ተፈፃሚነት እንዳይኖረው አድርጋለች። በዚህም ምክንያት አንድ ተማሪ በፈፀመው ተግባር ጉዳት የደረሰበት ሰው በመቆጣጠር ረገድ መምህሩ ጥፋት የፈፀመ መሆኑን የሚያስረዳ ማረጋገጫ በቅድሚያ ማቅረብ አለበት።[40]

እኛስ ይህን አስተሳሰብ በመከተል፣ ባይሆን እንኳን ለወደፊቱ፣ በመምህሩ ፋንታ ትምህርት ቤቱን አላፊ ማድረግ ይኖርብን ይሆን? ትምህርት ቤቱ አላፊ የሚሆን ከሆነ መምህራን ያለባቸውን የመቆጣጠር ተግባር በሚገባ ላያከናውኑ ይችላሉ የሚል ስጋት ይፈጠር ይሆን? ይኸ የእውን ፍራቻ ከሆነ የመምህሩ አላፊነት እንዲቀጥል ማድረግ ይቻላል። ይህ የሚሆነው ግን የመምህሩ ጥፋት የተለየ ክብደት ያለው ሆኖ በሚገኝበትና መምህሩ በመቆጣጠር ተግባሩ ላሳየው ጉድለት በቅድሚያ ማረጋገጫ በማቅረብ የማስረዳቱ ሸክም የተበዳዩ ወይም የትምህርት ቤቱ እንዲሆን በተደረገበት ሁኔታ ብቻ

መሆን ይኖርበታል። አሁን በሚሠራበት ሕጋችን ግን አንድ መምህር ተማሪዎቹ ላደረሱት ጉዳት አላፊ መሆን ብቻ ሳይሆን ተገቢ ያልሆነ የመቆጣጠር ተግባር ተፈፅሟል የሚለውን የጥፋት መኖር ግምት እንኳን ለመቃወም የሚችልበት መንገድ የለውም።

አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ የሙያ ትምህርት በለማጅነት በሚቀሰምበት ጊዜ ጉዳት ቢያደርስ የሙያ አስተማሪውም ልክ እንደ ቀለም መምህሩ አላፊነት ይኖርበታል። ይሁን እንጂ፥ በለማጅነት የሚቀጠሩት ዕድሜአቸው ከአሥራ አራት ዓመት በላይ የሆኑት በመሆኑ የሙያ አስተማሪው ያለበት አላፊነት የቀለም መምህሩ ያለበትን አላፊነት ያህል የሠፋ አይመስለኝም። እነኚህኞቹ ልጆች አካለመጠን ለማድረስ እየተቃረቡና በአዕምሮ በሰል እያሉ በመሆኑ አላፊነትን ለመሸከምና ከአስነዋሪ ተግባር ራሳቸውን ለማቀብ ዝግጁ የሆኑ ይመስላል።

የአንቀጽ 13 ምዕራፍ 1 ክፍል 4፥ ርዕስ፥ ቁጥር 2136 እና የቁጥር 2124 የአማርኛ ቅጅ የአባት ወይም የሌላ የማንኛውም አሳዳሪ አላፊነት አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ በሚፈፅማቸው ተግባሮች ጉዳት በሚያደርስበት ሁኔታ ላይ ብቻ የተወሰነ መሆኑን ይጠቁማሉ። አንድ ሰው እነዚህን ሁሉ በአንድነት ቢያጤን በሌሎች የሲቪል የሕግ ሥርዓቶች እንደሚታየው ሁሉ በኛም ሕግ አካለመጠን ላላደረሱ ልጆች ተግባሮች ያለው አላፊነት የመቆጣጠሩ ተግባር ቸልተኝነት /ማለትም የአጥፊነት ሁኔታ/ አለበት በሚል ግምት ላይ የተመሠረተና አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ በራሱ ጥፋት አላፊነት ውስጥ በሚገባበት ሁኔታዎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ እንደሚደርስ ግልፅ ነው። ያለው ልዩነት በእኛ ሕግ ከአቅም በላይ[42] በሆነ ምክንያት ካልሆነ በቀር ይህን የሕግ ግምት መቃወም የማይቻል መሆኑ ብቻ ነው።

አካለመጠን ያላደረሱ ልጆችን እንዲቆጣጠር አላፊነት በተጣለበት ሰው ላይ የተጣለው ይህ አላፊነት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ካሣ እንዲያገኙ ዋስትና መሆኑ ግልፅ ነው። ዳሩ ግን፥ እንዲህ ዐይነቶቹ ዋስትናዎች አዕምሮ ሊቀበላቸው በሚችለው

ገደቦች ውስጥ እንዲወሰኑ ርትዕና ፍትሕ ያስገድዳሉ። አካለመጠን ላላደረሱ ልጆች የሚኖረው አላፊነት በጥፋት ላይ የተመሠረተውን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ውል ሳይኖር የሚደርሱ አላፊነቶች ይሸፍናል የሚል አቋም ከተወሰደ፥ ለምሳሌ ሀብትነቱ የአንድ አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ የሆነ እንስሳ ወይም ሞተር ተሽከርካሪ[43] በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሲያደርስ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ያለጥፋቱ አላፊ ስለሚሆን፥ ልጁ ይህ አላፊነት በመጣበት ጊዜ በማን ተቆጣጣሪነት ሥር እንደነበረ በመመልከት ብቻ እንደነገሩ ሁኔታ ከልጁ ወላጆች አንዱ ወይም በቁጥር 2125 ሥር ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል አንደኛው አላፊ እንዲሆን ይደረጋልማለት ነው። ፕሮፌሰር ክሽቼኖቪች በግርጌ ማስታወሻ ያሉትም ይኸንኑ ነው።[44] ይህ ዓይነት አላፊነት አግባብ መሆኑን ለማሳየት ምን አሳማኝ ምክንያት ሊቀርብ ይችላል? እንዲያው ዝም ብሎ ልጁ በትምህርት ገበታ ላይ በነበረበት ጊዜ እንዲህ ዓይነት አላፊነት የመጣበት መሆኑን መሠረት በማድረግ በቻ የቀለም ትምህርት መምህሩ አላፊ መሆን ይኖርበታል? አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ለማጅ ሆኖ በሚያገለግልበት የሥራ ቦታ ሳለ እንዲህ ዓይነቱ አላፊነት የመጣበት በመሆኑ ብቻ የሙያ አስተማሪው አላፊ ሊሆን ይገባል? ወላጆቹስ ቢሆኑ የእነዚህ ነገሮች ሀብትነት የልጃቸው በመሆኑ ምክንያት ብቻ አላፊ መሆን አለባቸው? የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ እንዲህ ባሉት ሁኔታዎች እነዚህን ሰዎች አላፊ ለማድረግ አሳማኝና አግባብ የሆነ አንዳች ምክንያት አይታየውም። አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ያለጥፋቱ አላፊ እንዲሆን በተደረገባቸው ሁኔታዎች እነዚህን ሰዎች አለፊ ማድረግ በእነሱ ላይ ማሕበራዊ ኢፍትሕ መፈፀም ይሆናል። በእርግጥም "እንዲህ ዓይነቱ የፍትሐብሄር አላፊነት በወንጀል ጉዳይ በአንድ ንፁሕ ሰው ላይ ከሚሰጥ የቅጣት ፍርድ ጋራ የሚተካከል ይሆናል።"

እንዲህ ባሉት ሁኔታዎች አላፊ መሆን ያለበት የንብረቱ ባለሀብት ወይም ጠባቂ ብቻ ነው። በአንዳንድ የተግባር ክንዋኔዎች ወይም በንብረቶች በመገልገል ምክንያት ጉዳት የሚደርሰው፥ የፕሮፌሰር ክሽቼኖቪችን አነጋገር ለመጠቀም "እጅግ ጠንካራ በሆነ የጥንቃቄ መመዘኛ እንኳን ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማድረግ በማይቻልበት፥ ወይም እጅግ ደካማ በሆነ የማረጋገጫ መመዘኛ እንኳን የጥፋት ማስረጃ ለማግኘት በሚሳንበት ሁኔታ"[45] እንደሆነ ልብ ማድረግ ያሻል። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቶች

ሁኔታዎች በተጠቀሱት ንብረቶች በመገልገል ወይም አንዳንድ ሥራዎችን በማከናወን ጥቅም የሚያገኘው ተከሳሹ ስለሆነ ተበዳዩ ተጎድቶ የሚተርፍበት ምንም ምክንያት የለም። በእነዚህ ሁኔታዎች ኪሳራው ወደ ንብረቶቹ ባለሀብት ወይም ተገልጋይ ወይም ወደ ሥራው ተጠቃሚ እንዲዛወር ርትዕ ያስገድዳል።

ስለዚህ ከቁጥር 2124 እስከ 2125 ያሉትን እና በተጣጣሚነት የቁጥር 2027/3/ ድንጋጌዎችን በጥንቃቄና በአንክሮ በማጤን /የክፍሉን ርዕስና ቁጥር 2136ን በመጨመር/ የተገናዘበ ፍቺ ካልሰጠናቸው በቀር ድንጋጌዎቹ የልጅ ወላጆችና ሌሎች አሳዳሪዎች አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ለሚመጣበት ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነቶች ሁሉ አላፊዎች ናቸው የሚሉ መስለው ይታያሉ። በተለይ የእንግሊዝኛው ትርጉም ሲመረመር ይህንን መስዕክት መያዙ ግልፅ ነው። ወሳኙነት ያለው የአማርኛ ትርጉም ግን አላፊነቱን አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ በሚፈፅማቸው ተግባሮች ጉዳት በሚደርስበት ሁኔታ ላይ ብቻ የገደበው ይመስላል። በአማርኛው ትርጉም መሠረት አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ድርጊት ፈፅሞ አላፊነት ውስጥ ሲገባ የተፈፀመው ድርጊት ጥፋት ቢሆንም ባይሆንም አባቱ ወይም የልጁ አሳዳሪ አላፊ ይሆናል። ነገር ግን ልጁ ድርጊት ሳይፈፅም አላፊነት ቢመጣበት፣ ለምሳሌ የእርሱ እንስሳ ወይም ታክሲ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት አድርሶ እንደሚገኝበት ባለ ሁኔታ፣ ባለሀብት ከሆነው ከራሱ ከልጁ በቀር ማንም በአላፊነት አይጠየቅም።

በሌላ በኩል፣ የአንቀጽ 13 ምዕራፍ 1 ክፍል 4 ርዕስንና የቁጥር 2136ን ድንጋጌ ወደጎን በመተው የቁጥር 2124ን የእንግሊዝኛ ትርጉም ብቻ መመልከት እነዚህ ሰዎች ለሁሉም የልጁ አላፊነቶች ተጠያቂ ናቸው ከሚል መደምደሚያ ላይ ያደርሳል። ይህ መደምደሚያ በተግባር ላይ ይዋል ቢባል ደግሞ ሁኔታው ፍቺ አልባና ስሜት የለሽ ይሆናል።

ማጠቃለያ

ከፍ ብሎ ከተሰጠው ትንታኔ በመነሳት እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል።

1. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2124 እና 2125 የተጠቀሱት ሰዎች ያለባቸው አላፊነት የመቆጣጠሩ ተግባር ተገቢ አልነበረም በሚል የጥፋት ግምት ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ በቁጥር 2125 ሥር የተዘረዘሩት ሰዎች በተለይም የቀለም መምህሩ፥ የሞያ አስተማሪውና ልጁን በእምነት የወሰደው የልጁ ጠባቂ አላፊ እንዲሆኑ ባልተደረገ ነበር። እንዲሁም የልጁ እናት አላፊ የምትሆነው በአባትየው ምትክ ባልሆነ ነበር። ይልቁንም አላፊነቷ የጋራ በሆነ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ዕብዶች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች አላፊነት በኖረ ነበር። እነዚህ ሁሉ ነጥቦች የሚያረጋግጡት የአባትና የሌሎች አሳዳሪዎች አላፊነት የተመሠረተው እነዚህ ሰዎች ያለባቸውን የመቆጣጠር ተግባር በአግባቡ ላይፈፅሙ በመቅረታቸው እንጂ የወላጅና ተወላጅ ወይም የአሳዳሪና የልጅ ግንኙነት በመኖሩ ወይም በተበዳዩ ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት ብቻ አለመሆኑን ነው።

2. አላፊነቱ የተመሠረተው የመቆጣጠሩ ተግባር ተገቢ አልነበረም በሚል የጥፋት ግምት ላይ በመሆኑም እካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ያለጥፋቱ አላፊ እንዲሆን በተደረገባቸው ሁኔታዎች ወላጆች ወይም ሌሎች አሳዳሪዎች አላፊነት አይኖርባቸውም።

3. በእኛ ሕግ እካለመጠን ላላደረሰው ልጅ አላፊ እንዲሆን የተደረገው ተከላሽ ጥፋት አለ የሚለውን የሕግ ግምት ለማፍረስ ተቃራኒ ማስረጃ ለማቅረብ አይችልም።

<u>የማጠቃለያ ሀሳብ</u>

እካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች ያለው አላፊነት ቁጥጥሩ ጉድለት አለው በሚል የጥፋት ግምት ላይ የተመሠረተ ነው። የሲቪል የሕግ ሥርዓትን በሚከተሉ አገሮች ሁሉ ሁኔታው ይኸንኑ ይመስላል። ይህን የጥፋት ግምት ተፈፃሚ ማድረግ ተገቢ ነው። ምክንያቱም "ብዙውን ጊዜ ተበዳዩ ጉዳቱ ከመድረሱ

አስቀድሞ ከልጁ ወይም ከወላጆቹ ጋራ ትውውቅ የሌለው ሊሆን ስለሚችልና የቁጥጥር ግዴታ መኖሩን ለማስረዳት በማይችልበት ሁኔታ ላይ ስለሚገኝ በቁጥጥር ረገድ ስለተፈፀመው ጥፋት ማረጋገጫ ለማቅረብ ያስቸግረዋል። በዚህም ምክንያት ተበዳዩ በማስረጃ አቀራረብ ረገድ ከልጁ አሳዳሪዎች አኳያ ሲታይ ለእሱ ሸክሙ የበለጠ ይከብደብታል።[46] ይሁን እንጂ ገምቱን ለማፍረስ እንደማይቻል አድርጎ መደንገጉ ትክክል አይመስልም። አካለመጠን ያላደረሰ ልጅን የመቆጣጠር ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች በእነርሱ በኩል የቁጥጥር ጉድለት አለመኖሩን የሚያሳይ ማረጋገጫ በማቅረብ ካለባቸው አላፊነት ነፃ እንዲሆኑ መፍቀድም አግባብና በሕሊና ዳኝነት የሚደገፍ ነው።

በወደፊቷ ኢትዮጵያ የተጋቢዎች እኩልነት በሕግ እንደሚረጋገጥ ተስፋ እናደርጋለን። በዚያን ጊዜም የወላጅነት ሥልጣን በአባትና በእናት በጋራ የሚሠራበት ይሆናል። እንዲህ ሲሆን አባትና እናት የሚኖርባቸው አላፊነት ምትክዊ በመሆን ፋንታ የጋራ መሆን ይኖርበታል።

መምህራንን በሚመለከት ግን ግምቱ አግባብ ያለው አይመስልም። በጥቂት የግል ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩት በቀር መምህራን የመንግሥት ተቀጣሪ ሠራተኞች ናቸው። ከሌሎቹ የመንግሥት ሠራተኞች ተነጥለው እንዲህ ያለው ከባድ የሆነ አላፊነት ለምን ይጫንባቸዋል? ቢያንስ ያለባቸውን ሸክም ለማቃለል መምህሩ በተማሪው ላይ ተገቢውን ቁጥጥር አለማድረጉን የማስረዳቱን ግዴታ በተበዳዩ ላይ ማድረግ ይገባል። ከዚህም ይልቅ ጉዳት የደረሰበት ሰው ካሣ ሊያገኝ የሚችልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ሲባል ካሣ የመክፈል ግዴታውን የመምህሩ ጥፋት እጅግ ከባድ በሆነበት ልዩ ሁኔታ ካልሆነ በቀር በትምህርት ቤቱ ላይ መጣሉ /የግልም ቢሆን የመንግሥት/ የተሻለ ይሆናል።

እላይ የተሰጡትን ምክንያቶች መሠረት በማድረግ የፍትሐብሔር ሕጉን አራተኛ መጽሐፍ እንዲያሻሽል የተሰየመው የሕግ አሻሻይ ኮሚቴ በቁጥር 2124 እና 2125 ምትክ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች እንዲቀበላቸው እናሳስባለን።

ቁጥር 2124 - የወላጆች አላፊነት

1) አባትና እናት አካለ መጠን ባላደረሰው ልጃቸው ላይ የጋራ የወላጅነት ሥልጣን ካላቸው ልጁ በጥፋቱ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት በሚያደርስበት ጊዜ፣ ጉዳቱ የደረሰው ተገቢ የሆነ ቁጥጥር ባለማድረጋቸው ምክንያት አለመሆኑን ካላስረዱ በቀር፣ በፍትሐብሔር በኩል በጋራ አላፊ ይሆናሉ።

2) በልጁ ላይ የወላጅነት ሥልጣን ያለው ከወላጆቹ አንደኛው ብቻ ከሆነ ይኸው ወላጅ ብቻውን አላፊ ይሆናል።

ቁጥር 2125 - የልጅ ሌሎች አላፊዎች

1) የሚከተሉት ሰዎች በወላጆች ምትክ አላፊ ይሆናሉ።
   (ሀ) አካለ መጠን ያላደረሰው ልጅ ከቤተሰቡ መኖሪያ ቤት ውጭ ሲኖር በእምነት የተሰጠው የልጅ ጠባቂ፣
   (ለ) ልጁ በትምህርት ቤት ባለበት ጊዜ ትምህርት ቤቱ፣
   (ሐ) ልጁ የሙያ ሥራ በሚለማመድበት ጊዜ የሙያ አስተማሪው።

2. በዚህ ቁጥር ንዑስ ቁጥር 1/ለ/ በተገለፀው ሁኔታ ጉዳት ለደረሰበት ሰው ካሣ የከፈለ ትምህርት ቤት የመምህሩ ጥፋት በጣም ከባድ መሆኑን ካረጋገጠ የከፈለውን የካሣ ገንዘብ መምህሩ እንዲተካለት ለመጠየቅ ይችላል።

በዚህም መሠረት በቁጥር 2027 /3/ ውስጥ "ወይም በሕግ መሠረት" የሚለው ሐረግ ምንም ዓይነት አግባብነት ስለሌለው መሠረዝ ይኖርበታል።

ማስታወሻዎች

1. በእኛ ሕግ ጥፋት "ሕሊናን ወይም የተለመደውን፣ መልካም አሠራር ተቃዋሚ በሆነ ዓይነት ድርጊት መፈፀም ወይም አለመፈፀም" ተብሎ የተተረጎመ ሲሆን ይኸውም አውቆ ወይም በቸልተኝነት ድርጊት መፈፀምን ወይም አለመፈፀምን ያጠቃልላል። ቁጥር 2030/1/ን ከቁጥር 2029 ጋራ በማጣመር ይመለከቷል። በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ጥፋት የሚመዘነው አጥፊ የተባለውን ሰው ዕድሜና የአእምሮ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ባለማስገባትና አንድ አስተዋይ ሰው ሊፈፅመው የሚገባውን መሠረት በማድረግ ነው። ቁጥር 2030 /2-3/ን ይመለከቷል። በመሆኑም ሕፃን ወይም ዕብድ የሆነ ሰው ጥፋተኛ ነው ተብሎ አላፊ ሊሆን ይችላል። በነገራችን ላይ ተለይቶ ካልተመለከተ በስተቀር ሁሉም ቁጥሮች የ1952ቱን የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ የሚመለከቱ ናቸው።

2. አንድን ሰው ያለጥፋቱ አላፊ የሚያደርጉት "ሥራዎች" /ሀ/ "አደገኛ" ናቸው የሚባሉት /ቁጥር 2069/፣ /ለ/ በእርግጥ ሊደርስ የሚችል አደጋን ለማስቀረት ሲባል ሆነ ብሎ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ /ቁጥር 2066/፣ እና በራስ ድርጊት በሌላ ሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ /ቁጥር 2067/ ናቸው።

   አንድ ሰው ጥፋተኛ ሳይሆን በሚፈፅመው ድርጊት በሌላ ሰው አካል ላይ እንዴት ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ለአንባቢ እንግዳ ነገር ሆኖ ይታይ ይሆናል። ለምሳሌ ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሕንፃ ግድ በሚገኘው ሜዳ አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች እግር ኳስ የሚጫወቱበትን ሁኔታ እንውሰድ፣ አንደኛው ተጫዋች አክርር የመታት ኳስ ከሜዳው ክልል ወጥታ እየፈጠነ ይሽከረከር የነበረን መኪና የፊት መስተዋት ስለሰበረች በመስተዋቱ ስብርባሪ ሾፌሩ የአካል ጉዳት ደረሰበት እንበል። በዚህ ጉዳይ ጉዳቱ የደረሰው ፍፁም በሆነ አጋጣሚ ነው። በሁለቱም ወገኖች ዘንድ ጥፋት ያልተፈፀመ ሲሆን ለጉዳቱ መድረስ ምክንያት የሆነው ኳሷን የመለጋቱ ድርጊት ነው። የሆነ ሆኖ፣ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ በመኪናው ላይ ለደረሰው ጉዳት አላፊነት የሌለበት መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

ሌላ ምሳሌ እንውሰድ፣ አንድ አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ ብስክሌት እየነዳ ሳለ የብስክሌቷ የፊት ጎማ በድንገት በመፈንዳቱ ሚዛኑን መጠበቅ ተስኖት በአንድ እግረኛ ላይ ወድቆ ጉዳት አደረሰ እንበል። እዚህም ቢሆን በሁለቱ ወገኖች የተፈፀመ ጥፋት የለም። ይሁንና በእግረኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት ምክንያት የሆነው አካለ መጠን ያላደረሰው ልጅ የፈፀመው የብስክሌት መንዳት ድርጊትና የብስክሌቱ ጎማ በድንገት መፈንዳት መሆኑ ግልፅ ነው። በነገራችን ላይ አንድ ተበዳይ በተከሳሹ ድርጊት ምክንያት የአካል ጉዳት ሲደርስበት ካሣ ለመጠየቅ ተከሳሹ ጥፋት የፈፀመ መሆኑን ማስረዳት እንደማያስፈልገው ልብ ማድረግ ይገባል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ጉዳት የደረሰበት ሰው ራሱ ጥፋተኛ ሆኖ ካልተገኘ በቀር ተከሳሹ ጥፋት ኖረበትም አልኖረበትም አላፊ ይሆናል።

3. ላደረሱት ጉዳት አንድ ሰው ያለጥፋቱ አላፊ እንዲሆን የሚያደርጉት ንብረቶች እንስሳት /ቁጥር 2071/፣ ሕንፃዎች /ቁጥር 2077/፣ መኪናዎችና ሞተር ተሽከርካሪዎች /ቁጥር 2081/፣ እና በሰው የተሠሩ ዕቃዎች /ቁጥር 2085/ ናቸው።

4. ኤም ፐላኒዮል፣ እነ ኤፍ ኤች ላውሰን በአሞፅና ዋልተን ኢንተርዳክሽን ቱ ፍሬንች ሎ ሁለተኛ እትም ውስጥ እንደጠቀሱት /አክስፎርድ፣ ክላሬንደን ፕሬስ፣ 1963/ ገጽ 203።

5. ለምሳሌ አር.ኤፍ.ቪ ሂውስተን ሳልመንድ.ኦን.ዘ.ሎ.ኦቭ ቶርትስ፣ 16ኛ እትም /ለንደን፣ ስዊት ኤንድ ማክስዌል፣ 1973/ ከገጽ 20-21 ይመለከቷል።

6. ለምሳሌ ጆርጅ ክሽቼኖቪች፣ ዘ.ኢትዮጵያን ሎ.ኦቭ.ኤክስትራ ኮንትራክቹዋል ሊያቢሊቲ /አዲስ አበባ፣ ሕግ ፋኩልቲ፣ 1970/ ገጽ 38 እና 61ን ይመለከቷል።

7. ብዙውን ጊዜ እነዚህ ሰዎች የቀለም ትምህርት መምህራን፣ የሙያ አስተማሪዎች፣ አስተዳዳሪዎችና፣ ልጁ ከቤተሰቡ ውጭ የሚኖር ከሆነ ልጁ በአደራ የተሰጠው ጠባቂ ናቸው።

8. አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ የሚባለው ዕድሜው 18 ዓመት ያልሞላው ሰው ነው። የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 198ን ይመለከቷል። ሆኖ ግን፣ ከሞግዚት አስተዳደር ሥልጣን ነፃ ለወጣ ልጅ ምንም እንኳን ዕድሜው አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላ ቢሆንም በሚፈፅመው ሥራ ለሚመጣበት ኃላፊነት ተጠያቂነት የሌለ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ይህ የሆነበት ምክንያትም ከሞግዚት አስተዳደር ሥልጣን ነፃ የወጣ ልጅ ሰውነቱንና የገንዘብ ጥቅሞቹን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ሁሉ ለማስተዳደር በሕግ አካለ መጠን እንዳደረሰ ሰው ሆኖ ስለሚቆጠር ነው። የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 329፣ 330፣ እና 333ን ይመለከቷል።

9. ከቁጥር 2126 እስከ 2127 እና 2129 እስከ 2131 ይመለከቷል። አንድ አሠሪ ጥፋት የሌለበት መሆኑን በማረጋገጥ ከኃላፊነት ነፃ ስለማይሆን በዚህ ረገድ ያለበት ኃላፊነት ፍፁም "ጥብቅ" ነው። አሠሪውን አጥፊ ሳይሆን ኃላፊ እንዲሆን ለማድረግ በቂ ምክንያቶች አሉ። አንደኛ፣ ጉዳት ያስከተለው የጥፋት ድርጊት የተፈፀመው ሠራተኛው ለአሠሪው ጥቅም ሥራ በማከናወን ላይ እያለ ነው። ሁለተኛ፣ የሠራው ሥራ ጉዳት ባያስከትል ኖሮ ብቸኛ ተጠቃሚ የሚሆነው አሠሪው ነበር። በመሆኑም ሠራተኛው የተመደበለትን ሥራ በማከናወን ላይ እያለ በተፈፀመ ጥፋት ለሚደርስ ጉዳት የሚከፈለውን ካሣ በአሠሪው ጫንቃ ላይ መጣሉ አግባብ ሊሆን ይችላል።

10. ቁጥር 2135ን ይመለከቷል። ደራሲ በፈፀመው የስም ማጥፋት ምክንያት በመጽሐፍ አውጭው ላይ ኃላፊነት የተጣለው መጽሐፍ አውጭው መጽሐፉን በማተምና ለሕዝብ በማሠራጨት በተዘዋዋሪ መንገድ በስም ማጥፋቱ ተግባር ተካፋይ ስለሆነ ይመስላል። ከዚህም በላይ ስም አጥፊ የሆኑ ዐረፍተነገሮች የያዘውን መጽሐፍ በማተም የገንዘብ ጥቅም አግኝቷል።

የጋዜጣ መሬን በሚመለከት የተጣለበት አላፊነት ከቸልተኝነት ተግባር አኳያ ሲታይ አግባብ ይሆናል። ምክንያቱም ቸልተኛ ባይሆን ኖሮ ስም አጥፊ የሆነው ጽሁፍ በጋዜጣው ላይ እንዲወጣ ባልፈቀደም ነበር። ከዚህም በላይ በሁለቱም ሁኔታዎች ደራሲው ማንነቱን የማይገልፅባቸው አጋጣሚዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ፣ የስም ማጥፋት በደል የተፈፀመበት ሰው እንደዚህ ካሉት ሰዎች ካሣ እንዲጠይቅ ይኸን ዓይነቱን እገዛ ማድረግ ያስፈልጋል።

11. ዣንፒየር ለጎል፣ "ሊያብሊቴ ፎር ፐርሰንስ አንደር ሱፐርቪዥን" ኢንተርናሽናል ኢንሳይክሎፒዲያ ኦቭ ኮምፓራቲቭ ሎ፣ ቮልዩም 11፣ እንድራቀንክ እንዳዘጋጀው/ ዘ. ሄግ፣ ቦስተን፣ ለንደን፣ ጂሲ ቢ ሞህር፣ እና ማርቲነስ ኒጆፍ፣ ቱቢንገን ፓቢሊሸርስ፣ 1973/ገጽ 7 ይመለከቷል።

12. ይህ ሁኔታ ከተወሰነ የዕድሜ ክልል በታች ያለ አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ከአላፊነት ነፃ የተደረገ መሆኑን ይጠቁማል። ለምሳሌ በፖላንድ ዕድሜው ከ13 ዓመት በታች የሆነ፣ በሶቪየት ኅብረት ደግሞ ከ15 ዓመት በታች የሆነ ዕድሜ ያለው ልጅ አላፊነት የለበትም። የፖላንድን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 426ን እና የሶቪየት ሕብረትን የፍትሐብሔር ሀግ ቁጥር 450ን ይመለከቷል።

13. ለጎል፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሰውን ገጽ 7 ላይ ይመለከቷል።

14. ይህንን መጽሐፍ ከገጽ 8-25 ይመለከቷል። ከዚህ የሚለዩት ሉዊዚያናና ማላጋሲ ብቻ ናቸው /የሉዊዝያና ሲቪል ኮድ አንቀጽ 2318ን እና የማላጋሲን ጀነራል ሩልስ ኦቭ ኦብሊጌሽን አንቀጽ 223ን ይመለከቷል።/ በዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ አስተሳሰብ ይኸ ልዩነት ኢትዮጵያንም ይጨምራል።/ ቁጥር 2124ን እና 2125ን ይመለከቷል/።

15. እላይ የተጠቀሰውን መጽሐፍ ገጽ 7 እና ከገጽ 25-29 ይመለከቷል።

16. ቁጥር 2124፥ የዚህ ቁጥር ሙሉ ድንጋጌ እንደሚከተለው ይነበባል፥ "አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ አላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሠራ እንደሆነ በፍትሐብሔር በኩል ለተሠራው ሥራ አላፊ የሚሆን አባት ነው።"

17. ቁጥር 2125፥ የዚህ ቁጥር ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ይነበባል፥
"የሚከተሉት ሰዎች በአባት አላፊነት ምትክ ተጠያቂ ይሆናል፥
/ሀ/ በልጅዋ ላይ በአባትነት ሥልጣን በምትሠራበት ጊዜ፥ እናት፥
/ለ/ ልጁ ከቤተሰቡ ቤት ውጭ የሚኖር ከሆነ ልጁ በአደራ የተሰጠው ጠባቂ፥
/ሐ/ ልጁ ት/ቤት ሳለ ወይምየሞያ ሥራ በሚማርበት ጊዜ የቀለም ወይም የሞያ ሥራ አስተማሪው።

18. አሠሪው መንግሥት ከሆነ አላፊነት የሚኖርበት ሠራተኛው በቁጥር 2126/2/ እና 2127 በተደነገገው መሠረት "የሥራ ጥፋት" የፈፀመ እንደሆነ ብቻ ነው። አሠሪው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ወይም ማሰሰብ ከሆነ አላፊ የሚሆነው ተቀጣሪው ሥራውን በማከናወን ላይ እያለ ለፈፀመው ጥፋት ነው። ቁጥር 2129 እና 2130ን ከቁጥር 2131 ጋራ አጣምሮ ይመለከቷል።

19. ቁጥር 2136ን እና ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 1 የተፃፈውን ይመለከቷል።

20. ቁጥር 2072 እና 2082ን ይመለከቷል።

21. በማስታወሻ 2 እና 3 የተፃፈውን ይመለከቷል።

22. ከኸቼኖቪቹ፥ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 6 የተጠቀሰውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

23. ቁጥር 2081ን ይመለከቷል።

24. ከዥቼኖዢች፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 6 የተጠቀሰውን መጽሐፍ ገጽ 51ን፣ የእርሳቸውን 145ኛ የግርጌ ማስታወሻና ገጽ 54ን ይመለከቷል።

25. የፈረንሳይኛው ቅጂ "ለሌሎች ሰዎች ተግባር ኃላፊ ስለመሆንና ስለብዙ ሰዎች ኃላፊነት "የሚል ይመስላል። እንደሚከተለውም ይነበባል፣ "De la responsiabilité du fait d'autrui et de la pluralité de responsables." የአማርኛው ቅጅ "ለሌላ ሰው <u>ተግባር</u> ኃላፊ ስለመሆን" ይላል /ሥርዝ የተጨመረ/። ስህተቱ መስሎ የሚታየው የፕሮፌሰር ከዢቼኖዢች የተሻሻለው ትርጉም ግን ዝምብሎ "ለሌሎች ሰዎች ኃላፊ ስለመሆን" ይላል።

26. ቁጥር 2136 እንደሚከተለው ይነበባል።
"/1/ አንድ ሰው ለአንድ ጉዳት በፍትሐብሄር በኩል ኃላፊ ነው ተብሎ በሕግ የተረጋገጠ መሆኑ ጉዳት አድራጊው ላደረሰው ጉዳት ካሣ መክፈልን አያስቀርለትም።

/2/ ጉዳት ያደረሰውና በፍትሐብሄር በኩል ኃላፊ የሆነው ለካሣው አከፋፈል የአንድነት ግዴታ አለባቸው።

/3/ በሕጉ አስተያየት ረገድ በፍትሐብሄር በኩል ኃላፊ ነው የተባለው በበኩሉ ጉዳት ያደረሰውን ዋንኛውን ኃላፊ በቀረበበት ክስ ውስጥ እንዲገባ ለማስገደድ ይችላል።"

27. ለጎል፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሰውን መጽሐፍ ገጽ 5 ላይ ይመለከቷል።

28. ሌላው ዓላማ ብዙውን ጊዜ ካሣ የመክፈል አቅም የሌላቸው አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች በሚፈፅሟቸው የጥፋት ተግባሮች ጉዳት ለሚደርስባቸው ሰዎች

የኪሣ ዋስትና ማስገኘት ነው። ፕሮፌሰር ክሽቼናዚች እላይ በማስታወሻ ቁጥር 6 በተጠቀሰው መጽሐፋቸው በገጽ 54 ላይ ያሉትም ይህንኑ ነው። ሲናገሩም እነዚህ ሰዎች በሕግ መሠረት ዋሶች ሲሆኑ፣ ዋስትናቸውም ልጁ ተፋት እንዳይፈፅም ነው ብለዋል።

29. ለጎል፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሰውን መጽሐፍ፣ ገጽ 5 ይመለከቷል።

30. ይህ መከላከያ ከእቅም በላይ ለሆኑ ምክንያቶች ብቻ እንዲያገለግል ተደርጎ አልተገደበም። የመቆጣጠር ተግባሩን በመፈፀም ረገድ ስሕተት ያልፈፀመ መሆኑን ለማሳየትም ማረጋገጫ ሊያቀርብ ይችላል። ላውሰን እላይ በማስታወሻ ቁጥር 4 የተጠቀሰውን መጽሐፍ ከገጽ 227-228 ድረስ ይመለከቷል።

31. ቁጥር 635/1/።

32. ቁጥር 644/2/ በተጣጣሪነት ከቁጥር 635/2/ ጋራ ሲነበብ።

33. የእናትዮዋ አላፊነት በአባትዮው አላፊነት ምትክ ከሆነ ደግሞ አባትዮው አላፊ በሆነበት ሁኔታ ልጁ በፈፀመው የጥፋት ተግባር ሳቢያ የመጣው ዕዳ የሚከፈለው ከአባትዮው የግል ሀብትና ይህ ካልበቃ ከጋራ ሀብታቸው ላይ ብቻ ይሆናል ማለት ነው። በሌላ አነጋገር፣ ዕዳውን ለመክፈል የአባትዮው የግል ሀብትና የጋራ ሀብታቸው በቂ ሆኖ ካልተገኘ ዕዳው ከእናትዮዋ የግል ሀብት ላይ ሊከፈል አይችልም። አላፊነቱ የሚመለከተው እናትዮዋን በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ሁኔታው የዚሁ ተገላቢጦሽ ይሆናል። ቁጥር 659ን በተጣጣሪነት ከቁጥር 660 ጋራ ይመለከቷል።

34. ቁጥር 638

35. ቁጥር 681 በተጣማሪነት ከቁጥር 682 ጋራ ሲነበብ

36. ቁጥር 639

37. ቁጥር 2125 /ለ/።

38. ቁጥር 2125 /ሐ/።

39. ሰንአ፥ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 23።

40. እዚያው ቦታ ይመለከቷል።

41. የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 64/68 አንቀጽ 27ን ይመለከቷል።

42. ያለጥፋት አላፊ በሚኮንበት ሁኔታ እንደተደረገው ሳይሆን በዚህ ጉዳይ ይህ መከላከያ እንዳያገለግል በግልፅ አልተከለከለም።

43. አንዳንድ አንባብያን አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ እንዴት በህጋዊ መንገድ የንብረት ባለሀብት ሊሆን ይችላል? በተለይም ደግሞ ጉዳት ሊያደርሱ አንድን ሰው ያለጥፋቱ አላፊ የሚያደርጉትን ንብረቶች እንዴት የግል ሀብቱ ሊያደርጋቸው ይችላል? ብለው ይጠይቁ ይሆናል። በእኛ ሕግ መሠረት አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ በባለሀብትነት ሊይዘው የሚችለውን የንብረት ዓይነት በሚመለከት ገደብ አልተደረገም። በመሆኑም አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ለንግድ፥ ለኢንዱስትሪ፥ ወይንም ለሌሎች ሥራዎች አገልግሎት የተመደቡ የማናቸውም የንብረት ዓይነቶች ባለሀብት ሊሆን ይችላል። ቁጥር 288ን ይመለከቷል። አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ እነዚህን ንብረቶች በስጦታ፥ በኑዛዜ፥ ወይም በውርስ ሊያገኝ ይችላል። ቁጥር 287 እና 299 /1/ን ይመለከቷል። በነገራችን ላይ አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ሀብቶች ሁሉ በሞግዚት

እንደሚጠበቁና እንደሚተዳደሩ፣ እንዲሁም ሞግዚቱ የልጁ ንብረቶች ከራሱ የግል ንብረቶች ጋራ እንዳይደባለቁ ተገቢውን ማድረግ እንዳለበት መገንዘብ ያሻል። ቁጥር 280/2/ እና 283ን ይመለከቷል። ብዙውን ጊዜ አባትና እናት ጋብቻቸው ፀንቶ እስካለ ድረስ አካለመጠን ላላደረሱት ልጆቻቸው በአንድነት ሞግዚቶች ናቸው። ቁጥር 204ን ይመለከቷል።

44. እላይ በማስታወሻ ቁጥር 24 የተጠቀሰውን ይመለከቷል።

45. ክሽሞናዚች፣ በማስታወሻ ቁጥር 6 የተጠቀሰውን መጽሐፍ ገጽ 38 ይመለከቷል።

46. ሰጎል፣ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሰውን መጽሐፍ ገጽ 6 ይመለከቷል።

ተጠየቅ ሙግት
ልማዳዊው የኢትዮጵያ የክርክር ሥልት

አበራ ጀምበሬ*

የተጠየቅ ሙግት ባለፈውና በያዝነው ክፍለ ዘመን በመጀመሪያዎቹ ሦስት አሠርተ ዓመታት ውስጥ ከፍ ካለ ደረጃ የደረሰ፥ ፍጹም ኢትዮጵያዊ የሆነ ልማዳዊ የፍርድ ቤት የክርክር ሥልት ሲሆን፥ ይኸውም የሕግ ዓይነት በዘመናዊ የሕግ ሳይንስ የፍትሐ ብሔርና የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ በመባል ይታወቃል። ይህም ሥርዓት በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወራረስ የመጣ ነው።

ይህ የሥነ ሥርዓት ሕግ በተራቀቀ የጥያቄና መልስ /በክሮስ ኤግዛሚኔሽን/ ሥልት የነገርን ጭብጥ አፍረጥርጦ ለማውጣት የሚደረግ ሙግትንና የማስረጃ አቀራረብን /ሩል ኦፍ ኤቪደንስ/ ያጠቃልላል። "ተጠየቅ" የሚለው ቃል በቀጥታ ትርጉሙ "ልጠይቅህ" ማለት ሲሆን፤ በቴክኒካል /በሕጋዊ/ ትርጉሙ ግን ልማዳዊ የኢትዮጵያ የክርክር ሥልት ማለት ነው። "እሰጥ አገባ"[1] የሚለው ቃል በዚህ ዓይነቱ የሙግት ሥልት፥ በፍርድ ቤት የሚደረግ ክርክር ሂደትን የሚያመለክት በመሆኑ ለተጠየቅ ሙግት በተለዋጭ ቃልነት ያገለግል ነበር። ሙግት ማለት በፍትሕ አስተዳደር ክርክር ማለት ሲሆን፤ ሥነ ሥርዓት ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ሁሉ ያጠቃልላል።

ጀኔራል ዠርጀን በዚህ ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነው የሙግት ሥልት መሠረት ሲካሄድ ስለተመለከቱት የፍርድ ቤት ክርክር የሰጡትን ሐተታ ሲያጠቃልሉ፤ የዓይን ምስክርነታቸውን በሚከተለው አኳኋን ገልጸውታል።

---

* በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ፋኩልቲ የትርፍ ጊዜ ረዳት ፕሮፌሰር

ኢትዮጵያዊ ጥሩ ተናጋሪ ስለሆነ፣ ተሰጥኦውን ለመግለጽ የሚችልበትን ማንኛውንም ዕድል ሳይጠቀምበት አያልፍም። ሙግት ብዙውን ጊዜ ብዛት ያለውና አድናቂ አዳማጭ የሚሰበሰብበት ጥሩ አጋጣሚ ነው። አንዳንድ ጊዜ ትከሻውን እያሳየ፣ አንዳንዴም ጣቱን ወደ ተከሳሹ እየቀሰረ በሚያስፈራራ አኳኋን ሲቃ እየተናነቀው የነገር ፍላጻውን ያንበለብለዋል።

ዳኛውም ዙሪያውን በከበቡት አድማጮች መካከል ተቀምጦ እንደበተ ርቱውን ተከራካሪ በጥሞናና በተመስጦ ከአዳመጠ በኋላ ተከሳሹን መልስ እንዲሰጥ ይጠይቀዋል። እርሱም ከምንጭ ገንፍሎ እንደወጣ ፈሳሽ ተፍ ብሎ ይነሳና ንጹህነቱን እንዲመሰክርለት እጆቹን ወደ ሰማይ እንደዘረጋ በርከክ ይላል። በተከራካሪውም አፍንጫ ሥር ቡጢውን ያወዛውዛል። ከመሳሉ የቃላት ውርወራውን ሳያቋርጥ፣ እጆቹን አጣጥፎ ወደዳኛው ይቀርባል።[2]

ይህ የፍርድ ቤት ቲያትራዊ ገለጻ የአማራ ባሕላዊ ቅርስ /ውርስ/ አካል የሆነው የተጠየቅ ሙግት እንዴት ይካሄድ እንደነበር ያሳያል። ከ1928 ዓ.ም. በፊት የአማራ ልማዳዊ ሕግ፣ ከተጠየቅ የሙግት ሥርዓት ጋር በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ጎልቶ ይታይ ነበር።

እዚህ ላይ መነሳት የሚገባቸው ጥያቄዎች፣ በተጠየቅ ሙግት አፈጻጸም አግባብነት የነበራቸው ዋና ዋና ሁኔታዎች ምን ነበሩ? እንዴትስ ይሠሩ ነበር? የሚሉት ናቸው።

1. በፍርድ ቤት የሚካሄዱ ሁኔታዎች

ሙግት ሲጀመር አብዛኛውን ጊዜ በበጎ ፈቃድና ከመቅጽበት የሚፈጸም የግልግል ሂደት ሁኖ ነበር። አንደኛው ወገን ተከራካሪ ባላጋራውን መንገድ ላይ ሲያገኘው ማንኛውም ተላላፊ መንገደኛ ጉዳዩን በዳኝነት እንዲያይለት /እንዲዳኘው/ የመጠየቅ መብት በሕግ ተሰጥቶታል።[3] ከርከሩ የሚያገባው ወገን የተላላፊ መንገደኛው

/የመንገድ ዳኙ ፍርድ ቤት/[4] ውሳኔ ቢያረካው ጉዳዩ በዚሁ እንዳለቀ ይቆጠራል። ለሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወይም ለአንደኛው አርኪ የሆነ ውሳኔ ያልተገኘ እንደሆነ ግን ወደ ፍርድ ቤት ተያይዘው ይሄዳሉ፤ ወይም አንዳንድ ጊዜ የመንገድ ዳር ዳኛ ሁኖ የዳኛቸው ሰው በአቅራቢያ ከሚገኘው ዝቅተኛው የመደበኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ዘንድ ያደርሳቸዋል።

ዝቅተኛው የመደበኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ጭቃሹም[5] ወይም መልከኛ[6] ሊሆን ይችላል። ጭቃሹምና መልከኛ በመሠረቱ የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው የአስተዳደር ሹማምንት ነበሩ። በዚያ ጊዜ ለነበረው ሕብረተሰብ የመንግሥታዊ ሥልጣን መከፋፈል መሠረተ ሃሳብ እንግዳ ነበር። ስለዚህ የመንግሥት ባለሥልጣን ሁሉ ዳኛ ይባል ነበር።

በዳኝነት ሥራ አግባብ ካላቸው ከዳኞች ቀጥሎ ከፍተኛ ሥፍራ የነበራቸው ተቺዎች /አማኞች/[7] ነበሩ። ከአማኞቹ ከፊሎቹ በተከራካሪ ወገኖች ከፊሎቹ ደግሞ በፍርድ ቤቱ ከተገኙ ሰዎች መካከል በመደበኛው ፍርድ ላይ የሚመረጡ ነበሩ።

በፍትሕ ሥራ ዓይነተኛ ሂደት ውስጥ ሦስተኛ ደረጃ የሚሰጠው ደግሞ ዋስ ነበር። ብዙውን ጊዜ የሚዘወተሩት የዋስ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. <u>የቅብቃብ ወይም የመጋኘ ዋስ</u>:- አንድ ወንድ ለአካለ መጠን ደርሶ የራሱ መኖሪያ ቤት ሠርቶ ጎጆ ሲወጣ፥ የኅብረተሰቡ ሥርዓት ጥሩ አክባሪ እንደሚሆን ለማረጋገጥ የሚጠራው ዋስ፤

2. <u>የሥነ ሥርዓት ዋስ</u>:- ክስ ሲጀመር በሙግት ወቅት የሥነ ሥርዓት ሕግ የሚጠይቀውን ሁሉ ለማክበርና ለማሟላት፤ እንዲሁም ነገሩ በሚሰማበት ቀን ቀጠሮ እንዲሚቀርቡ ለማረጋገጥ ሁለቱም ወገኖች /ከሳሽና ተከሳሽ/ የሚጠሩት ዋስ፤

3. <u>የገሬ ዋስ</u>:- ከተከራካሪ ወገኖች አንደኛው በሌላው ላይ ወንጀል አውርቶ ወይም ተሳድቦ እንዳይቀር፣ በተናገረው ካልገፋበት ስለሚቀጣ፤ ለካሣው ክፍያ የሚጠራው ዋስ፤

4. <u>የዳኝነት ዋስ</u>:- በሙግት የተረታው ወገን ለመንግሥት ዳኝነት መክፈል ስለሚኖርበት፤ የዳኝነቱን ለመክፈል በሁለቱም ወገን የሚጠራ ዋስ፤

5. <u>የውርርድ ዋስ</u>:- በክርክሩ ወቅት ይህን እሰጥ ብሎ የሚተክለውን ውርርድ ተረቸው መክፈል ስለአለበት፣ አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ጉዳይ ብይን ሊሰጥበት፣ የውርርዱን ለመክፈል የሚጠራ ዋስ፣

6. <u>የበሰላ ዋስ</u>:- በፍትሐ ብሄር ጉዳይ ክስ የቀረበበትን ዕዳ ለመክፈል ፍርድ በሚሰጥበት ወቅት የሚጠራ ዋስ፤

7. <u>የጠለፋ ዋስ</u>:- አንድን ሰው እጁን ለማቅረብ ወይም ዕዳውን ለመክፈል ዋስ የሆነው ሰው በፋንታው ተጠያቂ የሚሆንለት ሰው እንዲሰጠው ጠይቆ የሚያስጠራው ዋስ፤

8. <u>የእጅ ጠብቅ ዋስ</u>:- በወንጀል ክርክር በማንኛውም ደረጃ ለሕይወቱ ያሰጋኛል ብሎ አንደኛው ወገን ሲያመለክት የእጅ እላፊ እንዳይፈጽም ሌላው ወገን የሚጠራው ዋስ።[8]

በዚህ የሙግት ሥርዓት በፍትሕ ሂደት አራተኛውና የመጨረሻው ነገረ ፈጅ የሚባለው ተቋም ነው። ነገረ ፈጅ የሚሆን ሰው በአብዛኛው በቂ የሕግ እውቀት ያለው ሁኖ፣ አንድን ሰው በመወከል በፍርድ ቤት ለመቆም የተስማማ ሰው ነው።

በፍትሕ ሂደት አግባብ ያላቸውን ተቅዋማት ከገለጽን ዘንድ፥ የተጠየቀ ሙግት እንዴት እንደሚካሄድ፤ ማለትም በማንኛውም ደረጃ በሚገኝ መደበኛ ፍርድ ቤት የሙግቱ ሂደት እንዴት እንደሆነ ወደ መግለጹ እናመራለን።

2. የፍርድ ሂደት

ሀ/ ክርክር መጀመር

በከሳሹና በተከሳሹ በሁለቱም የሥርዓት ዋስ በመጥራት በፍርድ ቤት ሙግት ይጀመራል። ሁለቱም ወገኖች ዋስ ከጠሩ በኋላ ዳኛው ተከሳሹ ክሱን እንዲያቀርብ ይጠይቀዋል። ተከሳሹ ይገባኛል የሚለውን ሁሉ ጠይቆ እንደጨረሰ፥ ተከሳሹ የእምነት ወይም የክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ይጠየቃል።

ክሱን የካደ እንደሆነ የከሳሹ ጠበቃ ዘንጉን እየተመረኮዘ በችሎቱ ከዳኛ ፊት ወደፊት ወደኋላ እየተንጎራደደና እየተንደረደረ በአከራካሪው ጉዳይ ያለውን የፍሬ ነገርና የተፍጫሬ ክርክሩን ያቀርባል።

ተከሳሹ ደግሞ በፋንታው ፍጆታ ጠይቆ፥ በዚሁ አኳኋን መከራከሪያውን /ተቃውሞውን/ ያቀርባል።

ለ/ ውርርድ መትከል

በዚህ ደረጃ ከሳሽ ቃብጡን ለማሳመን ውርርድ ይተክላል። ተከሳሹ ሲፈልግ፤ ለምሳሌ ከሳሽ በቅሎ እሰጥ ብሎ ውርርድ ተክሎ እንደሆነ፥ ውርርድህን አሰልስል /ዝቅ አድርግ/ ብሎ ይጠይቃል። ከሳሽ ፈረስ እሰጥ በማለት ውርርዱን ዝቅ ካደረገለትም በኋላ እንደገና ዝቅ እንዲያደርግለት ከፈለገ እንደገና አሰልስል ብሎ ሊጠይቅ ወደ ማር[9] ያወርድለታል። ተከሳሹ ከዚህ በኋላ ለከሳሹ የተከለውን ማር የሚሰጥ ለመሆኑ "እነና" ብሎ ይከራከራል። አለበለዚያም "እምና ይሟገታል፥

ከረከሰበት ይሸምቷል" እንደሚባል፣ ጉዳዩን እምና ተፋተኛ የማይሆንበትን ምክንያት ውርርድ ተከሉ ያስረዳል። ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ እርግጠኛነት ያመነ እንደሆነ ግን ለተተከለበት ውርርድ "አትራሁ ጠናኝ" ይላል።

እንደዚህ ያለው የእምነት ቃል ሲሰጥ ከሳሹ "በአትራሁ ጠናኝ የተረታ፣ መሐል አገዳውን የተመታ" ብሎ ቀኙ የእርሱ መሆኑን በቃለ እጋና በመግለጽ፣ በተከሳሹ ላይ እንዲፈረድበት ይጠይቃል። አትራሁ ጠናኝ ያለው ወገን አንድ ብር የዳኝነት እንዲከፍል ይጠየቃል።

በአትራሁ ጠናኝ የተፈጸመ ክርክር ይግባኝ የሌለው፣ የነገር መደምደሚያ ነበር።

ሐ/ የምስክሮች አመሰካከርና የጽሁፍ ማስረጃ አቀራረብ

ተከሳሹ ከቀረበበት ክስ እንዳንዱን ሁኔታ የሚክድ የሆነ እንደሆነ፣ የተካደው ጉዳይ በአስረጂ መረጋገጥ አለበት፣ ስለዚህ ከሳሹ ክሱን ለማስረገጥ በቃል ወይም በጽሁፍ ወይም በሁለቱም አስረጂውን ያቀርባል።

ሁለቱም ወገኖች ውርርድ ከተከሉና በመካከላቸው አከራካሪው ጭብጥ ተለይቶ ከታወቀ በኋላ በያንዳንዱ ወገን የሚቀርቡ፣ ቢያንስ ሦስት ሦስት ምስክሮች ይሰማሉ። ምስክሮቹም ከፍርድ ቤት ቀርበው ሁለቱም ወገኖች ወይም ነገረ ፈጆቻቸው በአሉበት በግልጽ ይመሰክራሉ። የጽሁፍ ማስረጃ ካለም ለፍርድ ቤቱ ይቀርባል። እዚህ ላይ በጭብጥ ዳኛ[10] አማካይነት የተገኘ መረጃ ተቀባይነት ያለው መሆኑንና የበቂነት ዋጋውን መረዳት ተገቢ ይሆናል።

በእርጅና ወይም በብርቱ ሕመም ምክንያት አንድ ምስክር ከፍርድ ቤት ቀርቦ ለመመስከር ያልቻለ እንደሆነ፣ ለማመሳከር በተሰየመ የጭብጥ ዳኛ አማካይነት የተባለው ምስክር ቃል ተሰምቶ ለፍርድ ቤቱ እንዲፈስ ይደረጋል። የጭብጥ ዳኛው በክርክሩ ጊዜ የተነሳው ጭብጥ ይገለጽለትና ምስክሩን አስመስክር ለፍርድ ቤቱ

እንዲያፈስ ይጠየቃል። እስመስካሪው ከተከራካሪዎቹ ጋር ምስክሩ ወደ ሚገኝበት ሥፍራ ይሄዳል። ተከራካሪዎቹ ወገኖችና የአካባቢው ጭቃ ሹም የመረጡአቸው አራት እማኞች በተገኙበት ምስክሩ የሚሰጠውን አድምጦ ሲመለስም፣ ተከራካሪዎቹ በተገኙበት ለላከው ዳኛ ምስክሩ የመሰከረውን በቃል ያፈሳል /ይገልጻል/።[11]

የጭብጥ ዳኛው የምስክሩን ቃል ሲያፈስ ያዳነ /ያሳሳተ/ እንደሆነ የሚቃረምበት ሁኔታ እንደሚከተለው ነበር።

> ምስክሩ ከተናገረው ቃል ውስጥ ያስቀረ ወይም የጨመረ እንደሆነ ቅር የተሰኘው ወገን "ተዘከረኝ ዳኛ ማርያም፣ እግዚአብሄር መዝከሪያ ልቡና መተላለፊያ ጎዳና ይስጥህ፣ አቶ እገሌ እንዲህ የመሰከረ መሆኑን አስታውስ ይለኛል።"[12] የተዘነጋው ነገር ቢኖር ያቃናል። በቃሉ የፀና እንደሆነ ግን፣ ተቃዋሚው "የምስክሩን ቃል በማጣረሱ ሰድቤዋለሁና ምስክሩን የሰሙት እማኞች ይንቀሉልኝ" ይላል። በዚህ ጊዜ እማኞቹ እንዴት እንደተመሰከረ ይጠየቃሉ። እንደርሱ ነው ብለው የመሰከሩ እንደሆነ ነቃፊው አመስካሪውን ዳኛ ይከሳል። አንድሎ የተገኘ እንደሆነ ግን የምስክሩ ድምፅ እማኞቹ እንደተናገሩት ሁና ይፀናል። ዳኛውም ይወቀሳል።

በመሠረቱ በተንቱ ልማድ ምስክር የምስክርነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ቃለ መሐላ እንዲሰጥ አይጠየቅም። ሆኖም "አምልሃለሁና የምታውቀውን እስተካክለህ መስክር" ብሎ ማስጠንቀቅ ይቻላል። የማስጠንቀቂያቸውም ቃል "ስማ ምስክር እንዳትል" የሚል ነበር።

ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ምስክሩ የሚያውቀውን በትክክል አለመመስከሩን ወይም መሸፈጡን ሲረዳ ለማስማል እንዲፈቀድለት ዳኛውን ጠይቆ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን

ጀደው በቅዳሴ ጊዜ ዕርገት ሲወርዱ የቤተ ክርስቲያኑን በር ይዘጋል[13] ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ እውነቱን ባልመሰከር

እንደ መስቀሉ ይበሳሳኝ
እንደ ሥዕሉ ይደምስሰኝ
እንደ ሥጋው ይቆራርሰኝ
እንደ ደሙ ያፍሰኝ
እንደ መቅደሱ በር ልሳኔን ይዝጋው

እያለ ይምላል።

አንድ ምስክር ከፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ሲመሰክር /የምስክርነት ቃሉን ሲሰጥ/ የተገኘ እንደሆነ፣ ሌላው ወገን አስቀድሞ የመሰከረ ስለሆነ አይነግርብኝም ወይም ለምስክርነት አይበቃም ብሎ የመቃወም መብት አለው።

አንድ ምስክር ሲቆጠር፣ ሌላው ወገን "እገሌ ለባላጋራዬ የሥራ ወይም የጋብቻ ዝምድና አለው፣ ወይም አበልጅ ወይም የጉድፈቻ ልጅ ነው" በማለት ወይም ነውር በመጥቀስ እንዳይመሰክር ብይ /እክይ/ ሊያወጣበት ይቻላል።[14] ምስክሩም የምስክርነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት የቆጠረው ወገን፣[15]

ሞቶ መክነን
ታሞ መመንመን
የአልጋ ቁራኛ መሆን

ያለ መሆኑን ተገንዝበሀ፥ እውነቱ እንዲህ መሆኑን ብታውቅልኝ ይለዋል።

ሌላውም ወገን በዚሁ አኳኋን ካዘከረ በኋላ፣ "እንደተባለው ለመሆኑ ባታውቅብኝ" ብሎ ይናገራል።

የምስክሮች ሁሉ ቃል ከተሰማ በኋላ አብዛኛዎቹ ምስክሮች የመሰከሩለት ወገን "ምስክር ለበለጠ፥ ውድማ ለመለጠ" በማለት፤ መብቱ ስለተረጋገጠለት ፍርድ እንዲሰጠው ይጠይቃል።

ምስክር ሲመሰክር ለኔ ነገረ፥ ለኔ ነገረ በማለት ሁለቱ ወገኖች የሚሻሙበት ሁኔታ ያጋጥማል። እንደዚህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥም፤ አርቀብ እማኞች[16] ተመርጠው "ምስክሮቹ የነገሩት ለተከሳሹ ወይም ለከሳሹ ነው" ብለው በመሰላቸው ያደሉ ነበር። በኋላ ግን ምስክሩ ራሱ ለማን እንደመሰከረ እንዲያረጋግጥ እንደገና እንዲጠራ ይደረግና በሚሰጠው ቃል [17] በዚህ ረገድ የተነሳው ክርክር ፍጻሜ እንዲያገኝ ይደረግ ነበር።

መ/ <u>ተጠየቅ</u>

በቀድሞ ጊዜ በፍትሐብሄር ክርክር የመከላከያ ምስክር በማቅረብ የመከላከል መብት አልነበረም። ተከሳሽ ክስ ለቀረበበት ነገር "ማስረዳት የሚገባኝ እኔ ነኝ እንጂ ከሳሽ አይደለም" ብሎ በይግባኝ ይከራከር ነበር።[18]

ሬቨረንድ ራሴል ስለዚህ ዓይነቱ የክርክር ዘዴ ሲያትቱ፤ ከአንድ ተኩል ምዕተ ዓመታት በፊት እንደሚከተለው ጽፈዋል።

> ጠበቆቹ እንደነገሩ ሁኔታ ከከሳሹ ወይም ከተከሳሹ ጎን ይቆሙና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ልዩ ልዩ ክርክሮቻቸውን ያቀርባሉ። በዚሁም ሂደት በክሱ ውስጥ የተመለከተውን እንደዚሁ እንደዚሁ ያሉትን ክርክሮች ለማስረገጥ በቅሎ፥ ላም፥ በግና ወርቅ እሰጥ በማለት ተናጋሪዎቹ እያደራረሱ ውርርድ ይተከላሉ።[19]

እንደዚህ ያለው በሥነ ሥርዓት የመጠቀም መብት በተከራካሪዎቹ ወይም በነገረ ፈጆቻቸው ይነሳ ነበር። እንደዚህ ያለው ክርክር ሲነሳበት ሌላው ወገን ካፌ[20] ወይም ከጠበቃዩ[21] ይላል።

በተወሰነው ቀን ቀጠሮ በተጠየቅ የሙግት ሥርዓት መሠረት በተያቁና መልስ ክርክሩን ለመፍታት ክርክሩን ከመጀመሩ በፊት ከሳሽ ራሱ ወይም በነገረ ፈጅ አማካይነት "ሥርዓት ልክ ነው?" ብሎ ይጠይቀዋል። ተከሳሹ አወንታዊ መልስ ስለሚሰጥ፤ ክሱ የሚያስከትለውን ሁኔታ ለማስገንዘብ፥ ከሳሹ ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ያቀርባል።

ጠያቂው በአንድ ጊዜ እንዲያቀርብ የሚፈቀድለት አንድ ጥያቄ ሲሆን፥ ተከራካሪውም ወገን ለያንዳንዱ ጥያቄ አንድና ቀጥተኛ የሆነ መልስ መስጠት አለበት። በዚህ አኳኋን በተከራካሪዎች ወገኖች መካከል የጥያቄና መልስ ልውውጥ ይደረጋል። ለዚህም ሥርዓት መከበር ውርርድ ይተከላል። ከተጠየቀው ውጭ ወይም ተረፍረፍ አድርጎ የመለሰ እንደሆነ ሥነ ሥርዓቱን እንደማጣረስ ይቆጠራል።[22]

ከተከራካሪዎቹ ወገኖች አንደኛው ይህን ሥነ ሥርዓት ያጣረሰ እንደሆነ አስቀድሞ የተሰነዘረውን ውርርድ ለመክፈል ዋስ እንዲጠራ ይጠየቃል። ለቀረበው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ሥነ ሥርዓት መጣረስ ወይም አለመጣረሱ በተቾዎች ይረጋገጣል። እንደዚህ ያለ ስህተት ማድረጉን ተጠያቂው ቢያምንም እንኳ ውርርዱን መክፈል አለበት። ከሣሽ ጥያቄዎቹን ሲጨርስ፥ ተከሳሹ በፋንታው ጥያቄዎች ማቅረብ ይቀጥላል።

ሠ/ <u>ውርድ መንዛት ወይም በላ ልበልሃ</u>

በክሱ ላይ ዋና ጥያቄና መሰቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ ጉዳይ እንዳበቃ፥ ዳኛው ውሳኔውን ከመስጠቱ በፊት ተከራካሪዎቹ ውርድ ወደ መንዛት ያመራሉ። ማለትም በግጥምና በርቱዕ አነጋገር ዳኛውንና በፍርድ ቤቱ የተገኙትን ሰዎች ለማሳመን የበላ ልበልሃ ሙግቱን ያኸጎደጉዱታል።

በዚሁም ጊዜ እያንዳንዱ ወገን የበላጋራውን ነውሩን፣ በዘሩ ጭምር ያለበትን መዘርዘር፣ በሾርኔ እያሰደበ የተቀማውን ሐሳብ ወደርሱ ለመሳብ፣ ነገሩን በሚመስል ሁኔታ እያብራራ በግጥም እያደረገ፣ ምሳሌ እየሰጠ ውርድ ይነዛል ወይም የመፋረጃ ቃሉን ይሰማል።

የሚከተለው የውርድ አነዛዙን በመጠኑ ያመለክታል:-
በላ ልበልሃ፣
የአጤ ሥርዓቱን[23] የአብርሃም አረቱን፣ የመሠረቱን
አልናገር ሐሰቱን፣ ሁልጊዜ እውነት፣ እውነቱን፤
ከ ... ወዲያ ላኛ
ከ ... ወዲያ ዝንገኛ
አልተፈጠረም ላገመኛ
... የፈረደው
የአዳል ዱቤት ያረደው፣
የፈረደው አይገለበጥ
ያረደው አይንፈራገጥ።
እስጥ ብየ ማር ጥየ
ከእግር ዘንጥየ
ባለማ ፍረዱልኝ፣
ባጠፋ ስደዱኝ፤
ሲል ይሟገታል፤ እሬ ማሩ ነገረ ደግሙ።[24]

ሌላውም ወገን በተራው በዚሁ ዓይነት ላኛውን ለመሳብና ተከራካሪውን ለማዋረድ ይጥራል።

የሚለዋወጡዋቸው በስሜት የተሞሉ ቃላት ቢሆኑም፤ በተያቄው ጊዜ ያስተማመነውንና ከቃሉ ያገኘውን መልስ ለከርከሩ እንዲደግፈው ባላጋራው

የሚያብራራበትና የራሱን ተፃተኛነትና እውነተኛነት የሚገልፃባቸው ሲሆኑ፤ በዘመናዊ ሙግት ለውሳኔ በደረሰ ነገር ዳኛው ከመፍረዱ በፊት እንደሚተርበው የመፋረጃ ቃል ያለ ነገር ነው።

የውርድ መንዛት ሌላው ዓላማ የዳኛውን ልቦና ማሞካሸት ነው። በዚህ ረገድ ባሻ ሙላት ወልደ ዮሐንስ የተባሉት ነገር አዋቂ፥ በአፈንጉሥ ነሲቡ ችሎት ላይ የተናገሩት የሚከተለው ግጥም የአፈ ንጉሥ ነሲቡን ልቦና ሰቅሎት እንደነበረ ይነገራል። ግጥሙም:-

እሳት ላይ የጣሉት ነት
አልጋ ላይ ያነጠፉት ቁርበት
ለእበተኛው እንደነቱ
ለእውነተኛው እንደቁርበቱ
ነው ነሲቡ ዳኝነቱ።
ፈረሱ ዳማ፥ ሚስቱ ደስታ
ጎራዴው ወንበዴ ዞር የሚመታ
ጌታየ አንተ ፊት አስተ ይገዞ አልመጣ
ቀጣፊ ወንበዴ ለይተህ በጅራፍ እምትቀጣ።[25]
የሚል ነበር።

ክርክሩ የውርድ መንዛቱን ደረጃ ሲያልፍ፥ ተቾዎች /አማኞች/ ከታች በመጀመር ወደ ላይ በየተራ እየተነሱ የመሰላቸውን እየተቹ እንዲፈርዱ ይጠየቃሉ።

ረ/ መተቸትና ፍርድ መስጠት

በፍርድ ጊዜ አማኞችም ሆኑ ወይም ዳኛው ለመፍረድ ሲነሱ የሚከተለውን ቃለ መሐላ ያደርጉ ነበር።

ይፍረድብኝ፥ ይፈረድብኝ
ባደላም ያድላብኝ
በጌታየ ጠላት ሠይፍ፥ ሞት ይፈረድበት፤
የራቀን በመድፍ የቀረበውን በሰይፍ
እርዶ፥ ፈርዶ ይጣለው።[26]

ተችዎቹ /እማኞች/ ፍሬ ነገሩን ካብራሩ በኋላ "እነሌ ሲረታ ይታየናል" በማለት አስተያየታቸውን ይገልጻሉ።

በመጨረሻም ዳኛው /ወንበሩ/ በትድሚያ ምክንያቱን ከተነተነ በኋላ "እገሌ ፈርጀብሃለሁና ውርርድህን አንሣ"[27] በማለት እንደነገሩ ሁኔታ፥ በተከሳሹ ወይም

በከሳሹ ላይ ፍርዱን ይሰጣል።

ፍርድ ተመነብኝ ባይ ይግባኝ ካላለ በቀር ክርክሩ በዚሁ ያበቃል።[28]

ሰ/ ይግባኝ ማሰማት

ይግባኝ በፍሬ ነገር ወይም በይገባል ወይም በተፍጻሜ ሊመሠረት ይቻላል። በማንኛውም ፍርድ ወይም ጊዜያዊ ትዕዛዝ የሚቀርብ ቅሬታ በዳኞች ብቻ ሳይሆን በቆርቋሪዎች ማለትም በፍርድ ቤቱ በተገኙ ተችዎች ጭምር ይመረመራል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ በቁጥር 184 እንደተመለከተው የትእዛዝ ይግባኝ እምብዛም አልነበረም። በተፍጻሜ ጉዳይ የተሰጠው ትእዛዝ የፍሬ ነገሩን ክርክር የሚጎዳበት መስሎ ሲታየው፤ ከተከራካሪዎቹ አንደኛው ወገን በፍርድ ቤቱ በተሰጠ ትእዛዝ ይግባኝ ለማለት ይችል ነበር። ለምሳሌ በባለንብረትነት ክርክር በአንድ በተለየ ኅብረተሰብ ልማዳዊ ሕግ የትድሚያ መብት /ፕሬኤሚቲቭ ራይት/

ስለመኖሩ፥ በማስረጃቱ ዘዴ ረገድ በተፍጻሚው ክርክር ላይ ብያኔ መስጠቱ ወዲያውኑ መፍትሄ ካልተገኘ በቀር የተከራካሪውን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ፤ በተፍጻሚ ጉዳይ በተሰጠ ትእዛዝ ይግባኝ ማቅረብ፥ በቂ ምክንያት ሁኖ ይቆጠር ነበር።

ለበላይ ፍርድ ቤት በተለይም ለአፈ ንጉሡ[29] የሚቀርበው ሌላው ነገር የሕግ አተረጓጎም ጥያቄ ነበር። የይግባል ክርክር፤ ማለትም አንድን ክስ የማስረዳት መብት ያለኝ እኔ ነኝ የሚለው ክርክር እና የሕግ ትርጓሜ ጥያቄ የሚቀርበው በራስ ወንበሮች[30] ለሚታገዘው ለአፈ ንጉሡ ነበር። አንድ ዓይነት ሁኔታ እንዴት እንዲፈታ ወይም ጥያቄዎች እንዴት እንደሚተረጎሙ አመራር ለማግኘት፥ የበታች ፍርድ ቤት ዳኞች ጉዳዩን የሚያስተላልፉት ለዚሁ ፍርድ ቤት ነበር።

3. ማጠቃለያ

ባለፈው ምዕተ ዓመትና በያዝነው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ በተጠየቅ መጓት ሥርዓት ይካሄድ የነበረው የክርክር ሥልት ፍጹም ኢትዮጵያዊና ልዩም ነበር።

ከዚህ በላይ በአጭሩ እንደተገለጸው የጥንቱን የኢትዮጵያ ሕግ ጠለቅ ብሎ ለመረመረ ከመሠረታዊ ሕጎች ይልቅ የሥነ ሥርዓት ሕጎች በይበልጥ መዳበራቸውን መረዳት ይቻላል። ይህም ሊሆን የቻለው <u>የፍትሐ ነገሥት</u>[31] ሊቃውንት በሚያስተምሩት፤ በአገሪ ገዢዎች፥ በቤተ መንግሥት ችሎቶች ላይ በመዋል ወጣቶች የፍርድ ሥርዓት እንዲለማመዱ በማድረግ ለፍትሕ በሚሰጠው ከፍተኛ ልማዳዊ ግምት ምክንያት ሁኖ ይገኛል። መጓት ቢያንስ የመንገድ ዳር ፍርድ ቤትን በተመለከተ በበኩ ፍቃድና ወዲያውኑ የሚከናወን መሆኑ፤ የፍትሕ አስተዳደር ለማንኛውም ሕግ አክባሪ ዜጋ ሕዝባዊ ግዴታ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህንና ሌሎች ሁኔታዎች ተጣምረው፥ ልማዳዊ የሥነ ሥርዓት ሕግ በአንጻራዊ አገላለጽ በይበልጥ እንዲዳብር ለማድረግ አስችለዋል።

ማስታወሻዎች

1. እሰጥ አገባ ማለት ውርርድ መትከል፣ ማለትም ባላጋራው እሰጣለሁ ያለውን ውርርድ ቢረታ ለመክፈል መስማማት ማለት ነው። ሺበሺ ለማ የጥንቱ እሰጥ አገባ ሙግት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ክፍል የቀረበ የመመረቂያ የምርምር ጽሁፍ /ያልታተመ፣ ከሕግ ፋኩልቲ አርሽቭ፣ 1965 ዓ.ም./

2. ዘርጂን ኤሪክ ዘ አብሲኒያ አይ ኒው (ሎንደን፣ ማክሚላን ኤንድ ካምፓኒ ሊሚትድ እ.ኤ.አ 1936) ገጽ 91፣ በሺበሺ ለማ የጥንቱ እሰጥ አገባ ሙግት ገጽ 2 የተጠቀሰ።

3. በብዙዎቹ የታወጁ ሕጎች መቅድም ላይ ማንኛውም ሰው በተላላፊ መንገደኛ ላይ ባላጋራውን ለመክሰስ መብት እንዳለውና ተላላፊ መንገደኛው እንደዳኛ ሁኖ ለማገልገልና ፍትሕ ለማስገኘት ሥልጣን እንዳለው ይገለጽ ነበር።

4. የመንገድ ዳር ዳኛ የተጠየቅ ሙግትን ሥርዓት አይከተልም።

5. ጭቃ ሹም የሚባለው የአንድ የተወሰነ አካበቢ ሹም ነው።

6. መልከኛ የቀበሌ ገዥ ነው።

7. በተለያየ ደረጃ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ቁጥራቸው የተለያዩ ተቺዎች ወይም ቀርቋሪዎች በሁለት ተከራካሪ ወገኖችና በዳኛው ይመረጡ ነበር። ቁጥራቸውም ከስድስት እስከ ስምንት ይለያይ ነበር።

8. በሁሉም ክሶች ሁሉም ዓይነት ዋሶች አይጠሩም።

9. ይህም በገንዘብ ይከፈል የነበረ ውርርድ ነበር። ማለትም በማር ለተተከለ ለያንዳንዱ ውርርድ አራት ብር ይከፈል ነበር።

10. ለማመሳከር የሚመደብ ዳኛ ነው።

11. ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል <u>የኛም አሉ እንውታቸው</u> /አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት 1958 ዓ.ም. ያልታተመ/ ገጽ 8።

12. ዝኒ ከማሁ።

13. የቤተ ክርስቲያን በር የሚዘጋው ለከፍተኛ ጉዳይ ብቻ ነው።

14. የቀድሞ ዳኛና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን ከሆኑ፥ የጥንቱን የሙግት ሥርዓት ከሚያውቁ ከፊታውራሪ አበበ ገብሬ ጋር የተደረገ ቃለ መጠየቅ።

15. ዝኒ ከማሁ።

16. የተለየ ጭብጥ ለመስማት የተመረጡ ተቾዎች።

17. ማኅተመ ሥላሴ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው በገጽ 40።

18. ዝኒ ከማሁ።

19. ሺበሺ ለማ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው በገጽ 2።

20. "ከእሬ" ማለት ተነጋጋሪየን ይዤ መቅረቢያ ጊዜ ይሰጠኝ በማለት የሚቀርብ ጥያቄ ሲሆን፥ እንደዚህ ያለው ጥያቄ የሶስት ቀን ቀጠሮ ያሰጣል።

21. "ከጠበቃዩ" ማለት ጠበቃ ይዞ የመቅረቢያ ጊዜ እንዲሰጥ የሚቀርብ ጥያቄ ሲሆን፤ የሰባት ቀን ቀጠሮ ያሰጣል።

22. ማኅተመ ሥላሴ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ገጽ 40።

23. ቀጥታ ትርጉሙ የንጉሥ ማለት ሲሆን፥ በፍርድ ቤት በመሠረታዊ ሕግነት ወይም በሥነ ሥርዓት ሕግነት በአገሪቱ ተቀባይነትና ተፈጻሚነት ያለውን የልማዳዊ ሕግ መርሆዎች መጥቀስ ማለት ነው።

24. ማኅተመ ሥላሴ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው በገጽ 40-41።

25. ከቀድሞ የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን ከቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ጋር የተደረገ ቃለ መጠየቅ።

26. ማኅተመ ሥላሴ ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ገጽ 39።

27. ከፊታውራሪ አበበ ገብሬ ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ።

28. ከ1928 ዓ.ም. በፊት የነበረው የመደበኛ ፍርድ ቤቶች የተዋረድ ደረጃ የሚከተለው ነበር:-

    1. የዙፋን ችሎት
    2. የአፈንጉሥ ፍርድ ቤት /ብሄራዊ ሥልጣን ያለው/
    3. የሻለቃ ፍርድ ቤት /አውራጃ ፍርድ ቤት/
    4. የአካል ዳኛ /የወረዳ ፍርድ ቤት/
    5. የሥር ወይም የአፈር ዳኛ /የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት/

29. "አፈንጉሥ" የሚባለው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ነበር።

30. "ራስ ወንበሮች" የሚባሉት አፈንጉሡን እንዲያግዙ በማዕከላዊ መንግሥት የሚሾሙ ዳኞች ሲሆኑ፤ በስድስት ችሎት ተከፍለው ከተመደበላቸው ክልል የሚቀርቡ ይግባኞችን የሚሰሙ ዳኞች ነበሩ።

31. ፍትሐ ነገሥት በ15ኛውና በ16ኛው ምዕተ ዓመት መካከል ወደ ኢትዮጵያ የገባና በዳግማዊ አጼ ምኒልክ በ1900 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ሕግ ተርታ የገባ የሕግ መጽሀፍ ነው።